3205

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል
# በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች ተማሪዎች
# በአማርኛ የሚከውኗቸው የጽህፈት
# ስራዎች ንጽጽራዊ
# ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምረቃ
ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናት /ቴሲስ/

በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ
ለማስተር ኦቭ አርትስ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት


በ

ግርማ አውግቸው


አዲስ አበባ
ሰኔ 1988 ዓ.ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
# ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል

በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች ተማሪዎች

በአማርኛ የሚከውኗቸው የጽህፈት

ስራዎች ንጽጽራዊ

ጥናት

በ

ግርማ አውግቸው

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

YENAS ADMASSU ______________________ Yonas Admasu ______________________

አማካሪ

Tekle Minas ______________________ ______________________

ፈታኝ

YILMA KEBEDE ______________________ ______________________

ፈታኝ

# ምስጋና

አማካሪዬ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ ከከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታ ስህተቶች በተጨማሪ ዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታ ስህተቶችን በማረም፣ ከጥናቱ መነሻ እስከ መድረሻ ገንቢ አስተያየቶች በመስጠት፣ በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ግልጽ ውይይት እንዳደርግ በወንድማዊ አቀራረባቸው በማበረታታትና በውይይቱም ጠቃሚ ሀሳብ በመስጠት ላደረጉልኝ ምሁራዊ ምክር ምስጋናዬ ወደር የሌለው ነው::

ከጥናቱ መነሻ ላይ ገንቢ አስተያየት በመስጠት አካሄዱ ሠምሮ ከዚህ እንዲደርስ አቅጣጫውን በማስተካከልና እስከመጨረሻው የጥናቱ ፍጻሜ ድረስ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ ምክራቸው፣ ክትትላቸውና በተለይም ልዩ ማበረታታታቸው ላልተለየኝ ለዶ/ር ሐይለሚካኤል አበራ ምስጋናዬ የልብ ነው::

ለዚህ ጥናት መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ጸሐፊዎች፣ ወ/ሮ ንጋቷ ብሩን እና ወ/ሪት ጽላት አድነውን ሳላመሰግናቸው አላልፍም:: በተለይም አቶ ደረጀ ገብሬ፣ አቶ ዘሪሁን አስፋው፣ አቶ በዛ ተስፋው እና ተማሪ ክበበ ጸሐይ ሠፊ መረጃ በተፈለገው ሰዓት ካለብዙ ድካምና ውጣ ውረድ እንዳገኝ ስለተባበሩኝ ምስጋናዬ ትልቅ ነው::

አቶ ብርሃኑ ገበየሁ ጊዜውን መስዋዕት በማድረግ ረቂቁን በማንበብ ላደረገልኝ የአርትኦት ስራ፣ የድሬዳዋው የስራ ባልደረባዬ አቶ ታደሰ ክፍሌ ላደረገልኝ የማመሳከሪያ ንባብ (proof reading) ጓደኛዊ ምስጋናዬ እንዳልተለያቸው ልገልጽ እወዳለሁ::

በመጨረሻም፣ በአንድ ጊዜ ከተለያዩ ሰ ዎች ምሁራዊ አስተያየት ለመሰብሰብ እንድችል የጥናቱን ረቂቅ ጽሁፍ በሦስት ኮፒ በታይፕ ለተየበችልኝ ለእህቴ ለወ/ሪት በላይነሽ አውግቸው፣ የመጨረሻውን ጽሁፍ በኮምፒውተር ለተየበችልኝ ለወ/ሮ አስማሩ ያለው እና በኮምፒውተር ትየባው ላይ ቴክኒካዊ እና ቁሳዊ ዕርዳታ ላደረገልኝ ለአቶ በሽር መሐመድ ከፍተኛ ምስጋናዬ ይድረሳቸው እላለሁ::

# የአርዕስት ማውጫ

አርዕስት ገጽ

ምስጋና ........ I

የአርዕስት ማውጫ ........ II

የሠንጠረዥ ማውጫ ........ V

የአባሪ ማውጫ ........ VI

አጠቃሎ ........ VII

ምዕራፍ አንድ - መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ........ 4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ........ 5

1.4 ስለበሳል ድርሰትና ሌሎች የአማርኛ ኮርሶች አጭር መግለጫ. 6

1.5 የጥናቱ ወሰን ........ 8

1.6 በጥናቱ የሕትመት ዓመትና የእንግሊዘኛ ስሞች አጠቃቀም........ 9

1.7 የጥናቱ አወቃቀር ........ 10

ምዕራፍ ሁለት - የተዛማጅ ድርሳን ክለሳ ........ 11

2.1 ጽህፈትን ማስተማር ........ 11

2.1.1 ጽህፈትን የማስተማር ስልተ ትውሮች ........ 11

2.1.1.1 ውጤት ተኮር ስልተ ትውር ........ 11

2.1.1.2 ሂደት ተኮር ስልተ ትውር ........ 12

2.1.2 በተለያዩ የትምህርት መስኮች ጽህፈትን ማስተማር ........ 15

2.1.2.1 በመጀመሪያ ቋንቋ ጽሀፈትን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ለማስተማር የተደረገ እንቅስቃሴ ........ 16

2.1.2.2 በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ ጽህፈትን በተለያዩ........ የትምህርት መስኮች ለማስተማር የተደረገ እንቅስቃሴ ........ 20

2.2 በትምህርት መስኮች የሚከወኑ የጽህፈት ስራዎችን የማጥናት አስፈላጊነት.................................. 21

2.2.1 የጽህፈት ዓይነቶች.................................. 22

2.2.2 ጽህፈትን ለማስተማር የተሻለ «ዘዴ».................. 25

2.2.3 ለተማሪ ጽሁፎች የመምህራን ምላሽ..................... 27

2.3 በሀገራችን የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተደረጉ ስራዎች...... 29

2.3.1 በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተደረጉ ስራዎች.................................. 29

2.3.2 በሃገራችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልን............ አስመልክቶ የተሠሩ ስራዎች.................................. 32

2.4 አካዳሚያዊ ጽህፈትን ለመበየን የተደረጉ ስራዎች.................. 34

ምዕራፍ ሦስት - የጥናቱ ንድፍ.................................. 37

3.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኒኮች.................................. 37

3.1.1 መጠይቅ.................................. 37

3.1.1.1 የተማሪ መጠይቅ.................................. 37

3.1.1.2 የመምህር መጠይቅ.................................. 38

3.1.2 የኮርስ ቢጋርና መግለጫ.................................. 39

3.1.3 ቃለመጠይቅ.................................. 39

3.1.4 የተማሪ ጽሁፎች.................................. 40

3.2 የመረጃ አተናተን ስልት.................................. 41

3.2.1 የጽሁፍ ስራዎች አከፋፈል ስልት.................................. 41

3.2.2 የመምህራን የእርማት ባህርይ አተናተን ስልት............ 42

ምዕራፍ አራት - ውጤትና ማብራሪያ.................................. 44

4.1 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች.................. 44

4.1.1 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች ዓይነት... 45

4.1.2 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች ባህርይ... 46

4.1.3 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች አከዋወን 48

4.1.4 በበሳል ድርሰት ኮርሶች ለተማሪ ጽሁፎች የመምህሩ ምላሽ.................................................... 49

4.2 በሳል ድርሰት ባልሆኑ ኮርሶች የጽህፈት ስራዎች................. 54

4.2.1 የጽህፈት ስራዎች ዓይነት፤ ምደባና ገለጻ................. 54

4.2.2 የጽህፈት ስራዎች አስፈላጊነት................................ 59

4.2.3 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮችና በጽሁፎቻቸው ውስጥ የሚታዩ ድክመቶች.................. 62

4.2.3.1 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮች.................................................. 62

4.2.3.2 በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶች.......................................................... 62

4.2.4 ለተማሪ የጽሁፍ ስራዎች የመምህራኑ ምላሽ........... 63

4.3 በበሳል ድርሰትና በሌሎች የአማርኛ ኮርሶች የሚከወኑ የጽህፈት ስራዎች እርስ በዕርስ ያላቸው ዝምድናና ልዩነት................. 65

ምዕራፍ አምስት - መደምደሚያና አስተያየት.............................. 68

5.1 መደምደሚያ..................................................................... 68

5.2 አስተያየት........................................................................ 70

ዋቢ ጽሁፎች.................................................................................. 73

ሙዳየ ቃላት.............................................................. 80

አ ባ ሪ........................................................................ 82

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ ገጽ

1. በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል በቀኑ መርሃ ግብር አማርኛን ዋና ያደረጉ ተማሪዎች በአማርኛ የሚወስዷቸው ኮርሶች ዝርዝር .......... 7

2. በበሳል ድርሰት ኮርሶች ተማሪዎች የከወኗቸው ጽሁፎች ስብስብ ዝርዝር ..... 40

3. በበሳል ድርሰት 1 ለተማሪዎች ጽሁፎች የመምህሩ የእርማት ትኩረት ..... 51

4. በበሳል ድርሰት ኮርሶች ለተማሪ ጽሁፎች የመምህሩ የጽሁፍ እርማት ትኩረት .. 52

5. ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች የጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት ..... 60

6. የጽሁፍ ክሂሎች አስፈላጊነት ደረጃ .................... 61

7. በተማሪዎች የጽህፈት ስራዎች ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩ ድክመቶች ... 63

8. በተማሪ ጽሁፎች ላይ የመምህሩ የጽሁፍ እርማት ............... 64

## የአባሪ ማውጫ


አባሪ ገጽ

ሀ/ መጠይቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 83

ሀ.1 የመምህሩ መጠይቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 83

ሀ.2 የተማሪ መጠይቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 85

ለ/ የበሳል ድርሰት ኮርሶች ቢጋሮችና መግለጫ . . . . . . . . . . . . . . . 87

ለ.1 የበሳል ድርሰት ኮርሶች ቢጋሮች . . . . . . . . . . . . . 87

ለ.1.1 የበሳል ድርሰት I ቢጋር . . . . . . . . . . . . . . . . 87

ለ.1.2 የበሳል ድርሰት II ቢጋር . . . . . . . . . . . . . 88

ለ.2 የበሳል ድርሰት ኮርሶች መግለጫ . . . . . . . . . . . . . . . 89

መ/ የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89

መ.1 ለበሳል ድርሰት ኮርሶች መምህርና ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች . . 89

መ.2 ለሌሎች ኮርሶች መምህራንና ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች . . . . . 90

ረ/ በተማሪ ጽሁፎች ላይ የተደረጉ የጽሁፍ እርማቶች ትንተና . . . . . . . . . 91

ረ.1 የጽሁፍ እርማቶች ክፍፍል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 91

ረ.2 የጽሁፍ እርማቶች አተናተን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 91

ሰ/ የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ዝርዝር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 92

ሸ/ ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮችና የሚያልፉበት የጽሁፍ ሂደት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 93

ሸ.1 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮች . . . . . . . . 93

ሸ.2 ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ ለመጻፍ የሚያልፉበት ሂደት . . . . . . . 94

## አ ጠ ቃ ሎ

ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል አማርኛ ዋና ትምህርታቸው ለሆኑ መደበኛ ተማሪዎች በሚሰጡ በበሳል ድርሰትና በሌሎች የአማርኛ ኮርሶች ውስጥ ተማሪዎች የሚከውኗቸውን የጽህፈት ስራዎች የሚመለከት ነው፡፡ ጥናቱ በአላማው በበሳል ድርሰት የሚደርጉት የጽሀፈት ልምምዶች በሌሎች ኮርሶች ከሚከወኑት የጽህፈት ስራዎች ያላቸውን መጣጣምና መደጋገፍ፣ የበሳል ድርሰት ኮርሶች በሌሎች ኮርሶች ለሚያስፈልጉ የጽህፈት ስራዎች የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ፣ ሌሎች ኮርሶች ደግሞ የጽህፈት ክሂልን ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት መርምሮ ማሳየት ነው፡፡

የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስም በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች የሚከወኑ የጽሁፍ ስራዎች አይነትና ባህርይ፣ በጽህፈት ስራዎቹ አስፈላጊ የሆኑ የጽህፈት ክሂሎች፣ መምህራን ለተማሪዎች ጽሁፎች የሚሰጡት ምላሽ እና ሌሎች በጥናቱ ተፈላጊ የሆኑ ዝርዝር ነጥቦች ከቃለመጠይቅ፣ ከመጠይቅ፣ ከኮርስ ቢጋርና መግለጫና ከተማሪ ጽሁፎች በተገኙት መረጃዎች መሠረትነት ተተንትነዋል፡፡

ከነዚህ ምንጮች የተገኘው የመረጃ ትንተና እንደሚያሳየን በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት የጽህፈት ልምምዶች ከአረፍተ ነገር ምስረታ አንስቶ ሙሉ ድርሰትን በገላጭ፣ በተራኪ፣ በአስረጂና በአከራካሪ ድርሰቶች እስከመከወን ይደርሳሉ፡፡ ልምምዶቹ ከተለያዩ ነገሮች (ከንባብ፣ ከስእል፣ ከተፈጥሯዊ ገጽታ) ጋር በመቀናጀት የሚቀርቡ ቢሆንም አብዛኞቹ ከግል ገጠመኝ ወይም ስሜት በመነሳት የሚከወኑ ናቸው፡፡ በነዚህ ኮርሶች የመምህሩ እርማት ከይዘት ይልቅ በቅርጽ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እርማቱም የሚሰጠው በአብዛኛው (80%) በተማሪዎች የመጨረሻው ጽሁፍ ላይ እንጂ በረቂቅ ጽሁፎቻቸው ላይ አይደለም፡፡

በሌላው መልኩ፣ ከበሳል ድርሰት ውጭ ባሉ ኮርሶች የሚከወኑት ጽሁፎች የተለያዩ አይነት ናቸው፡፡ ሆኖም በአብዛኞቹ ኮርሶች የሚጻፉት ተማሪዎች በይዘቱ (subject matter) ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳዩ ነው፡፡ የእነዚህ ሀሳብ ምንጭ ከባዶ ወይም ከግል ገጠመኝና ስሜት የሚነሳ አይደለም፡፡ የእነዚህ ስራዎች የሀሳብ ምንጭ ንባብ ወይም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከኮርሱ የተገኘው እውቀት ነው፡፡ በነዚህ ኮርሶች ተማሪዎች የሚጽፏቸው ጽሁፎች አብዛኞቹ አይመለሱም፡፡ መምህራኑ በጽሁፎቹ ላይ የሚሰጡት እርማት ባብዛኛው ማርክ (ቁጥር) መጻፍ ብቻ ሲሆን፣ ስህተቶችን በማመልከት የሚደረጉት እርማቶችም ከቅርጽ ይልቅ በይዘት ላይ በከፍተኛ ደረጃ የሚያተኩሩ ናቸው፡

ከነዚህ ነጥቦች አንጻር ስንመለከት በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል የጽህፈት ክሂልን በመተጋገዝና በመተባበር ለማዳበር የሚደረገው ጥረት ደካማ መሆኑን የመረጃው ትንተና አሳይቷል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጥናት ግኝት በመነሳት ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል የተሻሉ ጸሀፊዎችን ለማፍራት ይቻለው ዘንድ የበሳል ድርሰት እና የሌሎች ኮርሶች መምህራን ተሰባስበው የሚወያዩበትን መንገድ ክፍሉ እንዲያመቻች፣ የድርሰት መምህራን የጽህፈት ልምምዶቹ ከግል ገጠመኝ በመነሳትና በመጨረሻው ውጤት ላይ በማተኮር እንዲከወኑ ከማድረግ የጽሁፍ ሂደትን ንባብ-ምርኩዝ በሆኑ ስራዎች በማቀናጀት ቢያስተምሩ የተሻለ እንደሚሆን፣ የሌሎች ኮርሶች መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፎች በወቅቱ አርመው እንዲሰጡ፣ በእርማቱም ይዘት ላይ ከማተኮር ወይም ማርክ ብቻ ከመጻፍ ሌሎች የጽሁፍ ገጽታዎችን ተመልክተው ተማሪዎች ድክመት ያለባቸውን ገጽታ በማመልከት እርማታቸውን እንዲያደርጉ በዚህ ጥናት ተጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መ ግ ቢ ያ

### 1 . 1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ ጽህፈትን መማር ለተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ከመሆኑም በላይ፣ ከመካከላቸው የክሂሉ ባለቤት ለመሆን የሚበቁበት በጣም ጥቂቶች እንደሆኑ ይነገራል:: በእርግጥም፣ ጥሩ ድርሰትን መጻፍ መቻል ከባድ፣ አዝጋሚ ሂደት የሚታይበት፣ ብዙ ተማሪዎችን የሚያስጨንቅና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው (Richards 1990:100 ፣ Davies & Widdowsen 1974:77):: በአንጻሩ ጥሩ የመጻፍ ክሂል፣ ለስነትምህርታዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት ፣ ለተለያዩ ስራዎችና ሙያዎች እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው::

ይህ አስፈላጊና ጠቃሚ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ ረገድ ባሁኑ ጊዜ ምን ይመስላል? ብለን ስንጠይቅ ክሂሉ በከፍተኛ ደረጃ የደከመ መሆኑን በውል ከምናስተውለው በተጨማሪ የተለያዩ ጥናቶችም ይህንኑ ያረጋግጣሉ:: "ሁለተኛ ደረጃ የጨረሰ ተማሪ፣ ዛሬ ጥሩ የስራ ማመልከቻ ቀርቶ ተራ ደብዳቤ እንኳ መጻፍ እየተሳነው መጥቷል "( ባዬ 1987:8):: በሕትመት ደረጃ "አለቀላቸው" ተብለው ለአንባቢ የሚሰራጩትም ጽሁፎች(ጋዜጦች፣ መጽሄቶችና መጻህፍት) በርካታ ስህተት ይታዩባቸዋል (ተስፋዬ 1986:10):: ባጠቃላይ፣ ዛሬ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን አስመልክቶ የተማሪዎችም ሆነ ሙያቸው አስገድዷቸው የሚጽፉ ጸሐፍት ጽሁፎች ደካማ እንደሆኑ ሌሎች ጥናቶችም ይገልጻሉ (ክፍሌ 1986፣ አለማየሁ 1986፣ አምሳሉና ደምሴ 1982)::

ይሁን እንጂ የዚህ ችግር ምክንያት የቋንቋው ትምህርት በሀገሪቱ የትምህርት መርሃ ግብር (program) ወይም ስርዓተ ትምህርት ካለመካተት የመነጨ አይደለም:: ችግሩ፣ ቋንቋው በትምህርትነት ቢቀርብም የክሂሉ አሰጣጥ የተዳከመና በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት የተነፈገው ከመሆኑ ላይ ያርፋል (ለአስረጅ ስለሞን 1987 እና ከላይ የተጠቀሱትን የአማርኛ ስራዎች ይመለከቷል):: ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከፍ ብለን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስንመለከትም፣ ይህን ቋንቋ ራሱን በቻለ የትምህርት ክፍል ተማሪዎች የሚሰለጥኑበት ሆኖ እናገኘዋለን:: ከተቋማቱ አንዱ በሆነው በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ውስጥም ይህ ቋንቋ ይሰጣል:: ይህ ክፍል ተማሪዎችን

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ውስጥም ይህ ቋንቋ ይሰጣል፡፡ ይህ ክፍል ተማሪዎችን ለተለያዩ ሙያዎች በማሠልጠን አገሪቱ ውስጥ ካሉት ሌሎች ተመሳሳይ ክፍሎች አንጋፋውና ሠፊው እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ዛሬ፣ ከዚህ ክፍል ተመርቀው የወጡ ተማሪዎች በቋንቋው የጽህፈት ስራዎች በሚጠይቁ ሙያዎችና ቋንቋውን በማስተማር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም ከዚህ ትምህርት ክፍል (ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል) ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች ለክሂሉ መዳበርም ሆነ መድከም ጉልህ ቦታ እንደሚኖራቸው መገመት አያዳግትም፡፡ በሌላው መልኩ በማናቸውም ጸሐፊት ዘንድ የሚከወኑ ጽሑፎች ጥራትም ሆነ ድክመት ጸሐፊቱ የወሰዷቸውና /ወይም የሚወስዷቸው ስልጠናዎች አቢይ ሚና እንደሚጫወቱ በመስኩ ጥናት ያደረጉ ምሑራን ይገልጻሉ (ለምሳሌ White 1989፣ White 1987፣ Herrington & Moran 1992 ወዘተ.ን መጥቀስ ይቻላል)፡፡

ይህ ከሆነ፣ በትምህርት ክፍሉ ተማሪዎች ለክሂሉ መዳበር የሚወስዷቸው ስልጠናዎች እንደምን ያሉ ናቸው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለናል፡፡ በዚህ የትምህርት ክፍል ራሳቸውን የቻሉ ዓላማና ይዘት ያላቸው የተለያዩ ኮርሶች ይሰጣሉ፡፡ የጽሕፈት ክሂልን አስመልክቶም በሁለተኛ ዓመት ለሚገኙ ተማሪዎች የሚሰጡ ለሁለት ተከታታይ ሴሚስተሮች፣ ሁለት የበሳል ድርሰት ኮርሶች አሉ፡፡ የእነዚህ ኮርሶች ዓላማ ተማሪዎች የተለያዩ የክሂሉን ንዑሳን ክሂሎች (ክፍሎች) በመማርና በመለማመድ ለተለያዩ ተግባራት ሊውሉ የሚችሉ ድርሰቶችን መጻፍ እንዲችሉ እንደሆነ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የሚገኘው የኮርሶቹ መግለጫ (Course description) ያሳያል፡፡ ሆኖም ተማሪዎቹ ኮርሶቹን ከወሰዱ በኋላ በሌሎች ኮርሶች የሚያጋጥሟቸውን የጽሑፍ ስራዎች ለመከወን ያላቸው ችሎታና የጨበጡት ክሂል ምን ያህል ብቃት አለው? የሚለው ጉዳይ አጠያያቂና በእጅጉ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡

በዚህ ክፍል (በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል) የተለያዩ ኮርሶችን በማስተማር ላይ የተሰማሩ መምህራን፣ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን የጽህፈት ስራዎች ተማሪዎቹ በቀላሉ ለማከናወን የሚያስችል ብቁ ክሂል እንደሌላቸው ይናገራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት እጅግ ሲያማርሩ ይሰማሉ፡፡ ዳሩ ግን መምህራኑ የሚማረሩበትን ችግር መርምሮ የችግሩን ምክንያትና መፍትሔ ያመለከተ ስራ አላጋጠመንም፡፡

በተመሳሳይ ፣ የትምህርት ክፍሉ የሚሰጣቸው የበሳል ድርሰት ኮርሶች በራሳቸው፣ በሌሎች ኮርሶች የሚቀርቡ የጽህፈት ስራዎችን ለመከወን በማዘጋጀት ረገድ ያላቸው ጠቀሜታዎችና አስተዋጽኦዎች ምን ያህል እንደሆነና በአንጻሩም ሌሎች ኮርሶች ክሂሉን በማዳበር አኳያ ያላቸው ሚና ምን እንደሆነ የሚያሳይ መረጃም እንዲሁ አላገጠመንም:: በእርግጥ፣ ይህ ሊታወቅ የሚችለው በተለያዩ ኮርሶችና በበሳል ድርሰት ኮርሶች ስላለው የጽሑፍ ሁኔታ መረጃ ሲገኝ ነው (Leki & Sarson 1994:84)::

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የድርሰት ኮርሶች መምህራንና የሌሎች ኮርሶች መምህራን ስለተማሪዎች ጽሑፎች ያላቸው ግንዛቤ አብዛኛውን ጊዜ የተለያየ ነው:: ከድርሰት ኮርሶች ውጭ የሚያስተምሩ መምህራን ለተማሪዎች ድርሰት የሚሰጡት ምላሽ በይዘት ላይ ያተኮረ ነው (Longer 1992፣ Oderl 1992):: በድርሰት ኮርሶች የመምህራኑን ምላሽ ያጠኑ ደግሞ ከይዘት ይልቅ በቅርጽ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሆነው አግኝተዋቸዋል ( ለዚህ ጉዳይ Zamel 1985፣ Cohen 1987፣ Cohen & Covalcanti 1990፣ Getnet 1993፣ Reid 1994 እና Leki 1990ን ለተመሳሳይ ጥናቶች ቅኝት ይመለከቷል) :: በሌላ በኩል በዩኒቨርስቲ ትምህርት በርካታ ዓይነት የጽሑፍ ስራዎች አሉ:: የስራዎች ዓይነት በየትምህርት ደረጃዎቹ ፣ በየትምህርት ዘርፎቹና በአንድ የትምህርት ዘርፍ ውስጥ ባሉት ኮርሶች መካከልም ሊለያዩ እንደሚችሉ Shih (1986)፣ Kussel (1992) ወዘተ. ይገልጻሉ:: ይሁን እንጂ በድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት ልምምዶች ደግሞ በአብዛኛው የሚያተኩሩት በግላዊ ብዕርግ (Personal Essay) ላይ ሲሆን የዚህ ዓይነቱ ጽሑፍ ግን በሌሎች ኮርሶች እምብዛም አይታይም (Kroll 1979)::

በአንጻሩ፣ ተማሪዎች በአካዳሚያዊ ማኅበረሰብ አባልነታቸው የሚከውኗቸው ጽሑፎች በድርሰት ትምህርት ከተለማመዷቸው ጽሑፎች የተለዩ ከሆኑ፣ ለድርሰቶቻቸው የሚያገኙት ምላሽ እንዲሁ ከተለያየ የድርሰት ትምህርታቸው ጠቃሚነቱ አጠያያቂ ነው (Brooks & Grundy 1990)::

ተማሪዎችን ለቀጣይና ለዘላቂ የመጻፍ ፍላጐት ለማብቃትና ጥሩ ክሂል እንዲጨብጡ ለማድረግ በሚገቡበት የዲስኩር ማህበረሰብ (Discourse Community) ያለውን የጽሑፍ እውነታ ያገናዘበ ትምህርት በድርሰት ትምህርታቸው ሊያገኙ ይገባል:: ይህን ለማድረግ ደግሞ በቅድሚያ በአካዳሚያዊ ጥናታቸው የሚያጋጥሟቸውን የጽሑፍ ስራዎች በጥልቀት ማጥናት ያስፈልጋል:: በሌላ መልኩ፣ የተሻለ ስነዘዴ የሚባለው፣ በአሁኑ ጊዜ ጽህፈትንም ሆነ ቋንቋን ለማስተማር

በስርዓት ተቀንብቦ ከተዘጋጀ አለም አቀፋዊ ትውር (Global Theory) የሚመነጭ ሳይሆን መምህራኑና ተማሪው ከሚገኙበት ክፍል፣ ባጠቃላይ ከአካባቢው እውነታ የሚመነጭ ነው (Torane & Yule 1989)፡፡

በጽህፈት ትምህርትም የተሻለ ዘዴ ለመምረጥና ለመጠቀም፣ ለድርሰት መምህራኑ ተገቢውን መረጃ ለመስጠትና የሌሎች ኮርሶች መምህራን ክሂሉን በማዳበር በኩል ሊኖራቸው የሚችለውን አስተዋጽኦ ለመግለጽና ለመጠቀም፣ በተለያዩ ኮርሶች ተማሪዎች የሚከውኗቸውን የጽሑፍ ዓይነቶች፣ እነዚያን ጽሑፎች መምህራኑ ለተማሪዎች የሚሰጡበትን ምክንያት፣ ተማሪዎቹ ጽሑፎቹን በመከወን ረገድ ያለባቸውን ችግር፣ በድርሰት ኮርሶች የሚደረጉትን ልምምዶችና ለጽሑፎቹ የመምህራኑን ምላሽ ማጥናት እንደሚገባ Spack (1988) ይገልጻሉ፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህን ነጥቦች ከግንዛቤ በማስገባት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍልም ሆነ በማናቸውም ሌሎች ተቋማት፣ በአማርኛ የጽህፈት ስራዎች ላይ የተደረገ ስራ አላጋጠመንም፡፡በመሆኑም የኢትዩጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የተሻሉ የክሂሉ ባለቤቶችን (ጸሐፍትን) በማፍራት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በክፍሉ በአማርኛ በሚሰጡ ኮርሶች ውስጥ እነዚህን ነጥቦች መርምሮና ተንትኖ ማሳየት የዚህ ስራ አጠቃላይ ግብ ነው፡፡

## 1 . 2 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል በአማርኛ በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች የሚከወኑ የጽሑፍ ስራዎችን መጣጣም አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን መደጋገፍ ማሳየትና በተለይም ተማሪዎች አሁን ካሉበት ደረጃ የተሻሉ ጸሐፍት የሚሆኑበት መንገድ ካለ እሱን መጠቆም ነው፡፡

ከዚህም በተጓዳኝ ጥናቱ የበሳል ድርሰት ትምህርት በምን መልክ በሌሎች ኮርሶች ለሚያስፈልጉ የጽህፈት ስራዎች ተማሪዎችን ማዘጋጀት ይችላል? እና ሌሎች ኮርሶችስ ለተማሪዎች ዘላቂ የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸው መዳበር ምን እና እንዴት ዓይነት አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ? የሚሉትን ነጥቦች ለመመለስ ያስችል ዘንድ የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች በየፈርጁ ይመለከታል፡፡

1. በሳል ድርሰት ባልሆኑ ኮርሶች ተማሪዎች ምን ምን ዓይነት የጽህፈት ስራዎችን ነው የሚከውኑት? እነዚህን የጽህፈት ስራዎች ለመከወን ምን ዓይነት ዝርዝር (Specific) ክሂሎች ናቸው የሚያስፈልጉት? መምህራኑ ለተማሪዎች ጽሑፎች የሚሰጡት ምላሽ ምን ይመስላል? ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን በመከወን ያጋጠማቸው ችግር (ካለ) ምንድን ነው?
2. በድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት የጽህፈት ልምምዶች ዓይነትና የአከዋወን ባሕርይ ምንድንነው? ለተማሪዎች ድርሰት መምህራኑ የሚሰጡት ምላሽ ምን ይመስላል?
3. በድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች መካከልና በሌሎች ኮርሶች የጽህፈት ስራዎች መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት አለ? (እርስ በእርስ መጣጣማቸውና መደጋገፋቸው ምን ያህል ነው?)

## 1 . 3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በርካታ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ይታመናል:: በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለበሳል ድርሰት መምህራንም ሆነ ለኮርሱ ነዳፍያን የጽህፈት ክሂልን በተሻለ መንገድ ለተማሪዎች ለማስጨበጥ፣ እንዴትና ምን ይቅረብ የሚለውን ለመወሰን ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች የማይናቅ መረጃ ይሰጣል:: በሌላው መልኩ በክፍሉ የሚገኙት የሌሎች ኮርሶች መምህራን ለተማሪዎቻቸው ዘላቂ የክሂላቸው መዳበር አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን መንገድ ይጠቁማል:: ሁለተኛው ፣ ለበሳል ድርሰት ተማሪዎች በሌሎች ኮርሶቻቸው የሚያጋጥሟቸውን የጽህፈት ስራዎች በቀላሉ ለመከወንና ለዘላቂ የጽህፈት ክሂላቸው መዳበር ማድረግ የሚገባቸውን በመጠቆም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እምነት አለን::

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተሻሉ ጸሐፍት እንዲሆኑ፣ ወይም፣ በሌላ አባባል፣ ጥሩ የጽህፈት ክሂል እንዲይዙ ለሚያደርገው ጥረት በዚህ ጥናት የሚቀርበው መረጃ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ በመስኩም ተመሳሳይ ጥናቶች እንዲደረጉ ያበረታታል፤ የመነሻ ሃሳብም ይሰጣል የሚል እምነት አለን::

## 1 . 4 ስለበሳል ድርሰትና ሌሎች የአማርኛ ኮርሶች አጭር መግለጫ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛ አብይ ትምህርታቸው ለሆነ ተማሪዎች (Amharic major students) የሚሰጡ 27 ኮርሶች አሉ:: እነዚህም አስራ አራቱ በመጀመሪያ ሴሚስተር፣ አስራ ሦስቱ ደግሞ በሁለተኛ ሴሚስተር የሚሰጡ ናቸው:: ከእነዚህም ሁለቱ የበሳል ድርሰት ኮርሶች ናቸው:: እነዚህ ኮርሶች በሁለት ተከታታይ ሴሚስተር በሁለተኛ ዓመት ደረጃ የሚሰጡ ናቸው::

በክፍሉ አማርኛ ቋንቋን አብይ ትምህርታቸው ያደረጉ የቀን ተማሪዎች በሁለት የተከፈሉ ናቸው:: እነዚህም፣ መምህራንና መምህራን ያልሆኑ (Teachers & Non-Teachers) ተብለው ይታወቃሉ:: አጠቃላይ ብዛታቸውም 64 ሲሆን፣ አርባ ስድስቱ "በመምህራን" አስራ ስምንቱ ደግሞ "መምህራን ያልሆኑ " በሚሉት ምድቦች የሚገኙ ናቸው::

በአንደኛው ሴሚስተር ከሚሰጡት አስራ አራት ኮርሶች አስራ ሁለቱን ከመምህርነት ውጪ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ሲወስዷቸው፣ ዘጠኙን ደግሞ ለመምህርነት ሙያ የሚሰለጥኑት ይወስዷቸዋል:: በሁለተኛው ሴሚስተር ካሉት አስራ ሦስት ኮርሶች አስራ ሁለቱን ከመምህርነት ውጪ የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ሲወስዱ ለመምህርነት ሙያ የሚሰለጥኑት ደግሞ ስምንቱን ይወስዳሉ:: (ዝርዝሩን ከሚከተለው ሠንጠረዥ ይመለከቷል::)

* በ1988 ዓ.ም 1ኛው ሴሚስተር የተወሰደ::

## ሰ ጠ ረ ዥ 1

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል በቀኑ መርሃግብር አማርኛን ዋና ያደረጉ ተማሪዎች አማርኛ የሚወስዷቸው ኮርሶች ዝርዝር

| ተ.<br>ቁ. | የ ኮ ር ሱ ር ዕ ስ | የኮርሱ<br>ቁጥር | ኮርሱን የሚወስዱ<br>ተማሪዎች | ኮርሱ የሚሰጥበት ዓመትና ሴሚስተር | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዓመት | ሴሚስተር |
| 1 | Fundamentals of Literature | ELAm 201 | ሁለቱም | 2 | 2 |
| 2 | Research & Report Writing | ELAm 202 | መምህራን ያልሆኑ | 2 | 1 |
| 3 | Introduction to Language & Lingustics I | Ling 201 | ሁለቱም | 2 | 1 |
| 4 | Introduction to Language & Lingustics II | Ling 202 | ሁለቱም | 2 | 2 |
| 5 | Advanced Ccomposition I | ELAm 203 | ሁለቱም | 2 | 1 |
| 6 | Advanced Composition II | ELAm 204 | ሁለቱም | 2 | 2 |
| 7 | Amharic Prose Fiction I | ELAm 301 | ሁለቱም | 3 | 1 |
| 8 | Amharic Prose Fiction II | ELAm 302 | መምህራን ያልሆኑ | 3 | 2 |
| 9 | Amharic Poetry I | ELAm 303 | ሁለቱም | 3 | 1 |
| 10 | Amharic Poetry II | ELAm 304 | መምህራን ያልሆኑ | 3 | 2 |
| 11 | Introduction to Major Literary Movements | ELAm305 | መምህራን ያልሆኑ | 3 | 1 |
| 12 | Oral Literature | ELAm 306 | ሁለቱም | 3 | 2 |
| 13 | Structure of Amharic I | ELAm 307 | ሁለቱም | 3 | 1 |
| 14 | Structure of Amharic II | ELAm 308 | ሁለቱም | 3 | 2 |
| 15 | Journalism I | ELAm 309 | መምህራን ያልሆኑ | 3 | 1 |
| 16 | Journalism II | ELAm 310 | መምህራን ያልሆኑ | 3 | 2 |
| 17 | Lingustics & Amharic Teaching I | ELAm 401 | መምህራ | 4 | 1 |
| 18 | Lingustics & Amharic Teaching II | ELAm 402 | መምህራን | 4 | 2 |
| 19 | Translation I | ELAm 403 | ሁለቱም | 4 | 1 |
| 20 | Translation II | ELAm 404 | መምህራን ያልሆኑ | 4 | 2 |
| 21 | Major Thematic Trends in African Literature | ELAm 405 | መምህራን ያልሆኑ | 4 | 1 |
| 22 | Workshop on Creative Writing | ELAm 406 | መምህራን ያልሆኑ | 4 | 2 |
| 23 | Seminar on Selected Topics I | ELAm 407 | ሁለቱም | 4 | 1 |
| 24 | Seminar on Selected Topics II | ELAm 408 | ሁለቱም | 4 | 2 |
| 25 | Lexicography | ELAm 409 | መምህራን ያልሆኑ | 4 | 1 |
| 26 | Survey of Ethiopian Literature | ELAm 410 | ሁለቱም | 4 | 2 |
| 27 | Subject Area Method & Practice Teaching | ELAm 411 | መምህራን | 4 | 1 |

ከሁለቱ ተከታታይ በሳል ድርሰት ኮርሶች (ELAm 203 እና ELAm 204) ሌላ፣ ጽህፈትን የሚመለከቱ ኮርሶች አሉ (ለምሳሌ ከሠንጠረዡ ተራ ቁጥር 2 እና 22ን ይመለከቷል):: የበሳል ድርሰት ኮርሶች ከአረፍተ ነገር አገነባብ እስከ ድርሰት መጻፍ ድረስ ትውራዊ ገለጻ በማድረግ ሲያለማምዱ፣ ሌሎች ጽህፈትን የሚመለከቱት ኮርሶች ደግሞ የተወሰነ የጽሁፍ ዓይነትን /ለምሳሌ የምርምር ጽሑፍ፣ የሪፖርት ጽሑፍ ወዘተ.ን/ ያስተምራሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህን

* መምህራንና መምህራን ያልሆኑ

** ከመምህርነት ሙያ ውጭ የሚሰለጥኑ

*** ለመምህርነት ሙያ የሚሰለጥኑ

**** ከክረምት (summer) መርሃግብር ባሁኑ ጊዜ ወደ ቀን የዞሩ ለመምህርነት ሙያ ሚሰለጥኑትንም ይጨምራል::

የጽሁፍ ዓይነቶች የሚማሩት በመምህርነት ሙያ የማይሰለጥኑት ተማሪዎች ብቻ ናቸው:: ባሁኑ ጊዜ (1988 ዓ.ም) 63.89% አካባቢ የሚሆኑት የክፍሉ መደበኛ ተማሪዎች እነዚህን ኮርሶች አይወስዱም:: ሁለቱም ቡድን የጽህፈት ክሂልን በሚመለከት በጋራ የሚወስዷቸው የበሳል ድርሰት ኮርሶች ብቻ ናቸው::

በሌላው መልኩ ሌሎች ኮርሶች በቀጥታ ቀዳሚ ትኩረታቸው ጽህፈት አይሁን እንጂ የጽህፈትን ክሂል አይመለከቱም ማለት አይቻልም:: ኮርሶቹ ቋንቋውን ከማሰልጠን አኳያ የተቀረጹ እንደመሆናቸው የጽህፈት ክሂልንም በቋንቋው ክሂልነቱ አያልፉትም:: ቅንጅታዊ በሆነ መልኩ በነዚህ ኮርሶች ይሰጣል:: ነገር ግን የጽህፈት ክሂልን በቀጥታ ከማስተማር አኳያ ሳይሆን በኮርሶቹ የሚቀርቡትን ሌሎች እውቀቶች ለመገንዘብ ከሚደረግ ክዋኔ አኳያ ነው:: እነዚህን ከመሳሰሉት ኮርሶች መሀከል ELAm 405 አንዱ ነው:: ይህ ኮርስ፣ የአፍሪካ ስነጽሁፍን የሚመለከት ሲሆን በትምህርት ክፍሉ እንደሚሰጡት ሌሎች ኮርሶች የማስተማሪያ ቋንቋው አማርኛ ብቻ አይደለም:: ተማሪዎች ለኮርሱ ማሟያ የሚያቀርቡት «ወረቀት» በእንግሊዘኛ እንደሆነ መረጃዎች አግኝተናል:: ይህ ጥናት ደግሞ በአማርኛ የሚከወኑ ጽሁፎችን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ፣ ይህ ኮርስ በዚህ ጥናት አልታቀፈም::

## 1 . 5 የጥናቱ ወሰን

ዛሬ በአማርኛ ቋንቋ የሚጻፉ ጽሑፎች ጥራታቸው ደካማ እየሆነ መምጣቱን፣ ለዚህ መሻሻል በቋንቋው ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሰልጥነው የሚወጡት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው እና እነዚህ ስልጣኞች የሚያበረክቱት ወይም ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው ብሎ ከመመርመር በፊት እራሳቸው ሠልጣኞቹ ያላቸው የመጻፍ ብቃት ምን ያህል ነው ብሎ መጠየቁ ተገቢ መሆኑን ከላይ በ1.1 ስር መረጃዎችን በማጣቀስ መግለጻችን ይታወቃል:: ይህን ጥያቄ በሁሉም ከፍተኛ ተቋማት ማየት ስለማይቻለን አንደኛውን መምረጥ የግድ ይል ነበርና ለዚሁ ተግባር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍልን በዚህ ጥናት ለመመልከት ሞክረን:: ይህን ተቋም የመረጥንበት ምክንያት ቋንቋውን ከሚያሰለጥኑት (በዲግሪና በዲኘሎማ) ተቋማት አንጋፋውና ሠፊው ማሠልጠኛ በመሆኑና በተለይም አጥኚው በቀላሉ መረጃዎችን ለማግኘት ስለሚቻለውና ከብዙው ካሉት ሁኔታዎች ጋር በቅርቡ ከክፍሉ ሠልጥኖ የወጣ በመሆኑ በቅርበት ስለሚተዋወቅ ነው::

ከላይ በ1.1 እና በ1.2 ስር እንደተገለጸው ጥናቱ በአማርኛ ቋንቋ በተለያዩ ኮርሶች ተማሪዎች የሚጽፏቸውን የጽህፈት ስራዎችና ከነዚሁ ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በመመርመር ተማሪዎቹ ያላቸውን የጽሑፍ ክሂል ደረጃ የሚያሳይም ነው:: በአንድ ወገን የጥናቱ አላማ ይህ በመሆኑ ይህን ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ መረጃ እንዲሰጡ የተመረጡት፣ በክፍሉ በቀን ተማሪነት ለመጀመሪያ ዲግሪ አማርኛን በዋናነት (major) የሚያጠኑ ናቸው:: አጠቃላይ መረጃዎቹም (የጽህፈት ስራዎቹ፣ የመምህራኑ አስተያየት) የተሰበሰቡት እነዚህ ተማሪዎች ከሚከውኗቸው ውስጥ ሲሆን መምህራኑም የተጠየቁት እነዚህን ተማሪዎች አስመልክቶ ነው:: ይህ የተደረገው አንደኛ በማታ ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ከቀን ተማሪዎች ይልቅ የተለያየ ዳራ እንዳላቸው በሙከራ ጥናት (pilot study) መረጀ ስላገኘን ነው:: በሌላው መልኩ በመለስተኛነት /minor/ የሚሰለጥኑትን ደግሞ ያላካተተው እነዚህ ተማሪዎች ሁሉንም ኮርሶች ስለማይወስዱ የተሟላ (ትክክለኛ) መረጃ ስለማይሰጡን ነው:: ይህም አንዳንድ መምህራን በሙከራ ጥናቱ አነጋግረን እንዳገኘነው መረጃ ከሆነ፣ በሁለቱ መካከል ከፍተኛ ልዩነት በመኖሩ በአንድ አካቶ መመልከት በዚህ ጥናት የማይቻል ስለሆነ ነው:: ስለዘህም ፣ እነዚህን ተላውጦዎች (variables) ተቆጣጥሮ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ሠፋ ያለ ጊዜና ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ በዚሁ መልክ ሊወሰን (ሊገደብ) ችሏል::

## *1 . 6 በጥናቱ የሕትመት አመትና የእንግሊዘኛ ስሞች አጠቃቀም*

በዚህ ጥናት በዋቢ ጽሑፎች ስር የተዘረዘሩት መጻህፍት ወይም ጽሑፎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፉ ከሆነ በተዛምዶ በዚያው ስር ያለው ዓመት የሚያመለክተው የአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው:: አማርኛ ከሆነ እንደዚሁ የኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ነው:: ከዚህ ውጪ ሌላ አጠቃቀም ካለ እንደ ኤ.አ. እና ዓ.ም በሚሉ ምህጻረ ቃላት የአውሮፖው አቆጣጠርና የኢትዮጵያውያን አቆጣጠር እንደቅደም ተከተላቸው ተመልክተዋል / ተጠቅሰዋል::

በጽሁፉ አካል ውስጥ ያለው የመረጃ ስነዳም (documentation) ይህንኑ የሚያመለክት ነው:: ይህም በዋቢው የእንግሊዝኛው ስም በዚያው በእንግሊዝኛው ፊደል የተገለጸ ከሆነ በጽሁፍ አካል ውስጥ እንደዚያው ይቀርባል:: አማርኛውም በተመሳሰሉ በዚሁ መልክ ይቀርባል:: ይህ የተደረገው አንባቢው በጽሁፉ አካል ውስጥ ያገኘውን ሰነድ (document) ሙሉ መረጃ ፈልጐ ዋቢውን ሲያገላብጥ ሳይቸገር በቀላሉ እንዲያገኝ በማሰብ ነው:: ሌሎች በእንግሊዝኛው ታዋቂ የሆኑ ስያሜዎችና ምህጻሮች በአማርኛው አቻ ስያሜ ያልተገኘላቸው እንዳሉ ቀርበዋል::

## 1 . 7 የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናት አምስት ክፍሎች ወይም ምዕራፎች አሉት:: የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ ስለጥ ምክንያትና ዓላማ ግንዛቤ የሚሰጥ ነው:: ሁለተኛው ለጥናቱ ተዛማጅ የሆኑ ድ ተተንትነው የቀረቡበት ነው:: ሦስተኛው ፣የጥናቱ ንድፍ ወይም የአጠናኑ ዘዴ፣ የ መሰብሰቢያ ቴክኒኮቹን የአሰባሰብ እንዴትነትና የስብስብ መረጃዎቹን አተናተን ስልት በመ ወደ አራተኛው ምዕራፍ የሚያንደረድር ነው:: ምዕራፍ አራት በበኩሉ የስብስብ መረጃዎች ውጤት በመተንተንና ማብራሪያ በማቅረብ በጥናቱ ለተነሱት ነጥቦች መልስ የሚሰጥ ነው: የመጨረሻው ምዕራፍ ከጥናቱ ግኝት በመነሳት ድምዳሜ የሚያቀርብና ከድምዳሜው በማስከተል አስተያየት የሚሰጥ ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ድርሳን ክለሳ

## 2 . 1 ጽሕፈትን ማስተማር

### 2.1.1 ጽሕፈትን የማስተማር ስልተ ትውሮች

ጽሕፈትን በማስተማር ረገድ ያሉ ስልተ ትውሮችን በሁለት ጎራ ጠቅልሎ ማስቀመጥ እንደሚቻል በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ (ለምሳሌ Richards 1990፣ Riames 1983 ወዘተ.ን ይመለከቷል):: እነዚህም ውጤት ተኮር ስልተ ትውር (product-focused approach) እና ሂደት ተኮር ስልተ ትውር (Process-centerd approach) በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ ስልተ ትውሮች በውስጣቸው የተለያዩ ቴክኒኮችን ይይዛሉ:: በሌላ አነጋገር ከአካባቢ አካባቢ ወይም ከመምህር መምህር የሚለያዩ የማስተማር ስልቶችን ያቀርባሉ፤ በሁለት የመከፈላቸው ምስጢር በጋራ ከሚገናኙበት ባህርይ አንጻር መሆኑ ነው::

በዚህ ስራ የሚነሱ ነጥቦችም በስልተ ትውሮቹ የሚነኩ በመሆናቸው፣ በቅድሚያ ሌሎች ጉዳዩችን ከማቅረባችን በፊት የነዚህን ምንነት ማየቱ ተገቢና መሰረታዊ ይመስለናል:: ስለዚህም ቀጥለን እያንዳንዳቸውን በተናጠል እንመለከታለን::

#### 2.1.1.1 ውጤት ተኮር ስልተ ትውር

ይህ ስልተ ትውር ከረጅም ጊዜ አንስቶ ጽህፈትን በማስተማር ረገድ በአፍ መፍቻም ይሁን በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ ሲያገለግል የኖረና በአሁኑም ጊዜ በአንዳንድ አካባቢዎች ለአንዳንድ ልዩ ዓላማዎች በማገልገል ላይ ያለ ነው:: ይህ ስልት ትውር ጥሩ ጸሐፊዎች ጽሑፋቸውን ለማውጣት ካለፉበት ሂደት ይልቅ ጥሩ ወይም የተሻሉ የሚባሉ ድርሰቶችን በሞዴልነት በማቅረብ፣ ተማሪዎች እነዚያን አስመስለው እንዲከውኑ ወይም እንዲጽፉ ያለማምዳል:: ትኩረቱ «ትክክለኛ» ድርሰት ወይም ውጤት ከማግኘት ላይ ነው:: ዋና ዋና መርሆቹና ቴክኒኮቹ እንደሚከተለው ተጠቃለው ሊቀርቡ ይችላሉ፤

- የድርሰት ትምህርት መርሃ-ግብር (program) ግቡ ተማሪዎችን ለትምህርት፣ ለመስሪያ ቤትና ለግል ግልጋሎት የሚረዱ ድርሰቶች ለመጻፍ ማስቻል ነው፡፡ ይህ በገላጭ፣ በስዕላዊና በአመዛዛኝ ድርሰቶች መካከል ያሉ ልዩነቶችን በመጣጥፍ ወይም በሪፖርት መልክ አደራጅቶ ማቅረብ ወዘተ.ን ይመለከታል፡፡
- የድርሰት አጻጻፍ መመሪያዎችንና የሰዋሰው ሕጎችን በተለያዩ ድርሰቶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በማሳየት ተማሪዎቹ በተግባር እየከወኑ እንዲለማመዷቸው ያደርጋል፡፡
- ትክክለኛ የዓረፍተ ነገር መዋቅር መስራት የትምህርቱ አስፈላጊ አካል ነው፡፡ የሰዋሰው ችሎታ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፡፡
- ሞዴሎችን በማቅረብ ተማሪዎች አስመስለው እንዲጻፉና ስህተት እንዳይሰሩ ለማድረግ ይሞክራል፡፡
- የእጅ ጽህፈት፣ አገባብና ስርዓተ ነጥቦች የመሳሰሉ የሜካኒክስ እውቀቶች በትምህርትነት ይሰጣሉ (Richards *1990:30*)፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ስልተ ትውር ቀዳሚ ተግባሩ ድርሰቶችን ማምረት ሲሆን፣ ሁለተኛው ተግባሩ ተማሪዎች ስህተት እንዳይሰሩ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ስልተ ትውር የትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል የተለያዩ ዓረፍተ ነገሮችን በተናጠል ከመመስረት አንስቶ ፣ አንቀጾችን መገንባት፣ ከዚያም የተለያዩ ድርሰቶችን ወደ ማምረት የሚጓዝ ነው፡፡ በጉዞው ሰዋሰዋዊ ሕግጋት፣ የሜካኒክስ እውቀት፣ የአንቀጽ አገነባብ እውቀትና የተለያዩ ድርሰቶች ( አመዛዛኝ፣ ገላጭ ወዘተ.) ዓይነት በትምህርትነት ይሰጣሉ፡፡ አጠቃላይ ልምምዶቹ ሞዴሎችንና የአረፍተ ነገር አመሠራረት ሰዋሰዋዊ ሕግጋትን መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው ይህ ስልተ ትውር በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አንድን ድርሰት ለማምረት ከሚታለፍበት ሂደት ይልቅ በመጨረሻው ውጤት ላይ ነው ትኩረት የሚያደርገው፡፡ ከሂደት ይልቅ ውጤት ላይ ያተኩራል፡፡

### 2.1.1.2 ሂደት ተኮር ስልተ ትውር

ሂደት ተኮር ስልተ ትውር ከመነሻው በእንግሊዝና በአሜሪካ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጽህፈትን ለማስተማር የዋለ ሲሆን፣ ባሁኑ ጊዜ ግን በበርካታ አገሮችና በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ ጽሕፈት ትምህርትም በስፋት የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ ስልት ትውር ተጽፎ ያለቀለትን ስራ

ከመመርመር ይልቅ የተሳካላቸው ደራሲያን እንዴት እንደሚጽፉ ይመረምራል:: በዚህም መሰረት በዚህ ስልተ ትውር ተማሪዎች ሃሳብ እንደመጣላቸው ማስፈርን፣ ያንንም ማደራጀት፣ የመጀመሪያውን ረቂቅ መንደፍና እንዴት መከለስ እንደሚችሉ እንዲያውቁና እንዲለማመዱ ይደረጋል::

ከማናቸውም ነገር በላይ ተማሪዎች የሚፈልጉት ነገር ፣ እንደ Raimes /1983:143/ አባባል፣ የራሳቸውን ስራ በጥያቄና በሒስ አይን ማንበብ የሚያስችላቸውን ክሂል፣ እንዴት አድርገው ማሻሻል፤ ፍስት ባለው መልኩ ፣ በተጠያቂያዊና በአግባቡ ሃሳባቸውን በቀጥታ ማስተላለፍ እንደሚችሉ መማር ነው:: ተማሪዎች ስህተታቸውን ሽተው ማግኘትና በራሳቸው ማስተካከል መቻልን መማር ይፈልጋሉ:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ከውጤት ይልቅ ሂደት ላይ እንዲያተኩሩ ግድ ይላል:: በመሆኑም ይህ ስልተ ትውር ዋናው ትኩረቱ የመጻፍ ሂደትን ከማለማመድ ላይ ነው:: እነዚህን የጽሑፍ ሂደቶች Hedge /1988:2/ እንደሚከተለው ያቀርቡታል፤




ይሁን እንጂ እነዚህን የጽሑፍ ሂደቶች በሦስት ደረጃዎች ማስቀመጥ ይቻላል:: እነዚህም ቅድመ ጽሑፍ (pre-waiting) መጻፍ (on-writing) እና ድህረ-ጽሑፍ (post-writing) ናቸው::

ሀ / ቅድመ ጽሑፍ :- በዚህ ደረጃ በዚህ ስልተ ትውር ተማሪው እንዲያደርግ የሚጠበቀው የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች በማንሳት መልስ መፈለግ ነው:: እነዚህም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ምንድን ነው? እና ለማን ነው ይህን ጽሁፍ የምጽፈው? የሚሉት ናቸው (ዝኒ ከማሁ)::

ለ / መጻፍ :- ይህ ሁለተኛው ደረጃ ( phase ) እራሱ መጻፍ ነው:: ለጥሩ ጸሐፊዎች ይህ ደረጃ የመጀመሪያውን ረቂቅ መንደፍንና ክለሳ ማድረግን ይመለከታል:: ክለሳው የመጀመሪያውን ረቂቅ በማሰስ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ውሳኔ መስጠት ነው:: እነዚህ ነጥቦች :-

- ለማለት የፈለግሁትን ለአንባቢዎቼ በግልጽ አስተላልፌያለሁ?
- የረሳሁት ወይም የዘለልኩት ጠቃሚ መረጃ አለ?
- ቃላቱ ከዚህ በላይ ጠንካራ ሊሆኑ የሚገባበት ቦታ አለ?

- ተመሳሳይ የሆኑ አንዳንድ ዓረፍተ ነገሮች ቢወጡ ያጉድላሉ? ወዘተ. ናቸው (Hedge 1988:22)::

በአጠቃላይ በሁለተኛ ደረጃ የተካተቱት ረቂቅ መንደፍና ክለሳ ናቸው:: ረቂቁ በመጀመሪያው ደረጃ ጸሐፊው ለማለት የፈለገው እንደመጣለት የሚያሰፍርበት ነው:: ከዚሁ በቀጣይ የሚከሰተው ክለሳ ነው:: የክለሳው ትኩረት ለማለት የተፈለገው ነገር በትክክል የሚባልበትን መንገድ ማስተካከል ነው::

መ/ ድሕረ-ጽሑፍ :- ይህ ሦስተኛው ደረጃ አርትኦት በመባልም ይታወቃል:: ድህረ ጽሑፍ በመጨረሻው ረቂቅ ላይ የሚደረገውን የአርትኦት ስራ የሚመለከት ነው:: የጸሐፊው ተግባር እንደተደራሲው / ታላሚው አንባቢ በመሆን ጽሑፉን ማንበብ ነው:: ንባቡ «ግልጽ በሆነ መንገድ አንባቢዎቼ ለማለት የፈለኩትን ሊረዱት ይችላሉ ወይ?» የሚለውን ለመገምገም ነው:: የአርትኦቱ ሂደት የመጨረሻው ማስተካከያ የሚካሄድበትና የመጨረሻው የርቱዕነት (accuracy) ቅርጹን እንዲይዝ የሚደረግበት ነው (ዝኒ ከማሁ: 23)::

በእነዚህ ሦስት የጽሕፈት ደረጃዎች ጥሩ ጸሐፊና ደካማ ጸሐፊ በሚባሉት መካከል ልዩነት እንዳለ በርካታ ጥናቶች አመልክተዋል (Greham, Schwartz & McArthur 1995 ፣ Chenoweth 1987):: ስለሆነም በዚህ ስልተ ትውር አንድ የተማሪ ጸሐፊ ጥሩ ጸሐፊ የሚያልፍባቸውን የአጻጻፍ ደረጃዎችና ሂደቶች እንዲከተልና እንዲለማመድ ይደረጋል:: በሂደት ተኮር ስልተ ትውር ተማሪው በቀጥታ ከአንደኛው ደረጃ ወደ ሦስተኛ እንዲያልፍ ወይም የመጨረሻው ውጤት ላይ ብቻ እንዲያተኩር አይፈቀድለትም:: መምህሩም ለእነዚህ ሂደቶች ትኩረት ሰጥቶ ተማሪው ደረጃ በደረጃ መስራቱን እንዲከታተልና እንዲቆጣጠር፣ ይህ ስልተ ትውር እጅጉን ያስገነዝባል::

በሚጽፉት ድርሰት ላይ ርዕሱን በማብላላት፣ ረቂቅ በመንደፍ፣ ክልሶ በመጻፍና አርትኦት በማድረግ እንደቀደም ተከተሉ ሂደቱን ጠብቆ የመስራት ተግባር ይዘትንና ቅርጽን ያዋደደ ማለፊያ ድርሰት ለመጻፍ ያስችላል ከሚል እምነት የመነጨ ነው:: በዚህ ረገድ የሂደታዊ አጻጻፍ አመለካከት ጽሕፈትን በማስተማር መሰረታዊ ለውጥን እንዳመጣ በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ (ለምሳሌ Olshtain 1991፣ Kroll 1990፣ Kroll 1991፣ Richards 1990 ወዘተ.ን ይመለከቷል):: ለውጦቹም በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችና መምህራን በሚኖራቸው

ሚና እንዲሁም በድርሰት ትምህርት ወቅት በምንጠቀምባቸው ትምህርታዊ ልምዶች ላይ ይታያሉ (Hedge 1988:24)::

በሂደት ተኮር ስልተ ትውር የማስተማር ልምምድ የክፍል ውስጥ ክንውኑን ባሕርይ ከቋንቋ ተኮር ክንውን ወደ ተማሪ ተኮር ክንውን እንደለወጠው ይነገራል:: በዚህ ለውጥም የሚታየው ተማሪዎች ምን መጻፍ እንዳለባቸውና የራሳቸውን የጽሕፈት ስራ ራሳቸው በማረም ተሳትፎ እንዲያደርጉ መጠበቃቸው ነው:: ተማሪዎች በራሳቸው ለድርሰታቸው የሚሆን ዓላማ ማበጀት፣ ርዕስ መምረጥ፣ ተደራሲና ይዘት እንዲፈልጉ ይደረጋል:: የራሳቸውን ድርሰት በማረም ሂደትም እንዲያልፉ፣ በየረቂቅ ጽሁፋቸው ላይ ይህ ስልተ ትውር ያበረታታል:: የጽህፈት ልምምዱም በቡድን ወይም «በወርክ ሾፕ» አማካኝነት እንዲደረግ፣ የቢጤ ቡድን እርማት እንዲከወን ይህ ስልተ ትውር እጅጉን አጽንኦት ያደርግበታል:: ይህም በቡድን ጽህፈትን የሚማሩ ተማሪዎች የሚጽፉበትን ርዕስ በቀላሉ ይመርጣሉ ፤ በኅብረት ወይም በቡድን ከሆኑም ለመጻፍ ይደፋፈራሉ፤ ወዘተ. የሚሉ እምነቶች በመኖራቸው ነው::

በሂደት ተኮር ስልተ ትውር የሚያስተምሩ መምህራን ክፍሉ ጥሩ ወይም ምቹ የመጻፊያ አውድ እንዲሆን ማመቻቸትና ተማሪዎችን ማገዝ እንጂ በመጻፍ ወይም በትምህርቱ ላይ ማዕከላዊ ሚና የላቸውም:: መምህሩ በዚህ ስልተ ትውር ያላቸው ሚና ሁለት ናቸው (Raimes 1983:144) እነዚህም፣ አንደኛ፣ ተማሪዎች በሚሰሯቸው ረቂቆች ላይ ሃሳብ ማመንጨት እንዲችሉና የይዘት ምላሽ (Response ) ማግኘትም እንዲችሉ ጊዜ መስጠትና፣ ሁለተኛ የመጻፍ ሂደት የመፍጠር ሂደት እንዲሆንላቸው ተማሪዎቻቸውን ማገዝ ናቸው::

በአጠቃላይ ውጤት ተኮር ስልተ ትውር ጥሩ የሚባሉ ጽሁፎችን በሞዴልነት በማቅረብ ከስህተት ነጻ የሆኑ ድርሰቶችን እንዲጽፉ ያለማምዳል:: በአንጻሩም ሂደት ተኮር ስልተ ትውር ጥሩ ድርሰቶችን ሳይሆን ጥሩ (የተሻሉ) የተባሉ ደራሲያን አንድን ጽሑፍ ለማምረት የሚያልፉበትን ሂደት በመመርመር በዚያ ሂደት ተማሪዎች እንዲያልፉ ያደርጋል:: ልምምዱ በእያንዳንዳቸው የጽሑፍ ሂደቶች ላይ ጥሩ ጸሐፊ የሚባሉት ያላቸውን ስልት ተማሪውም እንዲኖረው ለማስቻል ነው::

## 2.1.2 በተለያዩ የትምህርት መስኮች ጽሕፈትን ማስተማር

ጽህፈትን ለማስተማር የተሻለ «ስነዘዴ» ለማግኘት፣ በአንድ በኩል ጥረት ሲደረግ በሌላ በኩል «ጽሕፈትን በጥሩ ሁኔታ ማስተማርና መማር የሚቻለው በሁሉም መስኮች ባሉ በፋኩሉቲ አባላት ትብብር ብቻ ነው» (Russel 1992:22) የሚል ሃሳብ አለ:: በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ጽሕፈትን ለማስተማር የተለያዩ ትምህርት መስክ-ምርኩዝ (discipline-based) የሆኑ መርሃ ግብሮችን በመንደፍ የማስተማር አዝማሚያ እንዳለ ይነገራል (ለምሳሌ Spack 1988ን ይመለከቷል):: ለዚህ መነሻ ምክንያቱ በርካታ ቢሆኑም፣ ዋናዎቹ ንቅናቄዎች (movements) ግን በመጀመሪያ ቋንቋ ረገድ «ራይቲንግ አክሮስ ዘ ካሪኩለም፣ በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ ረገድ ደግሞ «ኢንግሊሽ ፎር ስፒስፊክ / አካዳሚክ ፐርፐዝ» ናቸው::

እነዚህ ንቅናቄዎች፣ በአሁኑ ወቅት የጽሕፈት መርሃ ግብሮች በተለያዩ ቦታዎችና አገሮች ሲቀረጹ በጉልህ የሚንጸባረቁ ሆነዋል:: ይህን ስራም ለመገንዘብ የነዚህን ንቅናቄዎች ምንነት በአንጻሩ ማየቱ በይበልጥ ሊረዳ ይችላል:: ከዚህም በላይ፣ ይህ ስራ በአሰራር ሂደቱ ከእነዚህ ንቅናቄዎች የሚጋራቸው ነጥቦች አሉና ቀጥለን እያንዳንዳቸውን በተናጥል ለማየት እንሞክራለን::

### 2.1.2.1 በመጀመሪያ ቋንቋ ጽሕፈት በተለያዩ የትምህርት መስኮች ለማስተማር የተደረገ እንቅስቃሴ

በመጀመሪያ ቋንቋ ጽህፈትን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ለማስተማር የተደረጉ እንቅስቃሴዎች (ንቅናቄዎች) በርካታ ናቸው:: እነኚህን ሁሉ በዚህ ስራ ለመዘርዘር አንሞክርም:: ከዚህም በላይ ብዙዎቹ እንቅስቃሴዎች በዘመን ሂደት በተለያዩ ምርምሮች በመታገዝ እያደጉ ወይም እየተለወጡ «ራይቲንግ አክሮስ ዘ ካሪኩለም » የሚል ስያሜ ይዘዋል:: ይህ እንቅስቃሴ በስፋት የሚታወቅ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውጤት በመሆኑ፣ ምንነቱን ዘርዘር አድርጎ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል::

በትምህርት መስኮች ጽሑፎችን ማስተማር በተለያዩ ወቅቶች ብልጭ ድርግም ሲል የቆየ መሆኑን ገልጸው በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያለውን ይዞታ

ለማሳየት ያለፈበትን እድገት በእንግሊዝና በአሜሪካ Martin (1992) እና Russel (1992) እንደቅደም ተከተላቸው ለማሳየት ሞክረዋል::

ሁለቱ ሰዎች በታሪክ አዘጋገባቸው ላይ የተለያዩ አመለካከቶች ይታዩባቸዋል:: የMartin (1992) ትረካ ለጊዜው አሳማኝ እንደሚመስል Herrington & Moran (1992) ይገልጻሉ:: ምክንያቱም Martin እራሳቸው የእንቅስቃሴው ተካፋይ ስለነበሩ ነው:: እንደ Martin እምነት፣ በትምህርት መስኮች መጻፍ የብሪታኒያ ክስተት ሲሆን፣ ያም በ1960ዎቹ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የተከሰተ ነው:: የSpack (1988 ዓ/ም) ገለጻ ይህንኑ ሃሳብ ይደግፋል:: በዚህ ክስተትና ቦታ ዋናዎቹ ሰዎች Martin እና James Briton የተባሉ ሌሎች ሰዎች ነበሩ:: ለዚህ መነሻቸው ቋንቋና መማር በጣም በቅርብ የተቆራኙ በመሆናቸው አንድ ሰው ቋንቋን ከተቀረው የህይወት እንቅስቃሴ ወይም ከትምህርት ቤት ሊነጥለው አይቻለውም የሚል ነበር:: ይህ ግንዛቤ እንደ Herrington and Moran (1992:3) አባባል ከመምህራን ጋር ተማሪዎች በመተጋገዝ ክፍል-ምርኩዝ (Class Room-based) የሆኑ የምርምር "ፕሮጀክቶች" እንዲዘረጉ አደረገ:: ይህ በቋንቋ ትምህርት መምህራን ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የትምህርት አይነቶችም ነበር::

በሌላው መልኩ፣ ለብዙ ዓመታት ፋኩልቲዎች ከድርሰት ትምህርት ውጭ ባሉ የትምህርት ዓይነቶች ተማሪዎች ጥራት ያለው ወይም ደረጃውን የጠበቀ ጽሁፍ ባለመጻፋቸው ላይ ድክመታቸውን ሲያማርሩ ኖረዋል:: ድክመቱ የመጣው፣ በአንድ በኩል በትምህቱ ረገድ ያለው ደረጃ ዝቅ በማለቱ ሲሆን፣ በሌላው በኩል ደግሞ በ1960ዎቹና 70ዎቹ የተማሪዎች ቁጥር መጨመሩና ተማሪዎች ከተለያዩ ባህሎች የመጡና የተለያዩ ስነትምህርታዊ ዳራዎች ያሏቸው ቅይጥይጥ ከመሆናቸው ነው (ለዚህ ጉዳይ Russel 1992:22 ይመለከቷል):: በከፊል ለዚህ ጉዳይ ምላሽ ለማስገኘት ሲባል WAC* የተባለው እንቅስቃሴ በብሪቲሽ መርሐ ግብር ተነድፎ በ1970ዎቹ በዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች በተግባር ላይ ዋለ (Spack 1988:32):: እንዲሁም Russel (1992:36) እንደሚሉት ከሆነ፣ ለእንቅስቃሴው መነሳት አስተዋጽኦ ያበረከቱት መሰረታዊ የሆኑ ተቋማዊ ፣ ማኀበራዊና ትውርታዊ ለውጦች በ1960ዎቹ ቅርጽ ቢይዙም፣ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ድረስ በዩናይትድ ስቴትስ አልተከሰተም ነበር:: Herrington & Moran (1992:4) ይህን ጉዳይ አስመልክተው ሲገልጹም፣ በ1966 የአሜሪካና የእንግሊዝ የቋንቋ ሊቃውንት እንግሊዝኛን በማስተማር ረገድ ጉባኤ ካካሄዱ በኋላ በትምህርት መስኮች ጽሁፊትን የማስተማር መርሃ ግብሮች በአሜሪካን ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች መነሳት ጀመሩ::

---

* " Writing Acros the carriculum " ለሚለው ምህጻረ-ቃል ነው::
እንዳለ እንግሊዘኛውን የተጠቀምነውን አማርኛ እንዳያሳስት ብለን ነው::

እነዚህ ሰዎች አያይዘው ሲገልጹ በኢንግላንድ እንቅስቃሴው የጀመረው «ላንጉጅ አክሮስ ዘ ካሪኩለም» በሚል መንፈስ ሆኖ ወዲያው እየተለወጠ «ቋንቋና መማር» ወይም «ቋንቋን ለመማር» የሚል ሆኗል:: በዚያም በእንግሊዘኛ ትምህርት ላይ ትልቅ ለውጥ አሳድሯል::ይህም «መናገርና መጻፍ ቋንቋን እንዲያሳድጉ የሚለው ቀርቶ መማርን እንዲያሳድጉ ሆኗል» (ዝኔ ከማሁ:5):: ማለትም በአሜሪካ WAC የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋትና በዚያም ደረጃውን የጠበቀ የጽህፈት ቋንቋ የማስፈለጉ ውጤት መሆኑ ነው:: ዋናው ዓላማው ጽህፈት በመማሪያ ተቋማት ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የነበረውን ማዕከላዊ ሚና ለመመለስ ነው:: በእርግጥ በርካታ የWAC ሞዴሎች አሉ:: ይሁን እንጂ ሁሉም ሞዴሎች የሚጋሩት አንድ ዓይነት ግብ አለ:: ይህም በሁሉም የትምህርት መስኮች ያሉ መምህራን ጽህፈትን በማስተማር መማሩ ሂደት የኮርሶቻቸው አንዱ አካል እንዲያደርጉት ማበረታታቱ ወይም መገፋፋቱ ነው (Spack 1988:34):: የዚህ እንቅስቃሴ «ማዕከላዊ ጭብጡ ፣ ጽህፈት የመማር ልዩ እሴቱ ነው» (Russel በ1992:36) የሚለው ነው:: ይህም በቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሁሉም የትምህርት መስኮች ነው:: ይህ እሳቤም የWAC መርሐ ግብሮች ማዕከላዊ አካዳሚያዊ ሂደት ሆነ (ዝኒ ከማሁ) ::

የWAC እንቅስቃሴ ልክ እንደ አዳጊ ትምህርት ( Progressive education ) ልማድ አካሉ ያደረገውና ለውልደቱም መሰረት የሆነው ኅብረታዊ የትምህርት ስርዓትን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚያሰራጭና ሁሉንም ያካተተ ለማድረግ የሚጥር በመሆኑ ነው፣ ማለትም ይህን ሁናቴ ለመፍጠር የሚጥር ነው:: በሌላው መልኩ በተጓዳኝ በትምህርት መስኮች ስላለው የተሻለ ነገር እርስ በእርስ እንዲማማሩ በማድረግና በትምህርት መስኮች ውስጥ ያሉትን የዕውቀት ልዩነቶች በመገንዘብ ዘመናዊ/ እና ድህረ-ዘመናዊ ኅብረተሰብን (Modern / & post-modern society) ለማምጣት በሚደረገው እርብርቦሽ የበኩልን አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚጥር ነው (Russel 1992:41)::

ለምዕት ዓመታት ያህል ከቀኝና ከግራ ያሉ እንደሚያናፍሱት፣ WAC አንዳንድ ጠምዛዛ ስነ-ትምህርታዊ ፍልስፍናዊ መርሃ ግብሮችን በመፍጠር በነበሩት ላይ ለመተካት የሚጥር አይደለም:: በምትኩ WAC በትምህርት መስኮች መካከል ያለውን ልዩነት ይቀበላል፣ እናም እነኚህን ልዩነቶች ለማጥፋት ወይም ለመለወጥ ሳይሆን ለማገናዘብ ይሞክራል:: በአሁኑ ጊዜ በትምህርት መስኮች መጻፍ ለእንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል ጠቃሚ ነገር እንዳበረከተ፣

ይላሉ Russel (1992:39)። ዛሬ ለትምህርት እድገት ፋኩሊቲዎች በሚያደርጉት ሴሚናር ላይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህራን ከትምህርት ዓይነት መምህራን ጋር በመሆን በኅብረት ይሰባሰባሉ -- የይዘት ኮርሶች መምህራን ስለጽህፈት ብዙ እንዲማሩ በማለት።

ነገር ግን የWAC መርሃግብሮች ሁልጊዜ ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል ማለት አይቻልም (Russel 1987)። በርካታ እክሎች ያጋጥማሉ ፤ ለምሳሌ:- የማስተማር ጫና መጨመር፣ የተማሪ መብዛትና የመሳሰሉት እክሎች ይገኙበታል። በተጨማሪም፣ በሌሎች የትምህርት መስኮች ላሉ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ተጨማሪ ጫና ስለሚያሳድርባቸው የጽህፈት ሂደትን በኮርሶቻቸው ማስተዋወቅን እንዳይቀበሉት ሆነዋል። ከዚህም በላይ ግላዊና አንድምታዊ (personal & interpretive) ባልሆኑ ጽሁፎች ስላለው የመጻፍ ሂደት የግንዛቤ እጥረት አለ (Fulwiter በSpack 1988:35 ውስጥ)።

ይህን ችግር ለማስወገድ በአሁኑ ጊዜ በኮሌጆች የትምህርት እድገትን የሚመለከቱ ሴሚናሮች ሲካሄዱ፣ በብዙ ቦታ የጽህፈት መምህራን ከይዘት ኮርሶች መምህራን ጋራ በአንድነት እንዲሰባሰቡ ያደረጋል፡ ይህ የሚደረገው የጽህፈት መምህራን ስለትምህርት ዓይነት (subject matter) ይማሩ ብቻ ሳይሆን የይዘት መምህራንም ስለጽህፈት ሂደት ይማራሉ ከሚል መንፈስ በመነሳት ነው። በመጻፍና በማቀድ ረገድ መምህራኑ በመተባበር በኮርሶቹ መካከል ትስስር ፈጥረዋል። የቋንቋ ድርሰት መምህራን አጠቃላይ ግባቸው ከነበረው፣ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ማጠናከር፣ ዝርዝር ግብ ወደ ሆነው፣ ተማሪዎች፣ በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያሉትን ወይም የሚሰጡትን የጽህፈት ስራዎች በቀላሉ ሊተገብሩ ወደሚችሉበት ማስልጠን ተቀይሯል። ይህ ግብ በዛሬው ጊዜ በአሜሪካ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በትምህርት መስኮች መካከል የሚያስፈልገውን የጽህፈት ክሂል በማየት በድርሰት ኮርሶች አዲስ መርሐ ግብሮች ተነድፈዋል። የመጀመሪያ ቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት በሌሎች የትምህርት መስኮች ያሉ ጽሑፎችን የሚመለከቱ ክፍለ ትምርህቶችን በመያዝ ተቀርጸዋል። የተለያዩ ጥናቶች በተለያዩ የትምህርት መስኮች ተደርገዋል፤አሁንም በመደረግ ላይ ይገኛሉ (Spack 1988፣ Royster 1992)።

### 2.1.2:2 በሁለተኛ/ ውጪ ቋንቋ ጽህፈትን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ለማስተማር የተደረገ እንቅስቃሴ

የWAC እንቅስቃሴ በመጀመሪያ ቋንቋ የጽህፈት ትምህርት ተሰሚነትን እያገኘ በሄደበት ወቅት፣ በተቀራራቢው ጊዜ በሁለተኛ ቋንቋም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ EAP ወይም ESP በሚል እንደተጀመረ Spack (1988:35) ይገልጻሉ:: ይህ እንቅስቃሴም በአሁኑ ጊዜ በዓለማችን ላይ በስፋት በተለያዩ አገሮች በጽህፈት መርሃ ግብሮች እንደተነደፈ ይነገራል:: ይህ እንቅስቃሴ ትምህርትን ፣ ስልጠናን እና ልምምድን ያካተተ መርሃ ግብር ነው:: በይዘቱም ሦስት የእውቀት መስኮችን(ቋንቋ፣ ስነትምህርት፣ የተሳታፊዎች የስልጠና ፍላጎትን) ያካተተ እንደሆነ Robinson (1990:1) ይገልጻሉ::

በአሁኑ ጊዜ ብዙ ዓይነት ESP ሲኖሩ በተዛምዶው የተለያዩ ምህጻሮችም አሉ:: እነዚህም EOP (English for Ocupational Purpose) ፣ EAP (English for Acadamic Purpose) ፣ EST (English for Science & Technology) እና EEP (English for Educational purpose) የሚሉ ናቸው:: በእነዚህ መካከል መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች ባይኖሩም አንዳንድ አነስተኛ የሆኑ ጥቃቅን ልዩነቶች ይታዩባቸዋል:: እነዚህም በEOP መርሐ ግብር ለምሳሌ የሚቀርበው ከስራ እና ስልጠና ጋር የተያያዘ ክንውን ነው:: EEP እና EAP በተለዋዋጭነት የሚቀርቡ ሆነው ከአካዳሚያዊ ጥናት ጋር የተያያዙ ናቸው:: በEST ደግሞ ብዙ ጊዜ ከስራ እና ጥናት ጋር የተያያዙ ስራዎችን ወይም ፍላጎቶችን ያካትታል:: EST፣ በእርግጥ፣ በአሜሪካ ለESP በተለዋዋጭነት የሚያገለግል ስያሜ ነው (ዝኒ ከማሁ:2)::

Maherን ጠቅሰው Spack (1988:35) እንዳሰፈሩት፣ የ ESP መርሐ ግብሮች የተነሱት ትምህርት ለሕይወት ከሚል መንፈስ ነው:: ESP በቅድሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂን እንደዋንኛ ማተኮሪያ በመውሰድ እነዚህ ተማሪዎች ከትምህርት መስካቸው ጋር የተያያዘ የቋንቋ ትምህርት አዘጋጀ:: በነዚህ ዘርፎች የተተኮረው፣ እኚሁ ምሁር አያይዘው እንደገለጹት ከሆነ፣ በርካታ የአለም አቀፍ ተማሪዎች ስብስብ በመኖሩ ነው:: በዚህን ጊዜ ዋና አላማውም የ2ኛ/ ውጭ ቋንቋ ተማሪዎችን ተግባራዊ ፍላጎት ማሟላት ነው::

በEAP መርሐ ግብር ጽህፈት መካተቱ ከሌሎች፣ የትምህርት መስኮች መምህራን ጋር በመተባበር የመስራትን ጉዳይ እንዳነሳሳ ይነገራል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መርሐ ግብር የሚኖረው ጥንካሬና ድክመት፣ ማለትም ሊያበረክት የሚችለው አስተዋጽኦና የሚኖረው ድክመት በአንጻሩ ሊስተዋል እንደሚገባ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በተለይ እነዚህ መርሐ ግብሮች፣ ተማሪዎች የሚያጋጥሟቸውን የጽህፈት ስራዎች ለመከወን በማዘጋጀት ያላቸው አቅም፣ ለግምገማ መተው ይገባዋል(Shih 1986:640)፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ሁለት መርሐግብሮች (EAP & WAC) የቋንቋ ክሂል መምህራን በትምህርታቸው ከክሂል ውጭም ሌሎች ይዘቶችን እንዲያስተምሩ ያደርጋሉ፣ በዚህም ምክንያት በነዚህ መርሐ ግብሮች ላይ የተለያዩ ወቀሳዎች ከተለያዩ ቦታዎች ሲሰነዘሩባቸው ይታያል፡፡ ለምሳሌ፣ ሌሎች ይዘቶችን አምጥቶ የቋንቋ መምህራን እንዲያስተምሩ ማድረግ አዳጋች ነው፤ ይህም «መምህራን በቂ ዕውቀት ያላከበቱባቸውን የትምህርት ዓይነቶች በክፍል ውስጥ ማስተማራቸው ከፍተኛ ችግር ይፈጥራል» (Spack 1988:36)፡፡ በሌላው መልኩ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በራሳቸው መርሃ ግብሮች የተለያዩ ጥንካሬና ድክመቶች ቢታዩባቸውም፣ በአሁኑ ጊዜ በትምህርት ዓይነት መምህራን መካከል ትብብር በመፍጠር ጽሕፈትን ለማስተማር ለሚታየው አዝማሚያ ጉልህ ድርሻ እንዳበረከቱ ይነገራል፡፡

## *2.2 በትምህርት መስኮች የሚከወኑ የጽህፈት ስራዎችን የማጥናት አስፈላጊነት*

በተለይ ከ1970ዎቹ ወዲህ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ ጽህፈትን በማስተማር መርሐግብሮች የተለያዩ ስልተ ትውሮች ተሞክረዋል፣ እናም በጣም ተስማሚ ወይም ትክክለኛ ስልተ ትውርን ለመጠቀም ትኩረት በመስጠት፣ በርካታ ክርክሮች ተካሂደዋል (Horwitz $1986_a$ ፣ Horwitz $1986_b$ ፣ Horwitz $1986_d$ ፣ Leibman-Kleine 1986፣ Hamp-Lyons 1986 ይመለከቷል)፡፡ ክርክሩ አንድን ስልተ ትውር ከመንቀፍና ሌላን ከመደገፍ አንጻር የተካሄደ ቢሆንም፣ የመጀመሪያም ሆኑ የሁለተኛ/ውጭ ቋንቋ የጽህፈት አስተማሪዎችና ተመራማሪዎች ባአጠቃላይ የተስማሙበት ነገር አለ፡፡ ይህም፣ በኮሌጅ ደረጃ የጽህፈት መርሐ ግብሮች ግብ፣ ተማሪዎች የተሻሉ የትምህርት ዓለም ጸሐፊዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው(ለዚህ Spack 1988፣ Herrington & Moran 1992ን ይመለከቷል)፡፡

ይሁን እንጂ፣ የዚህ አላማ ግብ መምታት ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ውስብስብ ሆኗል:: አንደኛው፣ በርካታ ቅኝቶች ወይም አሰሳዎች ቢካሄዱም፣ የአካዳሚያዊ ጽሁፎችን ምንነት መግለጽ ባለመቻሉ ነው:: ሌላኛው፣ ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ማኅበረሰብ ይዘው በሚመጡትና የትምህርቱ ማኅበረሰብ ከነሱ ለማግኘት በሚጠብቀው መካከል ሰፊ ልዩነት በመኖሩ ነው (ሥበሶሻቅ 1988:30)::

እኚሁ ሰው Bizell'ን ጠቅሰው እንዳሰፈሩት ከሆነ፣ በመጀመሪያ ቋንቋ ረገድ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥሩ ጸሐፊዎች የነበሩ በቀጣዩ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት አካዳሚያዊ ጽሁፎችን ለመከወን የሚሳናቸው አሉ:: እንደነዚህ አይነት ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ አግኝተው ቀጣዩ የትምህርት አለም ሳይሳካላቸው ይቀራል:: ለዚህ ምክንያቱ፣ ተማሪዎቹ ያሏቸው ማኅበራዊ ሁኔታዎችና ቀድመው የወሰዷቸው ስልጠናዎች በትምህርቱ አለም ጥሩ ውጤት እንዳያገኙ ተጽዕኖ ስለሚያሳድሩባቸው ነው:: ይህ ሁናቴ፣ በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከዚህ የበለጠ ሊሰፉ ይችላል:: ማለትም፣ በመጀመሪያ ቋንቋቸው ከፍተኛ ትምህርት ካገኙ በኋላ ተጨማሪ ትምህርትን በአዲስ ወይም በሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩ ተማሪዎች ችግሩ ከዚህ የበለጠ ሊጎላ ይችላል:: የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ስነልሳናዊና ባህላዊ ዕውቀት እጥረት በትምህርት አለም ጥሩ ውጤት ማግኘታቸው ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል (Spack 1988:30)::

በኮሌጅ ደረጃ፣ መሰረታዊ ጸሐፊዎችንም ይሁን ምሁር ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያስተምር የጽህፈት መምህር ክፍተቱን ለማጥበብ መንገድ መፈለግ ግዴታው ነው:: ተማሪዎች ቋንቋውንና የዩኒቨርስቲውን ባሕል ጠንቅቀው እንዲያውቁ መርዳት ይኖርበታል:: የዩኒቨርስቲው የጽህፈት መምህሩም ሚና ተማሪዎችን ወደ አካዳሚያዊ ዲስኩር ማህበረሰብ (discourse community) እንዲገቡ ማነሳሳት ነው ( ዝኒ ከማሁ)::

ይህን ሚና ለመወጣት ፣ የድርሰት ኮርሶቹ ወደታላሚው አካዳሚያዊ ዲስኩር ማኅበረሰብ ለማስገባት የሚችሉ ሆነው መነደፍ ይገባቸዋል:: ከዚህም በላይ አጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት፣ ክንውንና ልምምድ ለዚህ አላማ ግብ መምታት የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክትና ወደዚያው ግብ የሚያመራ መሆን ይኖርበታል:: ይህ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ በቅድሚያ በዲስኩሩ ማኅበረሰብ የሚከወኑ አካዳሚያዊ ጽሑፎች ሲታወቁ ሲሆን፣ በዝርዝር፣ ግን በተዛምዶ የተማሪዎች ዳራና የጽሁፍ ክሂላቸው ደረጃ፣ በድርሰት ኮርሶች የሚሰጡ ልምምዶች እና/ ወይም ስልጠናዎች ወዘተ. ሲታወቁ ነው::

ስለዚህም፣ ጥቅል በሆነ መልኩ እንናገር ካልን፣ በትምህርት መስክ የሚከወኑ የጽሕፈት ስራዎችን ማጥናት፣ በወቅቱ በመስኩ ያሉ ተማሪዎች እየከወኑ ባሏቸው የጽህፈት ስራዎች ያሉባቸውን ችግሮች ያስገነዝባል:: ይህም የመስኩ መምህራን ያን ችግር ሊያቃልሉ የሚችሉበትን መንገድ ለመጠቆም ይችላል:: ከዚህም በላይ ወደዚያ የትምህርት መስክ የሚገቡ ተማሪዎችን ለሚያስለጥን የድርሰት መምህር የትኞቹን የጽህፈት ዓይነቶችና ክሂሎች እንዴት ማለማመድ እንደሚገባው (የትኞቹ የጽሁፍ ዓይነቶችና ንዑሳን ክሂሎች እንደጠቀሟቸውና እንደጎደሏቸው ማስተያየት ስለሚቻላቸው) ያሳየዋል:: በምን መልክ በማረም እርማት አጋዥ ሊሆን እንደሚችልም ይጠቁማል:: ባጠቃላይ ጽህፈትን በተሻለ ዘዴ ለማስተማር ይቻል ዘንድ፣ ቅድመ ግንዛቤ ለማግኘት አስፈላጊ ይሆናል:: የዚህን እውነትነት የበለጠ የሚያጎላው፣ የጽህፈት ዓይነቶች በርካታ በመሆናቸው፣ ሁሉንም በድርሰት ኮርስ ማስተማር ስለማይቻል ነው:: በዚህም ምክንያት፣ በዘፈቀደ ሳይሆን፣ ከዓይነቶቹ ለአውዱና ለታላሚው ግብ ተስማሚ የሆኑትን በዕቅድ መምረጥ ተገቢ ይሆናል:: ሌላው፣ ድርሰትን ለማስተማር የተሻለ ስልተ ትውር ከአለም አቀፋዊ ትውር የሚመነጭ ሳይሆን እንደ ጽህፈት ዓይነቶቹ፣ የተማሪዎች ዳራና የወቅቱ ችሎታን ከመገንዘብ የሚመነጭ ነው (ለዚህ ጉዳይ Torane & Yule 1989፣ Richards 1990ን ይመለከቷል):: ከዚህም በላይ፣ ተማሪዎቹ ለድርሰቶቻቸው ከመምህራቸው የሚያገኙት ምላሽ ለዘላቂ የመጻፍ ክሂላቸው መዳበር የሚያግዝ እንዲሆን ካስፈለገ መቼ፣ እንዴት እና ምን ላይ አስተያየት ቢሰጣቸው ይሻላል? የሚለው መታየት ይገባዋል:: ይህን ጥያቄ ለመመለስም ተማሪዎቹ በሌሎች ኮርሶች በሚከውኗቸው ጽሁፎች ላይ መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን አስተያየት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል::

እነዚህ ነጥቦች ለረጅም ጊዜ የበርካታ ምሁራንን ትኩረት በመሳብ ለጥናት መሰረት የሆኑና በርካታ ክርክሮችን ያስነሱ ናቸው:: ስለዚህም በነዚህ ነጥቦች ( የጽህፈት አይነቶች ለጽህፈት የተሻለ ማስተማሪያ ዘዴ፣ ለድርሰት የመምህራን ምላሽ) ላይ የቀረቡ ሃሳቦችን ድርሳናትን በማገላበጥ ቀጥለን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን:: ይህን የምናደርገው ባጠቃላይ ስለድርሰት ትምህርት እንዴትነት፣ በተለይም የዚህ ዓይነቱ ስራ ለምን እንደሚያስፈልግ በግልጽ ሊያሳዩ ስለሚችሉ ነው::

### *2.2.1 የጽሕፈት ዓይነቶች*

ጽህፈት ዝም ብሎ የንግግር ግልባጭ ወይም ቅጅ እንዳልሆነ ለመናገር ዋቢ መጥቀስ የሚያስፈልግ አይመስለንም:: ይህንንም ለማለት ከጠባብ ስነልሳናዊ አተያይ በመነሳት፣ ጽህፈት እንዴት የንግግር ግልባጭ እንዳልሆነ ምክንያት መደርደር ይቻለናልና ነው:: ሆኖም፣ ቋንቋ በማኅበራዊ መግባቢያነቱ ከታየ ይህን ማለቱ ምንም ትርጉም አይኖረውም:: ምክንያቱም ጽህፈት አይነቱ «ውሱንና » የተማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መግባቢያ በመሆኑ ነው:: እናም፣ «መጻፍን መማር ያንን ማኅበራዊ ባህርይ መማር ማለት ነው» ( Davies & Widdowson 1974:178)::

ይህ ከሆነ፣ ጽህፈት ምን ዓይነት ማኅበራዊ መግባቢያ ነው? የሚለውን መጠየቅ ይገባል:: በመጀመሪያ ደረጃ መታወቅ ያለበት በጣም ውሱን መግባቢያ መሆኑን ነው:: ብዙው የኅብረተሰብ ክፍል ምንም ዓይነት በጽህፈት መግባባት አያደርግም፣ ወይም በጣም ትንሽ መግባባትን ነው የሚያደርገው:: በጽህፈት መግባባት የሚያደርጉ ውሱን የኅብረተሰብ ክፍሎችም በሁለት መልክ ሊታዩ ይችላሉ:: እነዚህም ሙያዊ ግዴታ ያለባቸውና ሙያዊ ግዴታ የሌለባቸው ናቸው:: ሙያዊ ግዴታ ኑሮባቸው በሚጽፉ ሰዎች ጽህፈት መደበኛ (የዘወትር) ተቋማዊ መግባቢያ ሲሆን፣ ሙያዊ ግዴታ በሌለባቸው ሰዎች ዘንድ ደግሞ አንዳንድ ጊዜ የሚያገለግል ግላዊ መግባቢያ ነው:: ሙያዊ ሰዎች የሚጽፉበት ምክንያት የስራቸው አንደኛው አካል በመሆኑ፣ ይህን እንዲያደርጉ ሙያቸው ስለሚያስገድዳቸው ነው:: እነዚህ ሰዎች በሙያቸው ውስጥ ባለው ተለምዶአዊ ስምምነት ላይ በመመርኮዝ ይጽፋሉ:: በአንጻሩም ሙያዊ ግዴታ የሌለባቸው ሰዎች የሚጽፉት በተቋማዊ ስምምነት ላይ በተመሰረተ መርህ ባለመሆኑ በራስ አነሳሽነት በግል የሚከወን ነው:: ከነዚህ ማኅበራዊ ተግባራቱ በመነሳት Davies and Widdowson (1974) የጽህፈት ዓይነቶችን ተቋማዊ ጽሁፍ እና ግላዊ ጽሁፍ በማለት በሁለት ጎራ ይመድቧቸዋል::

ግላዊ ጽሁፎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: እነዚህም ግላዊ ደብዳቤዎችና የፈጠራ ስራዎች ናቸው:: ግላዊ ጽሁፎች በጣም በስሜት ላይ ያተኩራሉ፤ በተጠየቅ (Logic) ላይ ትኩረታቸው ትንሽ ነው:: ግላዊ ጽሁፎች በአብዛኛው እንደዚህ መሆን አለባቸው ተብለው የሚቀመጡ አይደሉም:: ምክንያቱም በተቀባዩና በጻፊው መካከል ባለው የግንኙነት መጠንና ዓይነት ላይ ስለሚመሰረቱ ነው:: በተቃርኖው፣ ተቋማዊ ጽሁፎች፣ በጻፊውና በተቀባዩ መካከል የፈለገው አይነት ግንኙነት

ይኑር፣ እንደሚጻፈው ጽሁፍ ዓላማና ዓይነት ስለሚወሰን፣ በምን ዓይነት መልክ እንደሚቀመር በተቋሙ ስምምነት ይኖራል ( White 1989:14 )::

ተቋማዊ ጽሁፎችን የሚከውኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣ «ጠበቆች፣ ጋዜጠኞች፣ ምሁራን፣ የንግድ ሰዎችና የኅብረተሰብ አገልጋዩች» ናቸው ይሉናል Davies & Widdowson (1974:178):: ሆኖም White (1989:15) ተማሪዎችም ከነዚሁ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጎራ ይመደባሉ ይሉናል:: እኚሁ ሰው አያይዘው ሲገልጹም፣ ከተቋማዊ የጽሁፍ ዓይነቶች የሚመደቡት የማስተማሪያ መጻህፍት፣ የሕጎች መጻህፍት እና /ወይም ጽሑፎች፣ ሪፖርቶች፣ የጥናት ወረቀቶች፣ የንግድ ጽሁፎች ወዘተ. ይገኙበታል ይላሉ:: እነዚህ ጽሁፎች በነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በጣም (በመደበኛነት) የሚዘወተሩ በመሆናቸው በርካታ ዓይነት ማግኘት ይቻላል::
ይህን እውነታ በመገንዘብ የጽሁፍ ዓይነቶችን ለማወቅ በተለያዩ የትምህርት መስኮች በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል (ለምሳሌ ያህል Kroll 1979፣ Johns 1981፣ Horwitz 1986ₑ Browne ፣ 1989 ወዘተ.ን መጥቀስ ይቻላል):: ከጥናቶቹና ከራሳቸው ግንዛቤ ወይም ገጠመኝና ስራ በመነሳት Shih (1986) እና Kusel (1992) የጽህፈትስራዎች በርካታ እንደሆኑና ዓይነታቸውም በሁለት የተለያዩ የትምህርት መስኮች እንዲሁም በአንድ የትምህርት መስክ ውስጥ ባሉ የትምህርት ዓይነቶች መካከልም እንደሚለያዩ ይገልጻሉ::

በመሆኑም የጽሁፍ ዓይነቶች እነዚህ ናቸው ብሎ ተቋሙን ወይም የትምህርት መስኩን በማየት ለማስቀመጥ ለተመራማሪዎችና ለመምህራን ቀላል ስራ አልሆነም:: ይህን ለማድረግ በየአንዳንዱ የትምህርት መስክና የትምህርት ዓይነት የሚከወኑትን የጽህፈት ስራዎች መመርመሩ የግድ ሆኗል::

### *2.2.2 ጽህፈትን ለማስተማር የተሻለ « ዘዴ »*

የመጀመሪያ ቋንቋና ሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ስነዘዴዎች በአሁኑ ጊዜ በቁጥር ከ16 በላይ እንደሆኑ በርካታ ድርሳናት ያሳያሉ (በመጀመሪያ ቋንቋ ረገድ Haliday & MacIntosh 1964፣ ተስፋዬ 1981፣ በሁለተኛ ቋንቋ ረገድ Stern 1983፣Richards & Rodgers 1986፣ Larsen Freeman 1986፣ Hutchinson & Waters 1987 ፣ O'Connell 1982፣ McArther 1984ን ይመለከቷል):: ይህ ቢሆንም፣ ለሁሉም አውድ ተስማሚ የሚሆን አንድ ስነዘዴ ግን ማግኘት

አልተቻለም። በተግባር በክፍል ውስጥ የሚታየው ቅይጥ ስልተ ትውርን መጠቀም ነው። ይህ ስልተ ትውር ከሁሉም የተሻለ ነው ይባላል።

ቅይጥ ስልተ ትውር በእርግጥ በአንድ ስነዘዴ ላይ የተመሰረተ ወይም በእራሱ እንዳንድ ስነዘዴ የሚታይ ሳይሆን ለተማሪው፣ ለመምህሩና ለትምህርቱ ከመማር ማስተማር አውዱ ጋር ተስማሚ የሚሆነውን ከተለያዩ ስነዘዴዎች እየመረጠ በመውሰድ የሚያቀርብና እንደየአካባቢው አካባቢያዊ ተላውጦዎችን (variables) ሊያካትት በሚችል መልኩ የሚለጠጥ ነው። መረጣው የሚደረገው በተለይ፣ በቅድሚያ የተማሪዎች ፍላጎቶች ከተለዩና ከታወቁ በኋላ ነው። እነዚህን ፍላጎቶች ለመለየት ዘዴው በቅድሚያ የሚመነጨው ከአለም አቀፋዊ ትውርቶች (Global Theories) ሳይሆን አካባቢያዊ ከሆነው የመምህራኑ የክፍል ሁኔታን ከማጥናት ነው። ምክንያቱም ይህ በብዙ ተላውጦዎች ተጽዕኖ ስለሚያርፍበት ነው (Torane & Yule *1989:11*)።

ይህ ቅይጥ ስልተ ትውር «አካባቢያዊ መፍትሔ ለአካባቢያዊ ችግሮች የሚል ፍልስፍና ይዟል» (ዝኒ ከማሁ)። ይህ የሚያሳየን ማናቸውም ለትምህርት የሚቀርብ ነገርና የመማር ማስተማር ሂደት የተሻለ ተብሎ ተቀምሮ በቀረበ ቴክኒክ ወይም ቁስ (material) ላይ የሚመሰረት ሳይሆን፣ ከዚያው ከመማር ማስተማሩ አውድ ፈልቆ፣ ለአውዱና ለተማሪው ተስማሚ የሚሆነውን ከመጠቀም ላይ መሆኑን ነው። ይህ በተማሪው ፍላጎት ላይ የማተኮርና አካባቢያዊ ተላውጦዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መጠቀም ባጠቃላይ በቋንቋ ትምህርት ብቻ ሳይሆን በጽህፈት ትምህርት ውስጥም በአሁኑ ጊዜ የሚታይ አዝማሚያ ነው።

ጽህፈትን ለማስተማር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአፍ መፍቻም ይሁን በሁለተኛ /ውጭ ቋንቋ በከፍተኛ ደረጃ ከውጤት ተኮር ስልተ ትውር ይልቅ ተሰሚነትና ተቀባይነት አግኝቶ ያለው ሂደት ተኮር ስልተ ትውር ሲሆን ለሁሉም አውድ ተስማሚ ሆኖ አልተገኘም። ለምሳሌ ይህ ስልተ ትውር ሃተታዊ ፈተናዎችን ለመከወን የሚያስችል ክሂል አያስጨብጥም፣ አካዳሚያዊ ጽሁፎችን በትምህርት መስክ መምህራን ዘንድ እንዴት እንደሚገመገሙ ስለማያሳይ ለተማሪዎች የተሳሳተ መረጃ ይሰጣል ፤ ወዘተ. የሚሉ ወቀሳዎች ይሰነዘሩበታል ( የዚህን ስልተ ትውር ድክመቶች አስመልክቶ ሰፋ ላለ ግንዛቤ Horwitz *1986*$_c$ን ይመለከቷል)።

ስለዚህም በድርሰት ትምህርትም ቢሆን ጽህፈትን በዚህ ስልተ ትውር፣ በዚህ መልክ ይማሩ ማለቱ በቅድሚያ በዚያ ወቅት ወይም ባሉበት የትምህርት መስክ ምን ዓይነት የጽህፈት ስራዎች ይከወናሉ በማለት የአከዋወናቸውን እንዴትነትና አጠቃለይ የየስራዎቹን ዓላማ ወዘተ.

በማየት የሚወሰን ይሆናል። ማለትም እያንዳንዱ የጽህፈት መርሃ ግብር በራሱ ከአላማው፣ ከታላሚው ተማሪ ፍላጎት እና ችሎታ አንጻር መጠናት ይገባዋል።

ባጠቃላይ፣ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው፣ በቋንቋ ብሎም በጽህፈት ትምህርት የተሻለ ወይም ምርጥ የተባለ ስልተ ትውር ከአካባቢው ጋር የሚስማማውን መርጦ ከመጠቀም ላይ የሚያርፍ እንጂ በስነዘዴ ደረጃ ተቀንብቦ ከቀረበ አለምአቀፋዊ ትውር ላይ የሚመጣ አይደለም።

## 2.2.3 ለተማሪ ጽሑፎች የመምህራን ምላሽ

የተማሪን ድርሰት እንዴት አድርጎ በተሻለ መንገድ ማረም ይቻላል? የሚለው ጥያቄ ሰዎች የተሻለ ለመጻፍ ይበልጥ በቀላሉ የሚማሩበትን አውድ እንዴት መፍጠር ይቻላል? የሚለው ሰፊ ጥያቄ አንዱ አካል ነው (Leki 1990:58፣ Hedge 1988:149)። በመሆኑም በርካታ ጥናቶች በእርማት ላይ ተካሂደዋል።

ጥናቶቹ እንዳመለከቱት ከሆነ፣ እርማቶች ሁልጊዜ ጠቃሚ ሆነው አልተገኙም። ይህም መምህራን ለድርሰቶች የሚሰጡት ምላሽ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አለመጣጣም ብቻ ሳይሆን ይዘትን ወደ ጎን በመተው በቅርጽ ላይ (ለምሳሌ ሜካኒክስ፣ ሰዋሰው)የሚያተኩር ነው (Cohen 1987፣ Cohen & Cavalcanti 1990፣ Getnet፣ 1993፣ Zamel 1985)። በሌላው መልኩ ከድርሰት ኮርሶች ውጭ ተማሪዎች የሚከውኗቸው ጽሁፎች ላይ የመምህራኑን ምላሽ ያጠኑ ደግሞ ከቅርጽ ይልቅ በይዘት ላይ እንደሚያተኩሩ ይገልጻሉ። ከዚህም በላይ በነዚህ ኮርሶች መካከል ልዩነት እንዳለ፣ ልዩነቱም በትምህርት መስኮች መካከል ብቻ ሳይሆን በትምህርት ዓይነቶችም መካከል እንደሆነ ይገልጻሉ (Odel 1992፣ Longer 1992)።

እርማት ጠቃሚ የሚሆነው ደግሞ ተማሪዎች ከተለያዩ መምህራን የሚያገኙት ግራ አጋቢና ፍጹም የተለያየ ካልሆነ ነው። በእርግጥ እንደጽሁፉ አይነት፣ አላማና ባህሪይ የተለያዩ ነጥቦች ላይ ማተኮር ይቻላል። ይህ ግን እንደ ልዩነት የሚቆጠር አይደለም። እንደልዩነት የሚቆጠረው በተመሳሳይ አውድ ፍጹም የተለያየ አስተራረም መጠቀሙ ነው። እርማት ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ የሚችለው በተጨማሪም ፣ተማሪው በማናቸውም አውድ ጽሁፉን ሲከውን በማሻሻልና በክለሳ ሂደት ላይ ሊያግዘው የሚችል ሲሆን ነው። ይህ እንዲሆን ተመሳሳይ የማርክ አሰጣጥ ስነዘዴ በየተቋማቱ መኖር አለበት (Hedge 1988:149)።

ስለዚህም፣ ለብዙ የጽህፈት መምህራን የተማሪዎቻቸውን ድርሰቶች መገምገም ብቻ ሳይሆን እንዴት መገምገም እንደሚገባ መግለጽ ይገባል (Leki 1990:58)፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች ወረቀት መምህራኑ የሚሰጡት ምላሽ ተማሪዎች የጽሑፍ ስራቸው ምን ያህል እንደተዋጣላቸው ያስገነዝባቸዋል፣ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ከስነልሳናዊ ቅርጽ ወይም ፍቺ ላይ እንዲያተኩሩ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል (Brumfit 1990:90፣ Ferries 1995:47)፡፡ ስለዚህ እርማት በተማሪው ድርሰት ላይ እና ተማሪው ለጽሑፍ ባለው ዝንባሌ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል __ ይህ ታላቅ ተጽዕኖ፣ ያ ጸሐፊው ያገኘው አስተያየት፣ ምናልባት መጻፉን እንዲቀጥል ወይም እንዲያቆም ሊያደርገው ይችላል (Leki 1990:58)፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች በድርሰት ትምህርታቸው የተሻሉ ጸሐፊዎች እንዲሆኑ በእርማት አሰጣጥ በኩልም መታገዝ ይገባቸዋል ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን እገዛ ለማድረግ፣ መሻሻልን ወይም እድገትን በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይ ሊያመጣ የሚችለው ምንን በመያዝ ምን አይነት አስተያየት በመስጠት ነው የሚለው ለተመራማሪዎች ቀላል ስራ አይደለም (ዝኒ ከማሁ)፡፡ ይህ በመሆኑም በርካታ ጥናቶች በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ላይ ቢካሄዱም፣ በቀላሉ መልሱን ለማግኘት ባለመቻሉ፣ ባሁኑም ጊዜ ጥናቱ ቀጥሏል (Reid 1994) ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በርካታ ቢሆንም፣ ዋናው ቁም ነገር ግን፣ በአንዱ ይህ ይሻላል ተብሎ የቀረበው በሌላው አውድ መስራት አለመቻሉ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶችና የጥናቶችም ቀጣይነት የሚያሳዩን ለሁሉም አውድ ተስማሚ የሚሆን እርማት ማግኘት አለመቻሉን ነው፡፡

እርማት ለመምህራኑ የሚያስደስትና ቀላል (ለስራ የማይከብድ)፣ ለተማሪው ደግሞ ጠቃሚ እንዲሆን ካስፈለገ የድርሰት መምህራን ተማሪዎቻቸው በሌሎች ኮርሶች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ላይ መምህራኑ የሚሰጧቸውን እርማት ማስተዋል ይገባቸዋል ይላሉ Odel (1992:96)፡፡

ከላይ በየርዕሶቹ ለማየት እንደሞከርነው በየትምህርት መስኮቹ ያሉትን ጽሑፎች ማጥናቱ ለበርካታ ምክንያቶች አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ Bazerman (1992) ትኩረት ሰጥተው ተመልክተውታል፡፡ እንደ እሳቸውም አባባል፣ አካዳሚያዊ ጽሑፎችን ማጥናቱ በየትምህርት መስኮቹ እና /ወይም በየትምህርት ዓይነቶቹ መካከል ያሉትን ልዩነቶችና አንድነቶች ሊያሳየን ይችላል፡፡ ይሁም ፣ ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራን የሚኖራቸውን ውስብስብ ተሳትፎ በየትምህርት መስኩ በግልጽ ያሳየናል፤ በነዚያ

ውስጥ ያለው ዲስኩር ህያው እንዲሆን የሚጠቀሙበትን ቋንቋ ከመርሃ ግብሮቹ ዓላማ አንጻር ያሳውቀናል፤ የተለያዩ የጽሕፈት ስራዎች በየትኛው አውድ ለምን እና እንዴት ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆኑ በተጨማሪ ያሳውቀናል (Bazerman 1992:64)::

## 2.3 በሐገራችን የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተደረጉ ስራዎች

### 2.3.1 በአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተደረጉ ስራዎች

በአሁኑ ጊዜ በአማርኛ በርካታ የተለያዩ ይዘትና ዓላማ ያላቸው መጻህፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች ወዘተ. ይታተማሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህ በሕትመት ደረጃ «አለቀላቸው» ተብለው ለንብረተሰቡ የሚሰራጩት ጽሑፎች በርካታ ስህተቶች ይታዩባቸዋል:: ይህን አስመልክተው ተስፋዬ እንዲህ ይላሉ፣ «... ዛሬ በጋዜጦች፣ በመጽሔቶችና በመጻህፍት ላይ የሰፈሩ ጽሁፎችን ብንመረምር ጉልህ የሆኑ ስህተቶች የምናገኝባቸው ብዙ ናቸው» (1986:10):: እነዚህ ስህተቶች ከላይ በተገለጹት ላይ ብቻ የሚታዩ ሳይሆኑ በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጽሑፎች፣ ከዚያም በታች ባለ ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ጽሑፎች ላይ ያሉ መሆናቸውን አምሳሉና ደምሴ (1982:7) ይገልጻሉ::

የስህተቶቹን አይነትና ምንጭ ለማወቅም በተለያዩ ወቅቶች ጥናቶች ተደርገዋል:: ነጋሳ (1965) ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ በሚወስዱት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ ስህተቶችን ለመተንተን ሞክሯል:: (ለጥናቱ መረጃ የሆነው የ1962 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ነው::)

ነጋሳ በዚህ ጥናቱ በተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ በርካታ ስህተቶች እንዳሉ አሳይቷል:: ይህ ጸሐፊ ስህተቶቹን ከዘረዘረ በኋላ፣ ስህተቶቹ የሚበዙት አማርኛ አፍ መፍቻቸው ያልሆኑ ተማሪዎች በሚከውኗቸው ድርሰቶች ውስጥ እንደሆነ ይናገራል:: እንደሱ እምነት ለብዙዎቹ ስህተቶች መከሰት ምክንያት የሆነው አፍ የፈቱበት ቋንቋ ተጽዕኖ ነው::

ይሁን እንጂ፣ ከሱ በኋላ በቅርብ ጊዜ የወጣ ስራ (አምሳሉና ደምሴ 1982 ይመለከቷል)፣ ለስህተቶቹ ዋና ምክንያት የመጀመሪያ ቋንቋ ተጽዕኖ አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው በሆኑት ላይ ስለሚያርፍ አለመሆኑን ይገልጻል:: በርግጥ ይህ ስራ በቀጥታ በአማርኛ አፍ የፈቱና ያልፈቱ ሰዎች የሚሰሯቸውን ስህተቶች ዓይነትና የትኞቹ ተናጋሪዎች በርካታ ስህተቶች እንደሚፈጽሙ

ባይገልጽም፣ በርካታ የስህተት ዓይነቶችን ሲዘረዝር፣ አብዛኞቹ ስህተቶች የተለቀሙት (የተገኙት) ከ2ኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጽሁፎች ውስጥ ሳይሆን የመጀመሪያ ቋንቋቸው የሆኑት ከሚከውኗቸው ጽሁፎች ውስጥ እንደሆነ ይገልጻል(ገጽ:7)::

አለማየሁ(1986) በሁለተኛ ደረጃ፣ በተለይም በዘጠነኛ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩትን (የሚፈጸሙትን) ስህተቶችና የስህተቶቹን ምንጭ ለሁለተኛ ዲግሪው ማሟያ ጽሑፍ ባቀረበው ጥናት ለመተንተን ሞክሯል::

በዚህ ስራው አለማየሁ፣ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ አምስት ዋና ዋና ስህተቶች እንዳሉ ይናገራል:: እነዚህ አምስት ዋና ዋና ስህተቶች ከአጠቃላይ የስህተት መጠን አንጻር ሲታዩ፣ የቋንቋ አጠቃቀም 35% ፣ የቋንቋ አወቃቀር 30% ፣የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም 27% ፣ በአይነት ለመፈረጅ ያልተቻሉት 6% እና የጽንሰ ሃሳብ የስህተት ዓይነቶች 3% እንደሆኑ ይገልጻል (ገጽ:56):: አለማየሁ የስህተት ትንተናውን እና የመጠይቆቹን መረጃ በማገናዘብ ለስህተቶቹ ዋና ዋና ምንጭ ናቸው ብሎ ያቀረባቸው ምክንያቶች፣ የጽሑፍ ቋንቋ አጠቃቀምና አወቃቀር ደንብን አለማወቅ፣ ጽህፈትን አለመለማመድ፣ ኢሉታዊ የመማርና የማስተማር ዝንባሌና የተሳሳተ የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ናቸው::

በዚሁ ዓመት (1986) ክፍሌ ለሁለተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ ባቀረበው ጥናት ላይ የሁለተኛ ደረጃ፣ በተለይም የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ጉዳይ ተመልክቷል:: በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት፣ ጥናቱ የተመለከታቸው ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሑፍ ለመግለጽ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው ያሳያል:: ይህም፣ ተማሪዎች ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሃሳብ (መልዕክት) በትክክል የሚገልጹ ቃላት የመምረጥ፣ ሰዋሰዋዊ አገባብን የመጠበቅ፣ በስርዓተ ነጥቦች በአግባቡ የመጠቀም፣ የዐረፍተ ነገርን ትክክለኛ አሰካክ ጠብቆ የመጻፍና ሃሳብን አቀናብሮ የመግለጽ ችሎታቸው አነስተኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው::
ክፍሌ ጽህፈትን በማስተማሩ ረገድ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ በመጠቆም፣ በጥናቱ ለተደረሰበት ውጤት መንስኤ ከሆኑት ነገሮችም የመማሪያ መጻህፍቱ አቀራረብና የትምህርቱ አሰጣጥ በዋነኛነት ሊጠቀሱ የሚችሉ መሆናቸውን ይገልጻል::

* ክፍሌ የመማሪያ መጽሀፍቱ ሲል ከ1985 በፊት በትምህርት ላይ የነበሩትን ማለቱ ነው::

ከላይ በዝርዝር ለማየት የሞከርናቸው ስራዎች ተማሪዎች በሚከውኗቸው ጽሁፎች ላይ የሚሰሯቸውን ስህተቶች በመለየትና ለስህተቶቹ ምንጭ የሆኑትን ምክንያቶች በመዘርዘር የቀረቡ ናቸው። እነዚህ ስራዎች የተማሪዎቹን (ጸሐፍቱን) የጽሑፍ ክሂል ደረጃ በማሳየት ረገድ የማይናቅ መረጃ ቢያቀርቡም ጸሐፍቱ አንድን ጽሑፍ ለማውጣት የሚያልፉበትን መንገድና በሂደቱ ያለባቸውን ውስጣዊ ችግር ባጠቃላይ የተለያዩ ጽሑፎችን ለመከወን ያላቸውን «ስትራቴጂ» የመረመሩ አልነበሩም። ባዬ ስለትምህርቱ፣ ስለመጻህፍቱና ስለተማሪዎች የመጻፍ ብቃት እንዲህ ይላሉ፤

> ቀደም ባለው ጊዜ ይሰጥ የነበረው ትምህርት የሰዋሰው፣ የድርሰትና የንባብ ነበር። እንዲህ ወደኋላ ግን አትኩሮቱ በክህሎት ላይ እየሆነ ስለመጣ የሰዋሰው ድርሻ ሊመናመን ችሏል።... ክህሎት አንዱና ዋነኛው የቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ነው ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ፣ በዚህም በኩል ቢሆን ተማሪዎቻችን የሚደርሱበት ደረጃ ከፍተኛ ነው ለማለት በፍጹም አያስደፍርም። ሁለተኛ ደረጃ የጨረሰ ተማሪ፣ ዛሬ ጥሩ የስራ ማመልከቻ ቀርቶ፣ ተራ ደብዳቤ እንኳ በወጉ መጻፍ እየተሳነው መጥቷል። ከሁለት ያጣ ጎመን እየሆነ ነው። ከስርዓቱም ሆነ ከክህሎቱ የለበትም (1987:8)።

በእርግጥ ባዬ እንዳሉት፣ ቀደምት የቋንቋ ትምህርት ሰዋሰውን፣ ንባብንና ድርሰትን መሰረት ያደረጉ ነበሩ። የድርሰትም ሆነ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ሰዋሰው - ምርኩዝ ነበር( ለምሳሌ ያህል ለሰባተኛ ክፍል የድርሰት መማሪያ በተክለማርያም ፋንታዬ፣ 1955 ተዘጋጅቶ የቀረበውን መመልከት ይቻላል)። ከዚያም በማስከተል፣ በዘመነ ደርግ የወጡት የቋንቋው ማስተማሪያ መጻህፍት ሰዋሰውን ወደ ጎን ቢሉም በበቂ ሁኔታ ክሂሎችን ለማዳበር ተዘጋጅተዋል ለማለት አያስደፍርም (ለአስረጅ ከላይ ክፍሌና ባዩ ከሰጡት መረጃ በተጨማሪ እነዚህን መጻህፍት በመገምገም የቀረቡትን የሺበሺ 1985 እና የበየነ 1985 ስራዎችን ይመለከቷል)። ይሁን እንጂ እነዚህ መጻህፍት በአሁኑ ጊዜ ተቀይረዋል። አዳዲሶቹ መጻህፍት (ጥንካሬና ድክመታቸውን ወደ ጎን ትተን) በስራ ላይ ከዋሉበት ጊዜ ጀምሮም ይሄነው የተባለ መሻሻል አልታየም። መጻህፍቱ ቢለዋወጡም የተማሪው የመጻፍ ክሂል አልተሻሻለም።

ለዚህ ዋንኛው ምክንያት፣ ከመማሪያ መጻህፍቱ ድክመት ይልቅ፣ በርካታዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ በትምህርት ቤቶች ጽህፈትን አስመልክቶ ትምህርት አለመስጠቱ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ተስፋዬ እንዲህ ይላሉ፤

> በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ድርሰት ሳንጽፍ ከትምህርት ቤት የምንወጣ ቁጥራችን ጥቂት አይደለም። በተለይ ከአስርና ከአስራ አምስት አመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ በትምህርት ክፍለ ጊዜ መብዛትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እየተሳበበ የሚጻፈውም ሳይታረም ይቀራል። የተጻፈው ካልታረመ ደግሞ፣ ስህተት ወይም ትክክል መሆን አለመሆኑ ስለማይታወቅ፣ ካለመጻፉ ብዙም አይለይም(1986:9–10)።

ይህን ችግር ለማቃለል ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ እርስ በርሳቸው ተለዋውጠው በመተራረም የመምህሩን ጫና ለመቀነስ ይቻል እንደሆነ በማለት ሰሎሞን (1987) ጥናት አድርጓል:: ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት አበረታች ነው ለማለት አያስደፍርም::

በሌላው መልኩ፣ የዚህ ችግር አሳሳቢነት ካለመማር የመጣ ብቻ ሳይሆን፣ በኮሌጅ ደረጃም የድርሰት ኮርስን ወስደው ባለፉ ተማሪዎችም ዘንድ መታየቱ ነው:: በእርግጥ የመጻፍ ክሂል በቶሎ የሚጨበጥ አይደለም:: ይሁን እንጂ ከድርሰት ኮርስ ውጭ (በአ.አ.ዩ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል) የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቹ በአማርኛ የመጻፍ ችሎታቸው ደካማ እንደሆነ አምርረው ሲገልጹ ይሰማሉ::

ማረውም (1987) እነዚህ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ተማሪዎች በድርሰት ትምህርታቸው የበለጠ የሚረዱበትን መንገድ ለመጠቆም በቡድንና በግል እንዲጽፉ በማድረግ ንጽጽራዊ ጥናት አድርጓል::በዚህ ጥናቱ፣ ማረው በቡድን የሚጽፉት የተሻሉ ጽሑፎችን ማምረት ችለዋል በማለት የቡድን ስራ ቢበረታታ በድርሰት ትምህርት፣ የተሻሉ ጸሐፊዎችን ማምረት እንደሚቻል ያስረዳል::

ይሁን እንጂ ማረው አጠቃላይ የልጆቹን የመጻፍ ችሎታ፣ የተለያዩ ጽሑፎችን በመከወን ያለባቸውን ችግር በጥናቱ ያላካተተ ከመሆኑም በላይ፣ መፍትሄ ብሎ ያቀረበውም ቢሆን ለየትኞቹ ጽሁፎች ክዋኔ እንደሚጠቅምና ተማሪዎቹ በገሀዱ አለም አካዳሚያዊ ሕይወታቸው ለሚያጋጥሟቸው ጽሑፎችም ሆነ በውጭያዊ ሕይወታቸው ለሚያጋጥሟቸው ጽሑፎች ምን ያህል እንደሚረዳ አያመለክትም::

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸው ስራዎች የተወሰነ ነገር ላይ በማተኮር የተሰሩ እንጂ የጽሑፍ ዓይነቶችን በመቃኘት የተደረገ አይደሉም::

### *2.3.2 በሐገራችን የእንግሊዝኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተሰሩ ስራዎች*

የእንግሊዝኛ ቋንቋ በሀገራችን በሁለተኛ ደረጃም ሆነ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከአማርኛ ይልቅ በሰፋት በተለያዩ የትምህርት መስኮችና የትምህርት ዓይነቶች በትምህርት መስጫነት

የሚያገለግል ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአላማው ተማሪዎች የተሻሉ አካዳሚያዊ ጸሐፍት እንዲሆኑ ለማስቻል በውጭ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል ባሉ የቋንቋው መምህራን «ሶፎመር እንግሊሽ» (Sophomor English) የሚል ኮርስ ይሰጣል፡፡ Getnet (1993)በዚህ ኮርስ መምህራኑ ለተማሪዎች ድረስት የሚሰጡትን ምላሽ ሲያጠና፣ መምህራኑ የሚጠቀሙበት የማስተማር ስልት ጥንታዊ መሆኑንና ከተማሪዎች፣ ከትምህርት አቅርቦት እና ከሚፈለገው ውጤት ጋር ያልተጣጣመ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

የGetnet ጥናት ትኩረት፣ በእርግጥ ለተማሪዎች ድርሰት መምህራኑ የሚሰጡት ምላሽ ባህርይ ላይ ቢሆንም፣ ተማሪዎች ከመምህራቸው ለድርሰቶቻቸው ለሚያገኙት ምላሽ ያላቸውን ዝንባሌም ተመልክቷል፡፡ በግኝቱም፣ በተማሪዎች ፍላጎትና በመምህራን ምላሽ መካከል ከፍተኛ አለመጣጣም መኖሩን አሳይቷል፡፡ በእርግጥ የGetnet ጥናት በተለያዩ ተቋማት የሚገኙት ተማሪዎች መከወን ረገድ ስለሚገባቸው የጽሕፈት ስራዎችና በእውን የሚያጋጥሟቸውን የጽህፈት ስራዎች በመከወን ያሉበትን ደረጃ አያመለክትም፡፡ የዚህ ዓይነቱ ጥናት በአማርኛ (በላይኛው ርዕስ) እንዳየነው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ላይም የተደረገ አላጋጠመንም፡፡

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽህፈት ላይ የተደረጉ ጥናቶች በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች ትንታኔ (Mamo 1981)፣ በስነዘዴዎች ላይ ንጽጽራዊ ጥናት (Tesfaye 1991) ናቸው፡፡ ከነዚህ ውጭ የተደረጉ ጥናቶች ተማሪዎች አንድን የጽህፈት ኮርስ ከወሰዱ በኋላ በነጠላ የጽህፈት ክሂል ላይ የሚያሳዩትን ለውጥ (ለምሳሌ Kifle-Mariam 1988) እና በእርግጥ ጽህፈትን በተናጥል የተመለከተ አይሁን እንጂ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ጥናታቸው (ትምህርታቸው) ውስጥ የሚያስፈልጋቸውን የእንግሊዝኛ ቋንቋ በመመርመር በMorris (1982) የተደረገ ጥናት አለ፡፡

የMorris ጥናት፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው፣ በተናጠል ተማሪዎች በዩኒቨርስቲ ትምህርታቸው የሚያስፈልጋቸውን የጽህፈት ክሂል በመውሰድ በጥልቀት አያሳይ እንጂ፣ በትምህርት አለም የተማሪዎችን ተግባራዊ ፍላጎት በመመርመር ትኩረት መስጠት እንደሚገባ በመጠቆም ረገድ የማይናቅ አስተዋጽኦ አለው ለማለት የሚቻል ይመስለናል፡፡

በአጠቃላይ በሐገራችን በእንግሊዝኛ ቋንቋም ሆነ በአማርኛ ቋንቋ ጽህፈት ላይ የተደረጉ ጥናቶች /ስራዎች/ ተማሪው በተለያዩ አውዶች የሚያጋጥመውን የጽህፈት ስራ በመመርመር በጽህፈት መርሃ ግብሮች እነዚያን ስራዎች ለመከወን የሚያስችሉትን ልምምዶች እንዲያደርግ የሚጋብዙ

አላጋጠሙንም:: በሌላ መልኩም ፣ ተማሪው በመጻፍ ክሂሉ ከጽህፈት ኮርሶች ውጭ ሊረዳ የሚችልበትን መንገድ የጠቆሙ ወይም ያሳዩ ስራዎችም አላጋጠሙንም::

## 2.4 አካዳሚያዊ ጽህፈትን ለመበየን የተደረጉ ስራዎች

በትምህርት ዓለም እውቀት ከሚተላለፍባቸውና ከሚገኝባቸው የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ጽህፈት ነው:: ጽህፈት ለአካዳሚያዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: እንደ Savil-Troike አባባል፣ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ይልቅ «አካዳሚያዊ ክህሎትን የበለጠ የሚያሳድገው የቋንቋ ክሂል ጽህፈት ነው» (በLeki and Carson 1994:83 ውስጥ):: በሌላው መልኩ በትምህርት ሂደት ደግሞ ከሌሎች ክሂሎች ይልቅ አስቸጋሪው ክሂል ይሄው ነው:: ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርታቸው በቀላሉ ክሂሉን ጨብጠው በአካዳሚ የጽህፈት ክዋኔያቸው ሁሌ ብቁ ሆነው ሊገኙ አልቻሉም::

ይህ ችግር በመኖሩ (እና በተለይም ከተማሪዎች ቁጥር መጨመር፣ የተለያየ ባህላዊና ስነልሳናዊ ዳራ ያላቸው ቅይጥይጥ ተማሪዎች በአንድ ክፍል መገኘት የተነሳ ችግሩ በመባባሱ) አካዳሚያዊ ጽህፈት ምን እንደሆነና ተማሪዎች ይህን ለመጻፍ ወይም ለመከወን ምን ማወቅ እንደሚኖርባቸው መግለጽ አስፈለገ:: ይህን መግለጹ ግን ለተመራማሪዎችና ለመምህራን ቀላል ስራ እንዳልሆነላቸው Spack (1988:31) ይገልጻሉ::

በመጀመሪያና በሁለተኛ ቋንቋ ተመራማሪዎች ፣ በተለያዩ የትምህርት መስኮች የተለያዩ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል:: ጥናቶቹ በአንድ የትምህርት መስክ የአባላቱን ግንዛቤና የሚደረጉትን ልምምዶች በመቃኘት ያለውን የጽህፈት ሚና ለማወቅ (Jenkins, Jordan and Weliand 1993)፣ በተለያዩ የትምህርት መስኮች መምህራኑ ለተማሪዎች ጽሑፍ የሚሰጡትን ግምገማ በመተንተን (Santos 1988 ፣ ተማሪዎች የሚሰጧቸውን የጽህፈት ስራዎች እንዴት እንደሚከውኑ /Marssela , Hilgers & MacLaren 1992) ወዘተ.ን የመሳሰሉ ናቸው::

Marssela , Hilgers & MacLaren (1992) በመጀመሪያ ቋንቋ ባደረጉት ጥናት እንዳመለከቱት ተማሪዎች የጽህፈት ስራዎችን ለመከወን ያላቸው ብቃት ላይ ሁለት ነገሮች ተጽዕኖ ያደረጉበታል:: እነዚህም፣ ተማሪዎች ቀድመው የወሰዷቸው ስልጠናዎችና መምህራኑ አንድ ስራ እንዴት እንደሚከወን የሚያዙበት መንገድ ናቸው:: ከዚህ ሃሳብ በመነሳት Leki & Carson (1994) ተማሪዎች በወቅቱ ለሚያከናውኗቸው አካዳሚያዊ ጽሑፎች ቀድመው የወሰዷቸው

ስልጠናዎች ምን ያህል እንደጠቀሟቸው ለማወቅ ጥናት አድርገዋል:: በሌላው መልኩ፣ በአንድ አካዳሚያዊ የጽህፈት ስራ ውስጥ ያሉ ንዑሳን ክሂሎችን ተንትኖ ለማሳየት የተደረገ ጥናትም አለ (Horwitz 1986c )::

ከነዚህ ጥናቶች ውጭ በመጀመሪያ ቋንቋም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ አካዳሚያዊ የጽህፈት ዓይነቶችን ለመወሰን በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል:: ለምሳሌ Herrington & Moran (1992) ውስጥ በርካታ ሥራዎችን መመልከት ይቻላል:: ከዚህም በላይ Horwitz (1986e) Johns (1981) Kroll (1979) ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

Kroll (1979) የጽህፈት ስራዎች ዓይነቶችን ለማወቅ መጠይቅ አዘጋጅተው በመጀመሪያ ዓመት ለ55 የእንግሊዝኛ (Freshman English) ተማሪዎች በካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ አሰራጩ:: ከነዚህ ተማሪዎች 35ቱ እንግሊዝኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አልነበረም:: ተማሪዎቹ በመጠይቁ፣ በአለፈ፣ በአሁንና በወደፊት ሕይወታቸው የትኞቹ የጽሁፍ ስራዎች በምን ያህል ደረጃ እንደሚያጋጥሟቸው እንዲገልጹ ተጠየቁ:: ከዚህ ጥናት እንደተገኘው መረጃ ከሆነ፣ በድርሰት ክፍል ተዘውትሮ የሚሰጠው ጥንታዊው ግላዊ ብዕሮግ (traditional personal essay) ባለፈ፣ ባሁንም ሆነ በወደፊት ሕይወታቸው የመጻፍ ገጠመኝ በተማሪዎች ጠቃሚ ነው ተብሎ ሊመረጥ አልተቻለም:: እኚህ ሰው በድምዳሚያቸው የሚከተለውን አስፍረዋል፣

> .. ተማሪዎች በሕይወታቸው በተጨባጭ ሲተገበሩ የሚችሏቸውን ዓይነት ጽሑፎች እንዲለማመዱ ማነሳሳቱ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ነው ብዬ ለማሰብ አልችልም:: ይልቁንም ሁልጊዜ አስቸጋሪ ወይም ከባድ የሚሆነው፣ ከትምህርት ቤት ውጭ በሚመሩት ኑሮ የሚያጋጥማቸውን ትተን፣ በሌሎች ኮርሶች ከሚያጋጥሟቸው እውነተኛ የጽህፈት ስራዎች የተለዩ እንዲከውኑ ማነሳሳቱ ነው(1979:227)::

Spackም ይህን ጉዳይ አስመልክተው ተመሳሳይ ሃሳብ ሰንዝረዋል:: ከድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች የሚከወኑ ጽሁፎች በተማሪዎች አጠቃላይ እውቀት ላይ ብቻ መመስረታቸው በጣም አጠያያቂ ነው:: ስለዚህም፣ የሚሻለው ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት መስኮች ካሉት የጽሑፍ ስራዎች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ነው:: የጽህፈት መምህራንም በሂደት ተኮር ኮርሶች ጽሑፍ-ምርኩዝ (text-based) ስራዎችን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል:: የጽሁፍ ስራዎቹም የሆነን ነገር (ይዘትን) ለመማር እንደማዕከላዊ አስተላላፊ በመሆን ጉልህ ሚና መጫወት ይገባቸዋል (1988:34)::

ይሁን እንጂ፣ እኒህ ሰው አካዳሚያዊ ጽሁፎችን ለማስተማር ሲባል በጽህፈት ክፍል ውስጥ የሌሎች ኮርሶች ይዘቶችን አምጥቶ ማስተማር የሚለውን የWAC እና ESP እሳቤ አጥብቀው ይቃወማሉ:: መምህሩ፣ አካዳሚያዊ የጽሁፍ ስራዎቹን ዓይነት ለተማሪዎች ለማሳወቅ፣ ልምምዱን ከፈለገው ይዘት ላይ አተኩሮ ማድረግ አለበት እንጂ፣ በቂ ዕውቀት የሌለውን የሌላውን ኮርስ ይዘት አምጥቶ ማስተማር የለበትም (ዝኒ ከማሁ)::

በሌላው መልኩ፣ Spackም ሆኑ ሌሎች አጥኚዎች የተስማሙበት ነገር የጽህፈት ትምህርት ከግል ገጠመኝ በመነሳት በጥንታዊ የድርሰት ዓይነቶች (traditional composition geners) ላይ ብቻ ተመርኩዞ መሰጠት እንደሌለበት ነው:: በአሁኑ ጊዜም የጽህፈት ስራዎች ዓይነትን ለመተንተን ያስችል ዘንድ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት፣ ይህንኑ ርዕሰ ጉዳይ ብቻ ያደረጉ መጻህፍት ወጥተዋል (ለምሳሌ Swales 1990ን ይመለከቷል):: በተጓዳኝም የተለያዩ የጽህፈት ማስተማሪያ ስልተ ትውሮችን በመቃኘት (Silva 1990) እና ከስልተ ትውሮቹ መሀከል የተሻለ የሚባለውን ወይም ከእያንዳንዳቸው የተሻሉ ፣ የተሻሉ ነጥቦችን በመውሰድ ሂደት ተኮር የጽህፈት ልምምድን ከይዘት ጋር በማቀናጀት በርካታ ስራዎች ቀርበዋል (ለምሳሌ Kroll 1991፣ Olshtain 1991፣ Brooks & Grundy 1990ን ይመለከቷል)::

በአጠቃላይ እነዚህና መሰል በአሁኑ ጊዜ ጽህፈትን አስመልክተው የሚደረጉ ስራዎች የሚያሳዩን ተማሪዎች በአካዳሚያዊና በውጭው አለም ሕይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን የጽሁፍ ስራዎች ዓይነት በጽህፈት ትምህርታቸው መማር እንደሚገባቸው ነው::

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ንድፍ

### 3.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኒኮች

ይህ ጥናት በተለያዩ ኮርሶች የሚከወኑ የጽህፈት ስራዎችን ዓይነት፣ ለስራዎቹ የሚያስፈልጉ ንዑሳን ክሂሎች፣ የተማሪዎችን የመከወን ብቃት ወዘተ. ነጥቦችን የሚመለከት እንደመሆኑ፣ ለዚህ ተግባር ተገቢነት ያላቸው መረጃዎች በሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኒኮች ተሰብስበዋል።

### 3.1.1 መጠይቅ

ለዚህ ጥናት መረጃ በማሰባሰብ ያገለገሉ ሁለት መጠይቆች አሉ። እነዚህም የተማሪና የመምህራን መጠይቆች ናቸው።

#### 3.1.1.1 የተማሪ መጥይቅ

ይህ መጠይቅ በዓላማው ተማሪዎች በወቅቱ በሚከውኗቸው የጽሕፈት ስራዎች ውስጥ ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ክሂሎች ለማወቅና በተለይ በመጻፍ በኩል ያለባቸውን ውስጣዊ ችግር ለመመርመር የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም በመጠይቁ ከ1 - 17 ባሉ ተራ ቁጥሮች የተለያዩ ንዑሳን ክሂሎች ተዘርዝረዋል። ለነዚህ ጥያቄዎች የቀረቡት አምስት አማራጮቹ የሚከተሉት ናቸው፣

1 . እጅግ አስፈላጊ ነው።
2 . በጣም አስፈላጊ ነው።
3 . በመሀከለኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው።
4 . በዝቅተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው።
5 . አያስፈልግም።

ሌሎች ጥያቄዎች ( 22 እና 23) ተማሪው አንድን ጽሁፍ በመከወን በኩል ያለበትን ችግር መርምሮ ለማሳየት የራሱን ሃሳብ እንዲገልጽ የቀረቡ ፣ በምርጫ ያልተገደቡ ናቸው። ከ18 - 21 ያሉት ጥያቄዎች፣ በአንጻሩ፣ በነዚህ ሁለት ከላይ በገለጽናቸው ነጥቦች ለቀረቡት አጋዥ ወይም

ማብራሪያ ናቸው። ይህ መጠይቅ፣ በሌላው መልኩ በሙከራ ጥናት ተሞክሮና አግባብነት ያላቸው ሰዎች ተመልክተውት፣ ከሙከራ ጥናቱና ከሰዎቹ አስተያየት በመነሳት በዚህ ጥናት አንዳንድ መሻሻያዎችን አድርጎ የቀረበ ነው።

መጠይቁን መሙላት ከሚጠበቅባቸው አርባ ስድስት ተማሪዎች መካከል አምስቱ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት አልሞሉትም። ከአርባ አንዱ ተማሪዎች የተገኘው የመጠይቅ ውጤት ወይም መረጃ ከሌሎች መረጃዎች ጋር በየአርዕስቱ በምዕራፍ አራት ተተንትኖ ቀርቧል።

### *3.1.1.2 የመምህር መጠይቅ*

ይህ መጠይቅ መምህራኑ በኮርሳቸው ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን የጽሑፍ ስራዎች ዓይነት፣ ከነዚህ ስራዎች ውስጥ ለተማሪዎች አስቸጋሪ የሆኑት የትኞቹ እንደሆኑ፣ የአስቸጋሪነት ምንጫቸው ምን እንደሆነና የመሳሰሉትን ነጥቦች በመያዝ የተዘጋጀ ነው። ( ስለዝርዝር ይዘቱ አባሪ «ሀ » ን ይመለከቷል)።

መጠይቁ እንደተማሪዎች መጠይቅ ሁሉ በሙከራ ጥናት የተሞከረና በገምጋሚዎች አስተያየት ቀርቦበት ለዚህ ጥናት ተሻሽሎ የቀረበ ነው። በሌላው መልኩ፣ ይህ መጠይቅ የበሳል ድርሰት ኮርሶችን ስለማይመለከት በወቅቱ ይህን ኮርስ የሚያስተምሩ ሦስት መምህራን፣ ሌሎች የሚያስተምሯቸው ኮርሶች ቢኖሩም እንዲሞሉት አልተደረገም። ይህም ከበሳል ድርሰት ውጭ ስላሉት ኮርሶች ተገቢውን መረጃ ለማግኘት በማሰብ ነው። ከዚህ ውጭ መጠይቁን ስድስት መምህራን ሞልተውት ከነዚህ መምህራን የተገኘው መረጃ ከሌሎች መረጃዎች ጋር በተጓዳኝ በምዕራፍ አራት ተተንትኗል።

እነዚህ ሁለት መጠይቆች(የተማሪና የመምህር መጠይቆች) በራሳቸው ከሚያመነጩት መረጃ ባሻገር በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያዎች የተገኙትን መረጃዎች ማጠናከርና ትክክለኛነታቸውን ወይም አስተማማኝነታቸውን ማረጋገጥ በመሆኑም በተጓዳኝ ታይተዋል።

### 3.1.2 የኮርስ ቢጋርና መግለጫ

በበሳል ድርሰት ኮርሶች፣ የጽህፈት ትምህርት አሠጣጥ፣ የይዘት አቀራረብና አከዋወን ለመመርመር የኮርሶቹ (ELAm 203 እና ELAm 204) ቢጋሮችና በትምህርት ክፍሉ በተዛምዶ ያለው የኮርሶች መግለጫ (Course description) ለዚህ ጥናት በመረጃነት አገልግለዋል:: እነዚህ መረጃዎች የድርሰት ኮርሶችን አስመልክቶ ከተሰበሰቡት ሌሎች መረጃዎች (ቃለ መጠይቆችና የተማሪ ድርሰቶች) ጋር በቅንጅት እንዳስፈላጊነቱ ተተንትነው ከመቅረባቸውም በላይ ለበለጠ ማገናዘቢያ በአባሪ ተያይዘዋል (አባሪ « ለ»ን ይመለከቷል)::

### 3.1.3 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለን ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ቃለ መጠይቅ ነው:: ቃለ መጠይቁን በሁለት መልክ ልንመለከተው እንችላለን:: ይህም፣ አንደኛው በሳል ድርሰት ኮርሶችን አስመልክቶ የተደረገ ሲሆን፣ ሌላኛው ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ያሉትን ኮርሶች አስመልክቶ የተደረገ ነው::

የበሳል ድርሰት ኮርሶችን አስመልክቶ የተደረገው ቃለ መጠይቅ ኮርሶቹን በመውሰድ ላይ ከሚገኙት የክፍሉ ሁለተኛ ዓመት ፍቃደኛ ተማሪዎችና እነዚህን ተማሪዎች በማስተማር ላይ ከሚገኙት አንድ መምህር ጋር ነው:: የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ ከኮርሶቹ መግለጫ፣ ቢጋር እና ከስብስብ ድርሰቶች (ጽሁፎች) በተጨማሪ ስለኮርሶቹ (ELAm 203 እና ELAm 204) ሠፊ መረጃ ለማግኘትና ከነዚህ የመረጃ መሳሪያዎች ለተገኙት መረጃዎች አስተማማኝነት ማመሳከሪያም እንዲሆኑ በማሰብ ጭምር ነው::

ከበሳል ድርሰት ኮርስ ውጭ ስላሉ ኮርሶች የተደረገው ቃለ መጠይቅ በበሳል ድርሰት ኮርሶች እንደተደረገው ከሁለቱም፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር ነው:: የዚህ ቃለ መጠይቅ ዋና አላማም በተዛምዶ ስለኮርሶቹ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያዎች የተገኙትን ለአስተማማኝነት ማመሳከሪያ እንዲሆንና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኛ ነው:: (በቃለ መጠይቆቹ የቀረቡትን ዝርዝር ጥያቄዎች በተመለከተ አባሪ «መ»ን ይመለከቷል::)

### *3.1.4 የተማሪ ጽሑፎች*

በዚህ ጥናት በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች ያሉትን የጽሁፍ ስራዎች ዓይነት ለማወቅ ወይም፣ በሌላ አገላለጽ የጽሁፍ ስራዎቹን ለመከልሰፍና የመምህራኑን አስተራረም ባህርይ በንጽጽር ለማየት ከሁለቱም ጎራ (በሳል ድርሰትና ሌሎች ኮርሶች) መምህራኑ እርማት ካደረጉባቸው በኋላ የተማሪ ጽሁፎች ተሰብስበዋል::

በበሳል ድርሰት ኮርሶች በርካታ የጽሕፈት ልምምዶች ይደረጋሉና ስለኮርሶቹ ተገቢ ግንዛቤ ለማግኘት (ከላይ ከገለጽናቸው ጉዳዩች በተጨማሪ – ለምሳሌ ስለአከዋወናቸው) የተወሰኑትን ብቻ መመልከቱ በቂ አልነበረም:: ስለሆነም፣ ስለኮርሶቹ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያዎች ከምናገኘው መረጃ በተጨማሪ (በዋናነት) በሁለቱም ኮርሶች በርካታ ጽሁፎች ተሰብስበዋል:: (ዝርዝሩን ከሚከተለው ሠንጠረዥ ይመልከቱ::)

<u>ሰ ን ጠ ረ ዥ 2</u>

በበሳል ድርሰት ኮርሶች ተማሪዎች ከሚከውኗቸው ጽሁፎች ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡ

| ተ | አንቀጽ ደረጃ ልምምድ ጽሁፎች(ለሐሀቄ 203) | | ድርሰት ደረጃ ልምምዶች(ለሐሀቄ 204) | |
|---|---|---|---|---|
| ቁ | የአንቀጽ ርዕስ ወይም ሐይለ ቃል | ብዛት | የድርሰት ርዕስ | ብዛት |
| 1 | የትምህርት ቤታችንን አጥር ለማሳጠር እንድንችል የገቢ ማስገኛ በዓል ማዘጋጀት አንዱ አማራጫችን ነው:: | 15 | የዩኒቨርስቲ ቆይታዬ /የኮሌጅ ውስጥ ኑሮ | 19 |
| 2 | ትምህርት ቤት የገባሁበት (ዕለት) ትዝታ/ የትምህርት ቤት ትዝታዬ | 9 | ግንቦት ልደታ | 6 |
| 3 | የልጅነት (ዘመን) ( (ጊዜ) ትዝታ) | 9 | የማርክስ ሀውልት | 1 |
| 4 | አበባ ውበቷ የተፈጥሮ ሀብቷ ብቻ ነው/ የሄዋንን (የደብሪቱን) ውበት አደንቃለሁ | 5 | ሴቶች ከወንዶች (አያንሱም) ያንሳሉ ወይስ እኩል ናቸው | 6 |
| 5 | ማንኛውም ሰው ችግር ሲጋረጥበት ከሦስት መርሆዎች በአንደኛው ተጠቅሞ ችግሩን ለመቋቋም ይሞክራል:: | 1 | (በአሁኑ ስዓት) ትምህርት ወይስ ንግድ/ እርካታ በገንዘብ ወይስ በትምህርት | 7 |
| 6 | (የመረዳጃ) እድር | 7 | የገጠርና የከተማ(ትምህርት ቤት/ኦች) ኑሮ | 11 |
| 7 | ተስፋ ያጣ ሕይወት | 1 | ወንደላጤነት ወይስ ባለትዳርነት | 5 |
| 8 | የአለሙ ሠርግ | 1 | መሬት ክብ ወይስ ዝርግ | 1 |
| 9 | ከወራቶች ሁሉ የሚያስደስተኝ መስከረም ነው | 3 | ዲሞክራሲ ለ3ኛው አለም ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም | 1 |
| 10 | አቶ ከበደ በጣም ደስ ብሏቸዋል | 1 | የኢትዩጵያ ጥናት ተቋም ሙዚየም | 1 |
| 11 | የመጀመሪያ ጉዞ | 1 | ኬኔዲ ቤተመጻህፍት | 2 |
| 12 | የፍትህ ሀውልት | 1 | «በግ ተራ» | 3 |
| 13 | ማሪዎች በኬኔዲ ቤተመጻህፍት | 1 | የጣሊያን ወረራ | 1 |
| 14 | የመጀመሪያ ዓመት ዩኒቨርስቲ ቆይታዬ | 1 | የመጽሐፍ ሪፖርት (የዕንባ ጠብታዎች ላይ) | 1 |
| 15 | ርዕስ የሌለው ወይም ሀይለ ቃሉ የማይታወቅ | 1 | ርዕስ የሌለው | 1 |
| | ድ ም ር | 57 | ድ ም ር | 66 |

በነዚህ ሁለት የበሳል ድርሰት ኮርሶች የተሰበቡት ጽሁፎችና በሌሎች ኮርሶች የተሰበሰቡት ጽሁፎች በሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከተገኙት መረጃዎች ጋር በተጓዳኝ (ከላይ

ላነሳቸው ጉዳዮችና በየጽሁፎቹ የሚያስፈልጉትን ዝርዝር ክሂሎች ለማወቅ) ተተንትነዋል:: የነዚህና የሌሎች መረጃዎችን አተናተን በተመለከተ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን::

## 3.2 *የመረጃ አተናተን ስልት*

ይህ ስራ ገላጭ የምርምር ዘዴን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ በዓላማው የታቀደውን ከግብ ለማድረስ በየመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎቹ የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደየነጥቦቹ ዓይነት ወይም ባህሪ በቅንጅትና በተጓዳኝ ይተነትናል፣ ማብራሪያም ይሰጣል:: ከላይ በየአርዕስቱ እያንዳንቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኒኮች በምንመለከትበት ወቅት አተናተናቸውን በዝርዝር የገለጽን በመሆኑ እንደገና በዚህ ርዕስ ስር ልንመለስበት አንፈልግም:: ይሁን እንጂ፣ የጽሁፍ ስራዎቹ ዓይነት አከፋፈልና ለነዚህ የጽሁፍ ስራዎች መምህራኑ የሚሰጡት ምላሽ (እርማት) በምን መልክ እንደተተነተኑ ወይም እንደተከፈሉ መግለጽ አስፈላጊ ይመስለናል:: ስለዚህምቀጥለን የጽሁፍ ስራዎቹን አከፋፈል ስልትና የመምህራኑን እርማት አተናተን ራሳቸውን በቻሉ አርዕስት እንመለከታለን::

### 3.2.1 የጽሑፍ ስራዎቹ አከፋፈል ስልት

ተማሪዎች በተለያዩ የትምህርት መስኮች እና/ወይም የትምህርት ዓይነቶች የሚያከናውኗቸውን የጽህፈት ስራዎች ዓይነት ለማወቅ በተደረጉ ጥናቶች ላይ ሁለት ዓይነት የአከፋፈል መንገዶች ይታያሉ:: አንደኛው፣ የጽሁፍ ዓይነቶችን በመዘርዘር መጠይቅ አዘጋጅቶ፣ የትኞቹ በምን ያህል ደረጃ እንደሚከወኑ፣ ተማሪዎችን ወይም መምህራንን መጠየቅ ሲሆን (ለዚህ ምሳሌ Kroll 1979 ይመለከቷል)፣ ሌላኛው፣ የጽሑፍ ስራዎቹን በመሰብሰብ፣ ስብስቦቹን መሠረት አድርጎ መከፋፈል ነው (ለዚህ Horwitz 1986ን ይመለከቷል):: ከነዚህ ስልቶች አንደኛው ከሌላኛው ሙሉ በሙሉ የተሻለ ወይም ደካማ ነው ማለት አይቻልም:: ሁለቱም የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመት አላቸው::

በመጠይቅ መልክ ተዘጋጅቶ የጽሁፍ ስራዎችን ለመክፈል የሚደረገው በጥናቱ በርካታ ተጠኝዎችን ለማካተት የሚችል በመሆኑ፣ በጠንካራ ጎኑ ቢጠቀስም፣ በጽሁፍ ስራዎቹ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ ባህሪ ሊያሳየን አይችልም የሚል ጠንካራ ወቀሳ ሲሰነዘርበት ይታያል:: ይህን አስመልክተው፣ ከላይ የጠቀስናቸው ምሁር፣ የጽህፈት ስራዎች ምን እንደሆኑ ከመፈልፈል

ይልቅ ቀድሞ በተተነበየ አከፋፈል ላይ ተመስርተው ተጠኝዎችን (respondants) ወደዚያ ቀመር፣ በየቅኝቱ በተዘጋጀው ለማስገባት ያስገድዳሉ (Horwitz 1986e :448) በማለት ይተቻሉ። በሌላው ወገን የጽሁፍ ስራዎቹን በመሰብሰብ የሚደረገው ምደባ ከዚህ ችግር (ድክመት) ነጻ በመሆኑ፣ በጠንካራነቱ ቢወደስም፣ በርካታ የጽህፈት ስራዎችን መሰብሰቡና፣ቢሰበሰቡም፣ በአንድ ጥናት (በተወሰነ ጊዜ) አካቶ ማየት አስቸጋሪ በመሆኑ ይህ የአከፋፈል ስልትም በዚህ መልኩ በድክመት ይተቻል።

ለዚህ ስራም እነዚህን ድክመቶች በተቻለ መጠን የሚያቻችል ሞዴል ማውጣት ነበረብን። በዚህም ምክንያት መረጃዎችን በሁለቱም መንገዶች ለመሰብሰብ ተሞክሯል። ይህም መምህራኑ ለተማሪዎች የሚሰጧቸውን የጽህፈት ስራዎች ዓይነት እንዲገልጹ በመጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን (ከአባሪ «ሀ» የመምህር መጠይቅ ቁጥር 2ን ይመለከቷል።)፣ መጠይቁን ባልሞሉ መምህራን ደግሞ ሌሎች ስራዎች ይሰጡ እንደሆን ለማወቅ ኮርሶቹን ከሚወስዱ ተማሪዎች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። በነዚህ ከሚገኙት መረጃዎች በመነሳት፣ የጽሁፍ ዓይነቶቹ ከተለዩ በኋላ፣ ውስጣዊ ባህርያቸውን ለመመርመር ስብስብ ድርሰቶቹም (የጽሁፍ ስራዎች) በተጓዳኝ ተተንትነዋል። በአጭሩ፣ ክፍፍሉ እነዚህን መረጃዎች በተጓዳኝ ወይም በቅንጅት በመመልከት የተደረገ ነው።

### 3.2.2 የመምህራን ምላሽ አተናተን ስልት

መምህራን ለተማሪዎች ጽሁፎች የሚሰጡትን ምላሽ ለማወቅ፣ ማለትም፣ መምህራን የተማሪዎችን ጽሁፎች በሚያርሙበት ወቅት ምን ላይ እንደሚያተኩሩ ለማወቅ፣ ለበሳል ድርሰት ኮርሶች መምህር ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ሲሆን፣ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ያሉ መምህር ደግሞ በመጠይቁ ተጠይቀዋል።

ከዚህ ውጭ፣ ከላይ እንደገለጽነው፣ ለመረጃው አስተማማኝነትና መምህራኑ የሚሰጡትን የጽሁፍ እርማት ባህሪ ለማየት የተሰበሰቡት ድርሰቶች ተተንትነዋል። በትንተናው እርማቱ በዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች (Low level features of writing) እና በከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች (High level features of writing) ላይ እንደሚያተኩር ለማወቅ ሜካኒክስ፣ ሰዋሰው፣ ቃላት፣ አደረጃጀት እና ይዘት በሚሉ አምስት የጽሁፍ ገጽታዎች ስር ታይቷል። በዚህ ስልት፣ የመምህራን የእርማት ትኩረትን ለማወቅ Cohen (1987)፣ Getnet (1993) እነዚህን የጽሁፍ

ገጽታዎች በመዘርዘር በመጠይቅ መልክ ተጠቅመውበታል:: (በነዚህ የጽሁፍ ገጽታዎች ስር እርማቶቹ በምን መልክ እንደታዩና እንዴት እንደተተነተኑ የሚያሳይ ተጨማሪ መግለጫ በአባሪ «ረ» ተያይዟል::)

# ምዕራፍ አራት

## ውጤትና ማብራሪያ

ይህ ክፍል በምዕራፍ አንድ የተነሱትን የምርምር ጥያቄዎች በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረትነት ተንትኖና አብራርቶ ለመመለስ የሚሞክር ነው፡፡ ጥናቱ በበሳል ድርሰት ኮርሶችና በሌሎች ኮርሶች የጽህፈት ስራዎችን በንጽጽር የሚመለከት በመሆኑ፣ ይህን ከግንዛቤ በማስገባትና ግልጽና ተገቢ አካሄድ እንዲኖር የውጤት ትንተናውና ማብራሪያው በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡

የመጀመሪያው ክፍል የበሳል ድርሰት ኮርሶችን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ክፍል በምዕራፍ አንድ በንዑስ ርዕስ 1 . 5 ስር በተራ ቁጥር ሁለት ለተነሱት አቤይት የምርምር ጥያቄዎችና ሌሎች እነዚህን ኮርሶች የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዩች ስለኮርሶቹ በተዛምዶ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተንና በማብራራት ምላሽ የሚያቀርብ ነው፡፡

ሁለተኛው ክፍል ከድርሰት ኮርሶች ውጭ ያሉ ኮርሶችን የሚመለከት ነው፡፡ የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ በነዚህ ኮርሶች የሚከወኑትን የጽሁፍ ስራዎች ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ ትንተናው በምዕራፍ አንድ በአላማው ስር በተራ ቁጥር አንድ ለተነሱ የምርምር ጥያቄዎችና ሌሎች ከነዚሁ ጋር ተዛምዶ ላላቸው ዝርዝር ነጥቦች በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረትነት ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡

ሦስትኛው ክፍል፣ ከላይ በቀረቡት ሁለት ክፍሎች በተናጥል፣ በመረጃ ትንተናው የተገኙትን ውጤቶች በመያዝ በየነጥቦቹ ንጽጽራዊ ማብራሪያ የሚያቀርብ ነው፡፡

## 4.1 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች

በዚህ ርዕስ ስር በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶችን ወይም ስራዎችን እና ተዛማጅ ጉዳዩችን አስመልክተው የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚከተሉት ንዑሳን አርዕስት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች ዓይነት

የጽህፈት ልምምዶችን በሁለት ጎራ መመደብ ወይም መክፈል ይቻለናል ይላሉ White (1989:17)። እነዚህም ዐረፍተ ነገር ደረጃ ማጠናከሪያ ልምምዶች (Sentence level reinforement exercises) እና ዲስኩር ደረጃ «የተግባር» ልምምዶች (discourse level practice exercises) ናቸው። የመጀመሪያው ዓይነት ልምምድ ከተወሰነ የቋንቋ አላባ ላይ የሚያተኩር (ለምሳሌ ሰዋሰው ፣ ስርዓተ ነጥብ) የዐረፍተ ነገሮች ተናጠል ክዋኔ ነው። ሁለተኛው ዓይነት ልምምድ ልዩ ልዩ የጽሁፍ መዋቅሮችን ለማሳየት ሲባል የተያያዙ ዐረፍተ ነገሮች ክትትል የሚደረግበት ነው። ይህም አንድና ከአንድ በላይ አንቀጾችን በመጻፍ የሚደረጉ ልምምዶችን ሁሉ ያካትታል።

በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት ልምምዶች ምን ዓይነት እንደሆኑ እንዲገልጹልን ላቀረብነው ጥያቄ መምህሩ የሰጡት ምላሽ የሚከተለው ነው፡-

> በዚህ ሴሜስተር ( ELAm 203) የሚሰጠው የድርሰት ልምምድ የቃላት አጠቃቀም፣ የዓረፍተ ነገር ምስረታ ዓይነት (ረጂምና አጭር)፣ የአንቀጽ ግንባታ ነው። ... የአንቀጽ አንድነት፣ ጽምረትና አትኩሮትን በሚመለከት ተከታታይ ልምምዶች ይደረጋሉ።

ተከታዩን ኮርስ (ELAm 204) አስመልክቶ ላቀረብንላቸው ጥያቄም የሰጡት ምላሽ ከአንቀጽ በላይ የመጻፍ ልምምዶች እንደሚደረጉ ያሳያል። በክፍሉ የሚገኘው የኮርሶቹ መግለጫ እና በተዛምዶ ያሉት የኮርሶቹ ቢጋሮችም የሚያሳዩን ይሄንኑ ነው። በመጀመሪያው ኮርስ (ELAm 203) ከዐረፍተ ነገር ምስረታ እስከ አንቀጽ ግንባታ የሚደርስ ልምምድ ሲደረግ፣ በሁለተኛው ኮርስ የተሟላ ድርሰት በመጻፍ ልምምድ ይደረጋል። (ለዝርዝር መረጃ የኮርሶቹን ቢጋርና መግለጫ ከአባሪ «ሀ» ይመለከቷል።)

ከመምህሩ ቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ፣ ከኮርሶቹ መግለጫና ቢጋሮች በመነሳት፣ እነዚህን ልምምዶች ከላይ ባየናቸው ሁለት ጎራዎች መመደብ ይቻለናል። በELAm 204 የሚደረጉት ልምምዶች በአጠቃላይ ዲስኩር ደረጃ ልምምዶች ሲሆኑ፣ በELAm 203 የሚደረጉት ደግሞ ሁለቱንም ዓይነት የያዙ ናቸው። በዚህ ኮርስ (ELAm 203) የሚደረጉት ልምምዶች 25% በዐረፍተ ነገር ደረጃ፣ 75% ዲስኩር ደረጃ መሆናቸውን ከመምህሩ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ

ያሳያል:: በሁለቱም ኮርሶች የሚደረጉት ልምምዶች በአንድነት ሲታዩ ዲስኩር ደረጃ ልምምዶች 87.5% ዐረፍተ ነገር ደረጃ ልምምዶች ደግሞ 12.5% ይሆናሉ::

### 4.1.2 በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች ባህርይ

ከላይ የጽህፈት ልምምዶቹን ዓይነት በሁለት ጎራ ስንከፍል፣ እንደ White (1989) ውስጣዊ ባህርያቸውን መርምረን በማካተት አልነበረም:: እኚህ ምሁር የጽህፈት ልምምዶችን ከባህርያቸው አንጻር፣ ስህተት ፍንጮች (false cues) እና ጥሩ ፍንጮች (good cues) በማለት በሁለት ይፈርጇቿዋል::

ጥሩ ፍንጮች የሚሏቸው ልምምዶች ተማሪው ስለሚጽፍበት ርዕስ ዓላማ (purpose)፣ ለጽሁፉ ተጨባጭ መነሻ ወይም መረጃ ኖሮት የሚከውናቸው ናቸው:: ከዚህም በላይ ልምምዶቹ በገሀዱ ዓለም ስላለ የጽሁፍ ዓይነት ተገቢ መረጃ የሚሰጡና በእውን የሚገኙ ዓይነት ቅርጽ ሲኖራቸው፣ በሌላ አነጋገር ተግባቦትን ለማዳበር ሲደረጉ ነው:: ተፈላጊዎቹ መዋቅሮች ወይም የጽሁፍ ሕግጋት እነዚህን መሠረት በማድረግ በሁለተኛነት በትምህርቱ የሚቀርቡ ናቸው፤ ማለትም ቅድሚያ ትኩረታቸው ተግባቦት ላይ ሆኖ መዋቅር ሁለተኛው ትኩረታቸው ይሆናል (White 1989:25 )::

ስህተት ፍንጮች የሚሏቸው፣ ማናቸውም ዐረፍተ ነገርን በተናጠል በመመስረት የሚደረጉ ልምምዶችና በዲስኩር ደረጃ ደግሞ፣ የተያያዙ ዐረፍተ ነገሮች አንድን መዋቅር (ለምሳሌ ሐይለ ቃል አቀማመጥን፣ ገላጭ ድርሰትን፣ ተራኪ ድርሰትን ...) ለማሳወቅ የሚደረጉ ልምምዶች ናቸው:: እንደኚህ ምሁር አባባል ከሆነ፣ እንደነዚህ ዓይነት ልምምዶች የተያያዙ ዐረፍተ ነገሮችን ቢያካትቱም ተግባቦትን ለማዳበር የሚረዱ ተግባራት አይደሉም (ገጽ:19)::

በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉትን ልምምዶች: ከእኚህ ምሁር ጋር በመወገን አሳሳችና ትክክለኛ ወይም ተገቢና ኢተገቢ በማለት ለመፈረጅ አንዳዳም:: ይሁን እንጂ በየነጥቦቹ በመታገዝ ባህርያቸውን መመርመሩ ተገቢ ይመስለናልና ልምምዶቹ በተግባቦት ወይም በመዋቅር ላይ እንደሚያተኩሩ ቀጥለን እንመለከታለን:: ከላይ እንደተገለጸው በአረፍተ ነገር ደረጃ የሚደረጉት ልምምዶች አጭርና ረጂም አረፍተ ነገር መጻፍ፣በአረፍተ ነገሩም ላይ ሰዋሰዋዊ ስህተት፣ የስርአተ ነጥብ ስህተት እንዳይከሰት መከታተልና ደጋግሞ መስራት እንደሆነ ከተማሪውና ከመምህሩ ጋር የተደረገው የቃለ መጠይቅ መረጃ ያሳያል:: እነዚህ አረፍተ ነገርን

በተናጠል እየጻፉ የሚደረጉ ልምምዶች ቅድሚያ ትኩረታቸው ተግባቦት ላይ ሳይሆን ከላይ በተገለጹት ነጥቦች (አገባብን ጠብቆ ረጅምና አጭር አረፍተ ነገር መጻፍ) ላይ ነው።

በዲስኩር ደረጃ ስንመለከት አንቀጽን በመጻፍ የሚደረጉት፣ ለአንቀጹ ሐይለ ቃል ወይም ርዕስ በተማሪው ወይም በመምህሩ በቅድሚያ ይመረጥና የተመረጠውን ርዕስ ወይም ሐይለቃል በመያዝ ልምምዱ እንደሚከናወን ከመምህሩ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ያሳያል። የነዚህ ልምምዶች ዋና አላማ የአንቀጽ ግንባታ፣ የአንቀጽ አንድነት፣ ጽምረትና አትኩሮትን በተመለከተ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ነው። ከአንቀጽ በላይ የሚደረጉ ልምምዶችም ገላጭ፣ ተራኪ፣ አስረጅ እና አከራካሪ ድርሰቶች ላይ የሚያተኩሩ ሲሆን በተጨማሪም፣ አንድ የታተመ መጽሐፍ አንብበው ሪፖርት እንደሚጽፉ ከኮርሱ ቢጋርና ከመምህሩ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ ያሳያል። በ ELAm 204 አስራ አምስት የተለያዩ ርእሶችን ከያዙት 66 ስብስብ ድርሰቶች ውስጥ አንደኛው ይህን የመጽሐፍ ሪፖርትን የተመለከተ ነው። (ከሠንጠረዥ 2 ቁጥር 14ን ይመለከቷል።)

እነዚህ በዲስኩር ደረጃ የሚደረጉት ልምምዶች በምን ዓይነት የቋንቋ አጠቃቀም ባህርይ ላይ እንደሚያተኩሩ ለማወቅ ለመምህሩ «ጽህፈትን የሚሰጡት ለብቻ ነው ወይስ ከሌሎች ስራዎች በማቀናጀት?» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው «እንዳስፈላጊነቱ ነው» የሚል ምላሽ መስጠታቸውን ከቃለመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያሳያል። በማስከተል፣ ከምን ዓይነት ስራዎች ጋር እንደሚቀናጁ ለተጠየቀው ጥያቄ፣ አንብቦ መረዳትና «መተርጎም»፣ ማስፋፋት፣ ማሳጠር፣ ስዕል አይቶ መጻፍ፣ አካባቢን ቃኝቶ መግለጽ የመሳሰሉ እንደሆኑ የተሰጠው ምላሽ ያመለክታል።

በጽህፈት ትምህርት እንደነዚህ ዓይነት የቅንጅት ልምምዶች ተገቢና የተማሪዎቹን የመጻፍ ክሂል በማጎልበት ረገድ ጠቃሚ እንደሆኑ ይነገራል። ይሁን እንጂ፣ አብዛኞቹ ልምምዶች የተለያዩ ምንባባትን፣ ምንጮችን (ስእልን፣ የተፈጥሮ ገጽታን) መሠረት በማደረግ የተሰሩ ሳይሆኑ ከግላዊ ገጠመኝ ወይም ልምድ በመነሳት የተጻፉ ናቸው። ከግላዊ ገጠመኝ ውጭ ሌላ ምንጭን መሠረት በማድረግ የሚሰሩትም ቢሆኑ የተለየ ቅርጽ የላቸውም። ባህርያቸውን ስንመለከት፣ በራሳቸው ከማሳጠር፣ ከመተረክ፣ ከማስፋፋት ወይም ከመግለጽ ባጠቃላይ ከአንድ መዋቅራዊ ባህርይ ላይ እንጂ አንድ ተግባቦታዊ አውድን ፈጥሮ ከመጠቀም ላይ ያተኮሩ አይደሉም።

### 4.1.3 የጽህፈት ልምምዶቹ አከዋወን

በበሳል ድርስት ኮርሶች የሚደረጉት የጽህፈት ልምምዶች፣ ዐረፍተ ነገር ደረጃ ልምምዶች እና ዲስኩር ደረጃ የጽህፈት ልምምዶች በማለት በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ከላይ፣ በ4.1.1 ስር ተመልክተናል:: ከነዚህ ልምምዶች፣ ዐረፍተ ነገርን በተናጠል በመጻፍ (በELAm 203) የሚደረጉት ልምምዶች፣ ባጠቃላይ በግል የሚከወኑ ሲሆኑ፣ በዲስኩር ደረጃ የሚደረጉት ልምምዶች ደግሞ በግልም በቡድንም የሚከወኑ ናቸው:: ከነዚህ፣ ዲስኩር ደረጃ ልምምዶች መካከል 1/3ኛ (33.33%) በቡድን፣ የተቀሩት 2/3ኛ (66.67%) በግል እንደሚከወኑ ከበሳል ድርስት መምህር የተገኘው የቃለመጠይቅ መረጃ ያሳያል::

በዚሁ ቃለመጠይቅ ላይ «ተማሪዎች እየጻፉ ባሉበት ወቅት ማለትም በመጻፍ ሂደት ላይ ሳሉ አብረዋቸው ይሠራሉ?» እና «እንዲከልሱና አርትኦት እንዲያደረጉ ያበረታቷቸዋል?» በሚል ለተነሱት ጥያቄዎች፣ «አንዳንድ ጊዜ እሠራለሁ» እና «ሁልጊዜ አበረታታቸዋለሁ» የሚሉ መረጃዎች እንደቅደም ተከተላቸው ተገኝተዋል:: ይሁን እንጂ፣ «ሁልጊዜ አበረታታቸዋለሁ» የሚል መረጃ ከመምህሩ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ ቢገኝም፣ ይህ በሃሳብነት በቃል ደረጃ ከመንገር አልፎ በመማር ማስተማሩ ስራ ሁልጊዜ በተግባር የጽሁፍ ሂደት ላይ ይተኮራል ማለት አይደለም:: ይህ አለመሆኑን በማስከተል በዚሁ ቃለመጠይቅ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምላሾችና ከስብስብ ጽሁፎቹ መረዳት ይቻላል::

በአጠቃላይ ከሚደረጉት ልምምዶች የንድፍ ክለሳ የሚደረግባቸው ወይም በመጻፍ ሂደት ላይ የሚያተኩሩት ምን ያህሉ እንደሆኑ እንዲገልጹ በቃለመጠይቁ ላይ ለተነሳው ጥያቄ 20% አካባቢ እንደሆኑ መረጃው ያሳያል:: ይህም 80% አካባቢ የሚሆኑት የጽህፈት ልምምዶች ክለሳ አይደረግባቸውም ማለት ነው:: ክለሳ በሚደረግባቸው ፣ 20% ልምምዶችም ላይ ክለሳው ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚደረግ ለመሆኑ መረጃ ተገኝቷል:: ይህ መረጃ በሚሰበሰብበት ሰዓት የመጀመሪያው ኮርስ (ELAm 203) ተጠናቆ፣ ተከታዩ ኮርስ ( ELAm 204) በመሰጠት ላይ ስለነበረ የመጀመሪያውን ኮርስ አስመልክቶ «ትክክለኛ» መረጃ ማግኘት ይቻላል ከሚል እምነት በመነሳት፣ ለቀረበው ጥያቄ፣ በዲስኩር ደረጃ ከተከወኑት 6 ልምምዶች በአንዱ ላይ ብቻ የክለሳ ሂደት እንደተካሄደና፣ በዚህም ላይ ክለሳው ለአንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነ መረጃ ተገኝቷል:: ከዚህ ኮርስ ከተሰበሰቡት ድርሰቶችም «የመረዳጃ እድር» እና «እድር» በሚሉ ርዕሶች የተጻፉት ብቻ

ለአንድ ጊዜ የንድፍ  ክለሳ የተደረገባቸው ናቸው:: በሌላው ኮርስ (ELAm 204) ከተሰበሰቡት ድርሰቶች ክለሳ የተደረገባቸው የሉም::

ከነዚህ ነጥቦች መረዳት የምንችለው በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት ልምምዶች ክዋኔ በአብዛኛው የጽሁፍ ሂደት ላይ ያተኮረ ሳይሆን የመጨረሻው ውጤት ላይ እንደሆነ ነው:: የጽሁፍ ሂደት ላይ የሚያተኩሩት የተወሰኑት (ከመምህሩ ቃለመጠይቅ በተገኘው መረጃ መሠረት 20%) ብቻ ናቸው:: በነዚህም ላይ ቢሆን ተማሪው የመጀመሪያውን ረቂቅ ይጽፋል፤በዚያ ላይ አስተያየት ከተሰጠ በኋላ አስተያየቱን መሠረት በማድረግ ለአንድ ጊዜ ከልሶ ይጽፋል:: ይህ ጽሁፍም እንደመጨረሻው ውጤት ይታያል:: የዚህ አይነቱ ልምምድም ቢሆን የመጻፍ ሂደትን ሙሉ በሙሉ መጠቀምን አያሳይም::

የመጻፍ ሂደት ሃሳቦችን ማሰባሰብ፣ እነዚያን ሃሳቦች ነጥብ በነጥብ መመርመርና በማስታወሻ ማስፈር፣ ከዚያም የመጀመሪያውን ረቂቅ ሃሳብ እንደመጣ ዝም ብሎ (ለሰዋሰው ፣ ለአደረጃጀት ... ሳይጨነቁ) ማስፈር (መጻፍ)፣ በዚያ ላይ ይዘቱን፣ አደረጃጀቱን፣ ባጠቃላይ ዋና ስህተቶችን (global errors) ማስተካከል – ይህም እነዚህ ስህተቶች እስከሚስተካከሉ ድረስ፣ አንዴ፣ ሁለቴ፣ ሦስቴ ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል፣ ከልሶና ከላልሶ መጻፍ፣ በመጨረሻው ክለሳ ላይ (እነዚህ ስህተቶች ከተስተካከሉ በኋላ) አርትኦት ማድረግ (አርትኦት በአነስተኛ ስህተቶች (Local errors) – ሰዋሰው፣ ሜካኒክስ፣ ስርዓተ ነጥብና የመሳሰሉት ላይ የሚደረግ ነው)፤ ከዚያም የመጨረሻውን ጽሁፍ ማውጣትን ይመለከታል::  የመጨረሻው የጽሁፍ ውጤት ቢያንስ በነዚህ ደረጃዎች ካለፈ በኋላ የሚገኝ እንደሆነ Raimes (1983)፣ Hedge (1988) እና ሌሎች ስራዎችም በግልጽ ያሳያሉ (ከዚህ ሠፋ ላለ ማብራሪያና ለተጨማሪ ዋቢዎች በዚህ ስራ ርዕስ ቁጥር «(2.1.1.2»ን ይመለከቷል)::

### *4.1.4 በበሳል ድርሰት ኮርሶች ለተማሪ ጽሑፎች የመምህሩ ምላሽ*

በዚህ ጥናት በዓላማው ስር የተነሳው አንደኛው የምርምር ጥያቄ በበሳል ድርሰት ኮርሶች፣ «መምህራኑ ለተማሪዎች ድርሰት የሚሰጡት ምላሽ ባህርይ ምን ይመስላል?» የሚል ነው:: ይህው ጥያቄ በተመሳሳይ መልኩ በሌሎች ኮርሶችም ስር ተነስቷል:: ለዚህ ምክንያቱ በሁለቱ (በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች) ጎራ መሀከል ያለውን ምላሽ (እርማት) በንጽጽር በማየት፣ ልዩነት ካለው ተጣጥሞ የሚቀርብበትን መንገድ ለመጠቀም ነው:: ከዚህም በላይ፣ ጥናቱ

በተጓዳኝ አላማው፣ «የበሳል ድርሰት ትምህርት በምን መልክ በሌሎች ኮርሶች ለሚያስፈልጉ የጽህፈት ስራዎች ተማሪዎችን ማዘጋጀት ይችላል?» እና «ሌሎች ኮርሶችስ ለተማሪዎች ቀጣይ የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸው መዳበር ምን እና እንዴት ዓይነት አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ?» የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው:: እርማት ደግሞ ተማሪዎች በሚያደርጉት ክዋኔ ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ስለሚኖረው፣ ማናቸውም መምህር የሚሰጡት አስተያየት ተገቢነት ያለውና ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መዳበር የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንዲሆን በእያንዳንዱ ጎራ ስር ያለውን በራሱ መርምሮ ጥንካሬና ድክመቱን ማሳየት ያስፈልጋል:: ስለሆነም በበሳል ድርሰት ኮርሶች ለተማሪ ጽሁፎች ስለሚሰጠው ምላሽ ሠፊ ግንዛቤ ለማግኘት በርካታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል:: እነዚህ መረጃዎች፣ ከተማሪና ከመምህሩ ቃለመጠይቆች እና አስተያየት ከተሰጠባቸው በኋላ ከተሰበሰቡት ድርሰቶች የተገኙ ናቸው:: የነዚህን የመረጃ ውጤቶች ቀጥለን በተጓዳኝ እንመለከታለን::

ለተማሪዎች ድርሰት የመምህሩን ምላሽ ከማየታችን በፊት፣ ከመምህሩ ሌላ ተማሪዎች የራሳቸው ድርሰት ላይ (እርስ በእርስ በመለዋወጥ) እርማት ያደርጋሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማየቱ ተገቢ ይመስለናል:: ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመምህሩ ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚከተለውን ያሳየናል::

> አለዋውጬ ለማሳረም እስካሁን አንድ ጊዜ ሞክሬው፣ በ86 ይመስለኛል ውጤት አላመጣም:: እና አቀርረቡን ማሻሻል አለብኝ በማለት እስካሁን እንዲያርሙ አላደረግሁም:: ግን የማረሚያ ቁልፎችን በማዘጋጀትና አንዳንድ መመሪያዎችን፣ ሲያርሙ ምን ምን ነገሮችን መከተል እንዳለባቸው የሚያመለክቱ መንደርደሪያ ነጥቦችን በማዘጋጀት ወደፊት በዚያ መልክ ለማሠራት ዕቅድ አለኝ:: እሱን እያዘጋጀሁ ነኝ:: የብጤ እርማትን ( peer correction) ለማለማመድ ዕቅድ አለኝ::

ከዚህ መረጃ በበሳል ድርሰት ኮርሶች (በዚህ ጥናት በተጠኑት) የተማሪዎችን ድርሰት የሚያርሙት መምህሩ ብቻ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል:: ይህ ከሆነ፣ ምናልባት የጊዜ ጥበት ወይም የስራ ጫና ሊኖርባቸው ስለሚችል፣ መምህሩ ድርሰቶችን አርመው የሚመልሱት በምን ያህል የጊዜ ገደብ ነው? የሚል ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይመስለናል:: የመምህሩ ቃለመጠይቅ እንደሚያሳየን ከሆነ፣ ተማሪዎች ድርሰታቸውን ጽፈው ለመምህሩ ካስረከቡ በኋላ አስተያየት ተሰጥቶበት፣ከሳምንት ባልረዘመ ጊዜ እንደሚመለስላቸው ነው:: ይህ ጥያቄ የተነሳበት ምክንያት ተማሪዎች ለድርሰቶቻቸው የሚሰጣቸውን እርማት «ወዲያው» የማያገኙ ከሆነ (ማለትም የጻፉትን ጽሁፍ ከአእምሯቸው ካስወጡት በኋላ ከደረሳቸው)፣ እርማቱ ለመምህሩ ውጤት በመመዝገቢያነት ከማገልገል ባሻገር ለተማሪዎቹ፣ ለክሂላቸው መዳበር የሚጠቅማቸው ነገር እንደሌለ ጥናቶች ስለሚጠቁሙ ነው (በዚህ ጉዳይ ላይ ሠፊ ግንዛቤ ለማግኘት በእርማት ላይ

የተደረጉ በርካታ ጥናቶች በመቃኘት የቀረበውን የLeki 1990 ስራ ይመለከቷል):: ከዚህ ነጥብ አኳያ በበሳል ድርሰት ትምህርት መምህሩ የሚሰጡት እርማት ዘገየ ተብሎ የሚወቀስ አይመስለንም::

እርማት፣ ውጤት ከመመዝገቢያነት ባሻገር ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መዳበር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዳያበረክት ወይም እንዲያበረክት ከሚያደርጉት ነጥቦች አንዱ የሚያተኩርበት የጽሁፍ ገጽታ ነው:: በበሳል ድርሰት ትምህርትም «እርማት ሲያደርጉ ምን ላይ ነው ትኩረት የሚያደርጉት?» በሚል በመምህሩ ቃለመጠይቅ ላይ ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው መረጃም የሚከተለውን ያሳየናል::

> እንደድርሰቱ ዓላማ ነው፣ የቃላት አጠቃቀምን የሚመለከት አላማ ካለ፣ ከቃላት አጠቃቀም ላይ ትኩረት ይደረጋል:: ከዐረፍተ ነገር አወቃቀር ላይ ከሆነም እንደዚሁ ነው:: የሃሳብ አወራረድ፣ ተጠየቃዊ ዝምድና ከሆነም እንደዚያው ነው::

ከዚህ ጥቅስ መረዳት እንደምንችለው ከይዘት ይልቅ ቅርጽ ላይ እንደሚተኮር ነው:: ምክንያቱም ከላይ የልምምዶቹን ዓይነት ስንመለከት ልምምዱ ስለጽሁፍ (አጻጻፍ) የቀረቡ ዕውቀቶች (የጽሁፍ ሕግጋት፣ መዋቅሮች) ከመከወን አኳያ የሚደረግ በመሆኑ ነው፤ ማለትም የድርሰቱ ዓላማ እነዚህን ሕግጋትና መዋቅሮች ለማሳወቅ የሚደረግ በመሆኑ ነው:: ይሁን እንጂ፣ ይህ የመምህሩ አስተያየት፣ ከተጨባጭነት ይልቅ ስሜታዊ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ወይም መቶ በመቶ እዚህ ድምዳሜ ላይ የማያደርስ ሊሆን ይችላል:: እናም ትክክለኛውን ግንዛቤ ለመጨበጥ፣ በእርግጥ በመጀመሪያው ኮርስ (ELAm 203 ) የተደረገውን ብቻ አስመልክቶ ተማሪዎች ነጥብ-በነጥብ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል::

## ሰ ን ጠ ረ ዥ 3

በበሳል ድርሰት / ለተማሪዎች ጽሁፎች የመምህሩ የእርማት ትኩረት በመቶኛ (ብዛት=13)

| የጽሁፍ ገጽታዎች | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | ምንም |
|---|---|---|---|---|
| ሜካኒክስ (ስርዓተ ነጥብ፣ፊደል) | 23.08 | 30.77 | 30.77 | 15.39 |
| ሰዋሰው | 30.77 | 38.46 | 7.69 | 23.08 |
| ቃላት | 38.46 | 38.46 | 7.69 | 15.39 |
| አደረጃጀት | 30.77 | 46.15 | 0 | 23.08 |
| ይዘት | 30.77 | 30.77 | 15.39 | 23.08 |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደምንችለው ከፍተኛ ትኩረት ከሚደረግባቸው የጽሁፍ ገጽታዎች የመጀመሪያውን ደረጃ፣ 38.46% የያዘው በቃላት ላይ የሚደረገው እርማት ሲሆን ዝቅተኛው፣ 23.08% ደግሞ በሜካኒክስ ላይ የሚደረገው ነው:: በሌሎቹ፣ በይዘት፣ በአደረጃጀትና ሰዋሰው ላይ ትኩረቱ እኩል ነው:: ይዘት፣ ባጠቃላይ ከሌሎቹ የጽሁፍ ገጽታዎች፣ ማለትም በቅርጽ ላይ ከሚያተኩሩት፣ አንጻር ሲታይ ደግሞ በከፍተኛነት ደረጃ የተሰጠው ትኩረት 30.77% ይሆናል:: ይህ መረጃ የሚያሳየን ከላይ ከመምህሩ ቃለመጠይቅ ባገኘነው መረጃ እና ተማሪው ለድርሰቴ አገኛለሁ ባለው የእርማት ትኩረት መሀከል ልዩነት አለመኖሩን ነው:: ከዚሁ በተጓዳኝ በተሰበሰቡት ጽሁፎች ላይ የሚታየው የመምህራኑ የጽሁፍ እርማት የሚከተለውን ውጤት ያሳያል (ሰንጠረዥ አራትን ይመልከቷል)::

### ሰ ን ጠ ረ ዥ 4

በበሳል ድርሰት ኮርሶች ለተማሪ ጽሑፎች የመምህራኑ የጽሁፍ እርማት ትኩረት በመቶኛ (ብ = 123)

| የ ጽ ሁ ፍ ገ ጽ ታ | የ ጽ ሁ ፍ እ ር ማ ቱ ት ኩ ረ ት | | |
|---|---|---|---|
| | ELAm 203 (የድርሰት ብዛት=57) | ELAm 204 (የድርሰት ብዛት=66) | ELAm 203 & ELAm 204 (የድርሰት ብዛት=123) |
| ሜካኒክስ (ስትዓተ-ነጥብ፣ ፊደል) | 14.85 | 38.02 | 27.48 |
| ሰዋሰው | 19.80 | 13.22 | 16.22 |
| ቃላት | 20.79 | 18.18 | 19.37 |
| አደረጃደት | 26.73 | 23.97 | 25.23 |
| ይዘት | 17.81 | 6.61 | 11.71 |
| ድ ም ር | 100.00 | 100.00 | 100.00 |

ከዚህ ሰንጠረዥ እንደምንረዳው በተማሪዎች ጽሁፎች ላይ የመምህሩ የጽሁፍ እርማት ትኩረት ከፍተኛው(27.48%) ሜካኒክስን በተመለከተ ሲሆን፣ ዝቅተኛው ደግሞ (11.71%) ይዘትን በተመለከተ የተደረገው ነው:: ይህ ውጤትም ከላይ ከመምህሩና ከተማሪው ቃለመጠይቅ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ «ከይዘት ይልቅ እርማቱ ቅርጽ ላይ ያተኩራል» ያልነውን የሚያጠናክር ነው:: በሌላው መልኩ፣ አደረጃጀት በሁለተኛነት ከፍተኛውን ደረጃ ቢይዝም (25.23%)፣ እርማቱ በዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎት ላይ ማተኮሩን ሊለውጠው አልቻለም::በሠንጠረዡ እንደተመለከተው በዝቅተኛ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ያተኮሩት እርማቶች

ከአጠቃላይ እርማቱ አንጻር፣ 63.07% ሲሆኑ በከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ያተኮሩት 36.94% ናቸው::

ከላይ፣ በሰንጠረዥ ሦስት የመጀመሪያውን ኮርስ (ELAm 203) አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ ይዘት ከሌሎች የጽሁፍ ገጽታዎች ወይም ከቅርጽ አንጻር ሰታይ በከፊተናነት ደረጃ የተሰጠው ትኩረት 30.77% እንደሆነ ተመልክተናል:: በዚሁ ኮርስ (ELAm 203) የተሰበሰቡት ድርሰቶች ላይ የተሰጠው የጽሁፍ እርማትም ከቅርጽ አንጻር ሲታይ፣ ይዘት 17.81% ይሆናል:: ይህ የሚያሳየን በELAm 203 ኮርስ የመምህርሩ እርማት ትኩረት በከፍተኛ ደረጃ በቅርጽ ላይ እንደሆነ ነው:: ባጠቃላይም በሚቀጥለው ኮርስ (ELAm 204) እና ሁለቱም ኮርሶች በአንድነት ሲታዩ፣ ትኩረቱ፣ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው፣ ከይዘት ይልቅ ቅርጽ፣ በተጨማሪም ከከፍተኛ የጽሁፍ ገጽታዎች ይልቅ በዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ነው::

የመስኩ ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ በዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚደረግ እርማት ለተማሪዎች ዘላቂ የመጻፍ ክሂላቸው መዳበር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እጅግ ደካማ ነው:: እርማት ጽሁፍን ገምግሞ ውጤት ከመስጠት ባሻገር ለተማሪው ጠቃሚ እንዲሆን ካስፈለገ፣ ከዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ማተኮር አለበት:: ይሁን እንጂ፣ ከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ ማተኮሩ ብቻውን ለመጻፍ ክሂል መዳበር በቂ ነው ሊባል የሚችል አይደለም:: ለመጻፍ ክሂል መዳበር አጋዥና ጠቃሚ የሚሆነው በነዚህ ገጽታዎች (ከፍተኛ የጽሁፍ ገጽታዎች) ላይ ማተኮሩ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹ በእርማቶቹ ተጠቅመው አስተካክለው መጻፍ ሲችሉ ነው:: እርማት ጠቃሚ እንዲሆን ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ እርማቱ በመጨረሻው ድርሰት ላይ ሳይሆን በረቂቆቹ ላይ ሲደረግ ነው:: እርማቱ በመጨረሻው ድርሰት ላይ ብቻ የሚደረግ ከሆነ፣ ተማሪዎች ከእርማቱ እንዴትነት ይልቅ ትኩረታቸው በውጤታቸው ላይ ስለሚሆን ትኩረት አያደርጉበትም (በዚህ ጉዳይ ላይ Chimombo 1986:20 ይመለከቷል):: ትኩረት ሰጥተውት ቢመለከቱትም፣ አስገዳጅ ሁኔታ ስለሌለ (ምክንያቱም ያ ድርሰት መልሶ ስለማይታረም) እርማቱን በመጠቀም ከልሰው ለመጻፍ አይነሳሱም:: ስህተታቸውን አስወግደው ከልሰው ለመጻፍ ካልሞከሩ ደግሞ እርማቱ ጠቃሚ ነው ለማለት እንደማያስደፍር ጥናቶች ይጠቁማሉ (ለምሳሌ Raimes 1983:139፣ Hedge 1988:145 በዚህ ጉዳይ ላይ ይመለከቷል)::

ከነዚህ ነጥቦች አንጻር፣ በዚህ ርዕሳችን በድርሰት ኮርሶች መምህሩ የሚሰጡትን እርማት ስንገመግመው፣ በጠቃሚነቱ ረገድ ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አናገኘውም:: ይህም ከከፍተኛ የጽሁፍ ገጽታዎች ይልቅ በዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ በማተኮሩ ብቻ ሳይሆን እርማቱ የሚደረገው በአብዛኛው የመጨረሻው ረቂቅ (ድርሰት) ላይ በመሆኑም ነው:: ከላይ በርዕስ ቁጥር 4.1.3 ስር እንደተመለከትነው የክለሳ ሂደት የሚደረግባቸው ጽሁፎች 20% ብቻ ናቸው:: በአብዛኛው በድርሰት ኮርሶች ከሂደት ተኮር ስለተ ትውር ይልቅ ውጤት ተኮር ስልተ ትውር ይዘወተራል:: ስለዚህም እርማቱ ከሂደት ይልቅ በመጨረሻው ውጤት ላይ ብቻ ይሰጣል::

## 4.2 በሳል ድርሰት ባልሆኑ ኮርሶች የጽህፈት ስራዎች

### 4.2.1 የጽህፈት ስራዎቹ ዓይነት፣ ምደባና ገለጻ

ከበሳል ድርሰት I እና ከበሳል ድርሰት II ውጭ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል አማርኛ አቢይ ትምህርታቸው የሆነ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚወስዷቸው ኮርሶች የሚከውኗቸው የጽህፈት ስራዎችን (ከመምህሩ መጠይቅ፣ ከተማሪው ቃለመጠይቅ እና ከስብስብ የጽህፈት ስራዎች በተገኘው መረጃ መሠረት) በሰባት አቤይት ክፍሎች ከፍለናቸዋል:: እነዚህም የፈተና መልስ ጽሁፎች፣ ሂሳዊ ጽሁፎች፣ ሪፖርቶች፣ የምርምር ጽሁፎች፣ የትርጉም ጽሁፎች፣ የተማሪ ማስታወሻዎች እና የዲግሪ ሟሟያ ጽሁፎች ናቸው::

1 . የፈተና መልስ ጽሁፎች

የፈተና መልስ ጽሁፎች ተማሪዎች በጽሁፍ መልስ ለሚሹ ጥያቄዎች በፈተና ወቅት የሚጽፏቸው ናቸው:: እነዚህ ጽሁፎች ፍጹም በጊዜ የተገደቡ ከመሆናቸው የተነሳ፣ ተማሪዎች ረቂቅ የመንደፍ፣ ክልሶ የመጻፍና አርትኦት የማድረግ ሰፊ ጊዜ አይኖራቸውም:: ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን፣ ለትምህርቱ አጋዥ ይሆናሉ ተብለው የተሰጧቸውን መርጃ መሳሪያዎች አንብበው ያገኙትንና ባጠቃላይ፣ በኮርሱ ስምምነት የተደረሰባቸውን እውቀቶች መገንዘባቸውን ለማሳየት ዋና ዋና ነጥቦችን በጥያቄዎቹ መሠረት የሚጽፉባቸው ናቸው:: ልዩ ባህሪያቸው፣ ግላዊ ስሜትና ገጠመኝ በነዚህ ዓይነት ጽሁፎች ቦታ አለመኖሩ ነው::

የፈተና መልስ ጽሁፎች አጭር መልስ የሚሰጥባቸው፣ በመስመር የተገደቡ፣ ወይም ሠፊ ማብራሪያ የሚቀርብባቸው በመስመር ያልተገደቡ ሊሆኑ ይችላሉ:: ባብዛኛው ሰፊ ማብራሪያ

የሚቀርብባቸው የፈተና ጽሁፎች በስነጽሁፍ ኮርስ የሚገኙ ናቸው፡፡ በሌላው መልኩ፣ በማናቸውም ኮርሶች ቢሆን፣ የጥያቄዎቹ አመላለስ እና ባጠቃላይ ተማሪዎች ሊያነሷቸው ወይም ሊገልጿቸው የሚገቡ ነገሮች በግልጽ በጥያቄው እና/ወይም በትዕዛዙ ላይ ይጠቆማሉ፡፡ ተማሪው በተቻለ መጠን ማናቸውንም ነገር በአእምሮው አስታውሶ እንዲጽፍ ይጠበቃል፡፡ ለትክክለኛ መረጃ ምንጫቸውን ወይም ማስታወሻ የወሰደባቸውን ደብተሮች ወይም ወረቀቶች ማየት አይፈቀድለትም፡፡

እንዲህ ዓይነት ጽሁፎች፣ ባጠቃላይ በግል የሚከወኑና፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርነው በጊዜ የተገደቡ በክፍል ውስጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከአጠቃላይ የጽህፈት ስራዎቹ አንጻር ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት፣ በሌላ አነጋገር፣ በተደጋጋሚ ተማሪዎች የሚከውኗቸው (በየኮርሶቹ ከሚከውኗቸው ማስታወሻዎች ውጭ) እነዚህ ጽሁፎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጽሁፎች ከሁለት ኮርሶች (ELAm 407 እና ELAm 408 በስተቀር) በሁሉም ኮርሶች ቢያንስ ለአንድ ጊዜ ይከወናሉ፡፡ በአንድ ፈተና የሚከወኑት በቁጥር ይህን ያህል ናቸው ብሎ በሁሉ ኮርሶች ላሉ ፈተናዎች የሚሰራ መረጃ መስጠት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ከኮርስ ኮርስ ብቻ መለያየታቸው ሳይሆን ከፈተና ፈተና እንደዓላማውና እንደጊዜው የሚለያዩ በመሆናቸው ነው፡፡

2 . ሂሳዊ ጽሁፎች

እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በአንድ የፈጠራ ስራ ላይ አንድን የስነጽሁፍ አላባ ወይም እሳቤ (element or concept) በመያዝ ሂስ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ በነዚህ ጽሁፎች መምህሩ ተማሪዎች የሚሰሩበትን መጽሀፍ ወይም ጽሁፍና ሂስ የሚያቀርቡበትን ነጥብ ወይም ርዕስ ይመርጣል፣ ወይም ባብዛኛው መምህሩ ዓይነቱን ከነገር በኋላ ተማሪው ይመርጥና መምህሩ ተማሪው የመረጠውን መርምሮ ያጸድቃል፡፡ እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች ሙለ በሙሉ የሚከወኑት ከተጻፈ ጽሁፍ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ አስተያየት ወይም ሂስ ለመስጠት ተማሪዎች፣ በርዕሳቸው ያነሱትን ነጥብ ባጠቃላይ በጽሁፋቸው ውስጥ ትኩረት ሰጥተው ተንትነው ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለሚሠነዝሯቸው አስተያየቶች ትውራዊ መሠረት በማስያዝ መረጃ አጣቅሰው ለማቅረብ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በነዚህ ዓይነት ጽሁፎች ግላዊ ስሜትና ዝንባሌ አንዳንድ ጊዜ ይንጸባረቅባቸዋል፡፡

ሂሳዊ ጽሁፎች በግልም በቡድንም የሚከወኑ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ጽሁፎች መሀከል በገጽ የሚገደቡና የማይገደቡም አሉ፡፡ ሁሉም ከሳምንት ያላነሰ ጊዜ በመውሰድ ከክፍል ውጭ የሚሰሩ

በመሆናቸው አስተያየቱ ወይም ሂሱ የሚሰጥበትን ስራ ደጋግመው የማንበብ፣ በሚሰሩበት ርዕስ ላይ በቂ ወይም ጠቃሚ ግንዛቤ ለማግኘት የተለያዩ መረጃዎችን ለማገላበጥ፣ የጻፉትን ለመከለስ እና አርትኦት ለማድረግ ጊዜ ይኖራቸዋል::

እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በሦስተኛ ዓመት ደረጃ በሚሰጡ የስነጽሁፍ ኮርሶች ( ELAm 301፣ ELAm 302 እና ELAm 304) የሚከወኑ ናቸው:: በመጀመሪያው ሴሚስተር በELAm 301 ሁለት (አንደኛው፣ ሁለት ሁለት በመሆን ከ3 - 5 ገጽ፣ ሁለተኛው፣ በግል የገጽ ገደብ የሌለው) ጽሁፎች የተከወኑ ሲሆን፣ በሁለተኛው ሴሚስተር በELAm 304 በግል የሚከወን አንድ ጽሁፍ፣ በ LAm 302 እንዲሁ በግል የሚከወን አንድ ጽሁፍ እንዳሉ ከመምህራኑ መረጃ ተገኝቷል::

3 . የሪፖርት ጽሁፎች

ሪፖርት (ወይም «ዘገባ») አጻጻፍን አስመልክቶ በሁለተኛ ዓመት ደረጃ «መምህራን ላልሆኑ» ተማሪዎች በሚሰጠው ኮርስ (ELAm 202) ትውራዊ ገለጻ ከቀረበ በኋላ ተማሪዎች ባብዛኛው አንድ የሪፖርት ጽሁፍ እንደሚጽፉ ቢደረግም፣ ይህ ጥናት በተመለከተበት ዓመት (1988) ይህ ላለመደረጉ መረጃ ተገኝቷል:: በመሆኑም በዚህ ጎራ የመደብናቸው ጽሁፎች ባህሪን ስንተነትን፣ በዚህ ኮርስ በሌሎች ጊዜያት የተከወኑትን ወይም ወደፊት የሚከወኑትን ጽሁፎች፣ ባህሪ ሳንጨምር ነው::

በዚህ ጎራ ስር የተመደቡት ጽሁፎች ልዩ ባህርያቸው በአንድ አካባቢ ስለተከወኑ ድርጊቶች (ሁነቶች) የሚዘግቡ ወይም አንድን ነገር ሰምቶ፣ አይቶ ወይም አንብቦ ራስን ወይም ሌላን መረጃ በማድረግ ምንጭ ጠቅሶ ለተደራሲ «እንዲህ እንዲህ ሆነ ወይም ተደረገ» በማለት የሚጻፉ መሆኑ ነው:: እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በተደራሲው አእምሮ ውስጥ ፈጣን ግንዛቤን ለመፍጠር የሚጻፉ ናቸው:: ተደራሲው ሳያሰላስልና በእያንዳንዳቸው ነጥቦች ላይ ብዙ ሳይመራመር ተፈላጊው መልዕክት እንዲደርሰው ለማድረግ የሚጻፉ በመሆናቸው ከጽሁፍ ቋንቋነት ወደ ንግግር ቋንቋነት ያደላሉ፤ ከቅርጽ ይልቅ መልዕክት ላይ ያተኩራሉ:: ይሁን እንጂ፣ ተደራሲው መልዕክቱ ወዲያው እንዲደርሰው ቅርጹ አሻሚና አደናጋሪ ወይም አመራማሪ እንዳይሆን ከፍተኛ ትኩረት ይደርጋል:: እነዚህ ጽሁፎች በወትሯዊ ቃላት፣ በአጫጭር እና ተራ ዐረፍተ ነገሮች የሚጻፉ ናቸው::

ከሌሎች የጽህፈት ስራዎች አንጻር በጣም ትንሹን የሚይዙ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህን ጽሁፎች የሚከውኑት ከመምህርነት ሙያ ውጭ ለሌሎች ሙያዎች የሚሰለጥኑ ተማሪዎች ብቻ ናቸው:: እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በሦስተኛ ዓመት ደረጃ «መምህራን ያልሆኑ» ተማሪዎች በሁለት ኮርሶች (ELAm 309 እና ELAm 310) የሚከውኗቸው ናቸው:: በዚህ ዓመት (1988)፣ በመጀመሪያው ሴሚስተር፣ በ ELAm 309 ተማሪዎቹ አንድ ጾሐፍ ያከናወኑ ሲሆን፣ በሁለተኛው ሴሚስትር በELAm 310 (ይህ መረጃ ለመጨረሽ ጊዜ እስከተጠናቀረበት ሚያዚያ 25 ድረስ) አንድ በማከናወን ላይ ናቸው:: እነዚህ ሁለቱም ጽሁፎች ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ናቸው::

4 . የምርምር ጽሁፎች

በዚህ ጎራ ውስጥ የተመደቡ ጽሁፎች ሁለት ዓይነት ናቸው:: እነዚህም ከመጀመሪያ ምንጭ ላይ በመመስረት የሚደረጉ የምርምር ጽሁፎችና ከሁለተኛ ምንጭ ላይ በመመስረት የሚደረጉ የምርምር ጽሁፎች ናቸው::

የመጀመሪያው ዓይነት ጽሁፎች (ከመጀመሪያ ምንጭ ላይ የሚደረጉ ጽሁፎች) ጥሬ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን የሚጻፉ ናቸው:: ትንታኔው የሚደረገው በርዕሱ ዙሪያ የተደረጉ ስራዎችን በማጣቀስና ትውራዊ መሠረት በማስያዝ ነው:: ተማሪዎች ለእነዚህ ዓይነት ጽሁፎች የሚሰበስቧቸው ጥሬ መረጃዎች ውስን ናቸው ማለት ይቻላል:: ምክንያቱም ጊዜና ኢኮኖሚ ስለሚገድቧቸው ሠፋና ላቅ ያሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን አይጠቀሙም:: እነዚህ መረጃዎች ከራስ በማመንጨት፣ አልፎ አልፎም ከሌላ አንድ ወይም ሁለት ሰው በመጠየቅ የሚሰበሰቡ ናቸው:: እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች «በአማርኛ ስነመዋቅር» (ELAm 307) ሁለት፣ አንደኛው በግል፣ ሌላኛው በቡድን፣ «በምርምርና 'ዘገባ' አጻጻፍ» (ELAm 202) አንድ ተከናውነዋል::

ሁለተኛው ዓይነት የምርምር ጽሁፎች (ከሁለተኛ ምንጭ ላይ በመመስረት የሚደረጉት) ከተለያዩ መጻህፍት፣ ትምህርታዊ መጽሄቶች፣ ጋዜጦች፣ ባጠቃላይ ከተለያዩ ጽሁፎች፣ተማሪዎች ባብዛኛው መምህሩ በመረጡላቸው ርዕስ ዙሪያ አንብበውና መረጃ አሰባስበው የሚጽፉባቸው ናቸው:: እነዚህ አይነት ጽሁፎች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙትን መረጃዎች በከፍተኛ ደረጃ ማዋቀርና ማደራጀትትን መጠየቃቸው ልዩ ባህርያቸው ነው:: እነዚህ ጽሁፎች በተለያዩ ኮርሶች የሚከወኑ ናቸው:: በELAm 402 አንድ፣ በELAm 310 አንድ፣ በELAm 305 አንድ በድምሩ ሦስት ጽሁፎች እንደተከወኑ መረጃ ተገኝቷል::

በአጠቃላይ በዚህ ጎራ ውስጥ የተመደቡት ጽሁፎች ልዩ ባህርያቸው በውስጣቸው ግላዊ ስሜትና ዝንባሌ ምንም ስፍራ የሌለው መሆኑ ነው። በምርምሩ የሚደረስበት መደምደሚያ ከመረጃዎቹ ውጤት ላይ የተመሠረተ እንጂ ከግል ስሜት የሚነሳ አይደለም። በሌላ አነጋገር በምርምርሩ የተነሱት ጥያቄዎች የሚመለሱት ወይም ምላሽ የሚያገኙት የተሰበሰቡት መረጃዎች ከሚሰጡት ውጤት እንጂ ከግል ዝንባሌ፣ ስሜትና አመለካከት አይደለም። እነዚህ ጽሁፎች ሁሉም ከክፍል ውጭ የሚከወኑ ናቸው።

5 . የትርጉም ጽሁፎች

በዚህ ጎራ ውስጥ የተመደቡት ጽሁፎች ባጠቃላይ በትርጉም ኮርሶች (ELAm 403 እና ELAm 404) የሚከወኑ ብቻ ናቸው። እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በቀጥታ ከእንግሊዝኛው ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ ተተርጉመው የሚቀርቡ ናቸው። ከራስ ግንዛቤ በመነሳት ወይም መረጃዎችን በማጣቀስ ሠፊ ማብራሪያ የሚቀርብባቸው አይደሉም። በነዚህ ዓይነት ጽሁፎች በእንግሊዝኛ የቀረበውን ጽሁፍ መልዕክት በአማርኛ ቋንቋ ሳያዛቡ ማስተላለፍ ይጠበቃል። በነዚህ ጽሁፎች፣ መልዕክቱ ከመገኛው ቋንቋ ሳይዛባ መተላለፉ ላይ፣ እና በአንጻሩም የተቀባዩን ቋንቋ ስርዓት ጠብቆ መጻፍ ላይ እጅግ ይተኮራል።

6 . የክፍል ውስጥ የተማሪ ማስታወሻዎች

እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች ከELAm 407 እና ELAm 408 በስተቀር በሁሉም ኮርሶች የሚከወኑ ናቸው። እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች መምህሩ በቃል ገለጻ ሲያደርጉ ተማሪዎች ማስታወሻ በወረቀት ወይም በደብተር ላይ የሚወስድባቸው ናቸው።

7 . የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች

የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች በክፍሉ የአራተኛ ዓመት ተማሪዎች በአማርኛ «ባችለር ኦቭ አርትስ» ለማግኘት በማሟያነት የሚጽፏቸው ናቸው። እነዚህ ጽሁፎች ከላይ ካየናቸው ጽሁፎች (በተለይ ከቁጥር 2 እና 4) የሚለዩበት ዋናው ነገር ረጅም ጊዜ ወስደው የሚጻፉ በመሆናቸውና ተማሪዎችም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስረክቧቸው፣ በዚያው መሠረት ብቻ የመጨረሻ ውጤት የሚሰጥባቸው ባለመሆናቸው ነው። ይህም ተማሪዎች ርዕስ ከመረጡ በኋላ ለጽሁፋቸው ክንውን አማካሪ ይመደብላቸዋል። ተማሪዎቹም ከርዕስ ማስተካከል እስከ መጨረሻው ውጤት (ጽሁፍ) ድረስ ከአማካሪያቸው ጋር ነጥብ በነጥብ ይሠራሉ። ረቂቃቸውን በየጊዜው እያቀረቡ አማካሪያቸው ከዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች እስከ ከፍተኛ ደረጃ

የጽሁፍ ገጽታዎች ባሉ ስህተቶች ላይ አስተያየት እየሰጣቸው ደጋግመውና ከላለልስው ይጽፋሉ:: ከዚህም በላይ እነዚህን ጽሁፎች የሚመለከቱ ሁለት ኮርሶች (ELAm 407 እና ELAm 408) አሉ:: በነዚህ ኮርሶች ተማሪዎች የሚሰሩበትን ርዕስ አማካሪዎቻቸው እና የክፍሉ ተማሪዎች በተገኙበት ያቀርባሉ:: በዚህም ከተሳታፊዎች ከሚነሱት ጥያቄዎችና ከሚሰጧቸው አስተያየቶች ለጽሁፋቸው ጠቃሚ የሆኑትን የመውሰድ ዕድል ያጋጥማቸዋል:: ይህ ከላይ ካየናቸው ከሌሎቹ ጽሁፎች (በተለይ ከምርምር ጽሁፎችና አንዳንዴም ከሂሳዊ ጽሁፎች) መለያ ባህርያቸው ነው::

እነዚህ ዓይነት ጽሁፎች የሚሰሩበት የትምህርት መስክ ስነጽሁፍ (ስነቃልን ጨምሮ)፣ ስነልሣን፣ ቋንቋን ማስተማር፣ ስነትርጉም ወይም ከጋዜጠኝነት ሙያ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል የተገኘው መረጃ ተማሪዎች ርዕሳቸውን ሊያስተካክሉ ወይም ሊለውጡ እንደሚችሉ ያሳያሉ:: ስለዚህም በዚህ ዓመት(1988 ዓ.ም) የተማሪዎች ርዕሶች የሚያተኩሩባቸው የትምህርት መስኮች «እነዚህ፣ እነዚህ» ናቸው ብሎ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አልተቻለም:: ተመሳሳይ ግንዛቤ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ በ1987 ዓ.ም. ተማሪዎች የሠሯቸው ዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች አርዕስት በአባሪ «ሠ» ቀርቧል::

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁጽ ክፍል፣ አማርኛን አቢይ ትምህርት ያደረጉ ተማሪዎች፣ በአማርኛ ቋንቋ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ በሌሎች ኮርሶች የሚከውኗቸው የጽህፈት ስራዎች ዋናዎቹ አይነቶች ከላይ ያየናቸው ናቸው:: ከነዚህ የጽህፈት ስራዎች ሌላ በELAm 406 የሚከወን የፈጠራ ጽሁፍ አለ:: ኮርሱን ከሚወስዱት ተማሪዎች እንደተገኘው መረጃ፣ በዚህ ሴሚስተር (1988 ዓ.ም 2ኛ ሴሚስተር) በሚያዚያ ወር አንድ አጭር ልብወለድ ከክፍል ውጭ በግል ተማሪዎች በማከናወን ላይ ይገኛሉ:: በዚህ ኮርስ (ELAm 406) ከሚያከናውኑት የፈጠራ ጽሁፍ ውጭ፣ በአጠቃላይ ማለት ይቻላል፣ ተማሪዎች ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች በአማርኛ የሚጽፏቸው የጽህፈት ስራዎች ከግል ገጠመኝ ወይም ስሜት ላይ በመነሳት የሚከወኑ አይደሉም::

### 4.2.2 የጽህፈት ስራዎቹ አስፈላጊነት

ከበሳል ድርሰት ኮርስ ውጭ በሌሎች ኮርሶች የተለያዩ የጽህፈት ስራዎች እንደሚከወኑ በላይኛው ርዕስ ስር ተመልክተናል:: ለመሆኑ፣ እነዚህ የጽህፈት ስራዎች አስፈላጊነታቸው

ምንድን ነው? የጽሁፍ ክሂል በነዚህ ኮርሶች አስፈላጊነቱ ምን ያህል ነው? የትኞቹ የጽሁፍ ክሂሎችስ አስፈላጊ ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመልከቱ ተገቢ ይመስለናል።

የመምህራን መጠይቅ ቁጥር ስምንት፣ መምህራኑ ለተማሪዎቻቸው የጽህፈት ስራዎችን የሚሰጡበትን ምክንያት ይጠይቃል። ለዚህ ጥያቄ ከመምህራኑ የተገኙት መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው። እነዚህም፣

- የኮርሱ ግዴታ ወይም መሠረታዊ አካል በመሆኑ፣
- የተሰጣቸውን የቃል ትምህርት በተግባር ማዋል መቻላቸውን ለማረጋገጥ፣
- ከኮርሱ ያገኙትን እውቀት በስፋት ለመገምገም ወዘተ. የሚሉ ናቸው።

በመምህሩ መጠይቅ በተራ ቁጥር 9 ላይ የቀረበው ጥያቄ የጽሁፍ ክሂል በነዚህ ኮርሶች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ጥያቄ መጠይቁን የሞሉት ሁሉም መምህራን ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ የተገኘው መረጃም የሚከተለው ነው።

*ሰ ን ጠ ረ ዥ 5*

ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች የጽህፈት ክሂል አስፈላጊነት በመቶኛ

| እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው | በጣም አስፈላጊ ነው | አስፈላጊ ነው | አስፈላጊ አይደለም |
|---|---|---|---|
| 66.67 | 16.67 | 16.67 | 0 |

ከሰንጠረዡ የምንረዳው፣ የጽህፈት ስራዎች የኮርሶች መሠረታዊ አካል እስከመሆን በመድረስ አስፈላጊ እንደሆኑ ሁሉ፣ የጽህፈት ክሂልም እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ነው።

ከመምህሩ መጠይቅ ውጭ የተማሪው መጠይቅ በነዚህ የጽህፈት ስራዎች (ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው) ውስጥ አስፈላጊ የሆኑት የጽሁፍ ክሂሎች የትኞቹ እንደሆኑ በደረጃ ይጠይቃል። ከዚህ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በሠንጠረዥ ስድስት ቀርቧል። በዚህ ሠንጠረዥ ከፍተኛ በሚል የቀረበው በመጠይቁ «እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው» እና «በጣም አስፈላጊ ነው» የሚሉትን አማራጮች በአንድ በማካተት ነው። ዝቅተኛ የሚለው ደግሞ ፣ «በዝቅተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው» እና «ፈጽሞ አያስፈልግም» በሚል በመጠይቁ የቀረቡትን አማራጮች የሚያካትት ሲሆን፣ መሀከለኛ የሚለው «አስፈላጊ ነው» በሚል በመጠይቁ የቀረበውን አማራጭ የሚወክል ነው።

## *ሰ ን ጠ ረ ዥ 6*

የጽሁፍ ክሂሎች አስፈላጊነት ደረጃ (ብዛት = 41)

| *የጽሁፍ ክሂሎች (ገጽታዎች)* | *አ ስ ፈ ላ ጊ ነ ት %* | | |
|---|---|---|---|
| | *ከፍተኛ (1-2)* | *መሀከለኛ(3)* | *ዝቅተኛ(4-5)* |
| ሃሳብን በተጠየቃዊና በተቀናበረ መልኩ ማቅረብ | 92.68 | 4.88 | 2.44 |
| ተጠየቃዊ ግንኙነትን በዐረፍተ ነገሮች በአንቀጾችና በምዕራፎች መሀከል መፍጠር | 58.54 | 21.95 | 19.51 |
| መረጃን መተንተን | 68.29 | 21.95 | 9.76 |
| ሃሳብን በሌሎች ድርሳኖች ወይም ምርምሮች ማጎልበት | 75.61 | 24.39 | 7.32 |
| የሰዋሰውና በዐረፍተ ነገር መዋቅር ጥራት | 92.68 | 7.32 | 0 |
| ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም | 92.68 | 7.51 | 4.88 |
| ስርአተ ነጥብና ፊደል አስተካክሎ መጻፍ | 65.86 | 14.63 | 19.51 |
| ቢጋር መንደፍ | 78.05 | 19.51 | 2.44 |
| ለየነጥቦቹ እንደአስፈላጊነታቸው ተገቢውን አጽንኦት መስጠት | 56.10 | 26.83 | 17.07 |
| የመጻፍ ፍጥነት | 34.15 | 31.71 | 34.15 |
| ንድፍና ክለሳ ማድረግ | 56.10 | 34.15 | 9.76 |
| አርትኦት ማድረግ | 34.15 | 51.22 | 14.63 |
| ጥሩ ማጠቃለያ ማቅረብ | 78.05 | 29.51 | 2.44 |
| መረጃን በተገቢው ቦታ መጥቀስና መሰነድ (ምንጩን ማመልከት) | 73.17 | 24.39 | 2.44 |
| ማሳጠር | 51.22 | 26.83 | 21.95 |
| ማስፋፋት | 58.54 | 24.39 | 17.07 |
| ውስብስብ ሃሳቦችን በተገቢው ጥራት መግለጽ | 80.49 | 17.07 | 2.44 |

በዚህ ሠንጠረዥ ላይ እንደምንመለከተው ለአብዘኞቹ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ አስፈላጊ ያልሆኑት የጽሁፍ ክሂሎች የመጻፍ ፍጥነትና አርትኦት ማድረግ ናቸው። ሁለቱም 34.15 ተማሪዎች ብቻ ናቸው። የመጻፍ ፍጥነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሚከወኑ፣ በተለይ በፈተና ወቅት ለሚጻፉ ጽሁፎች አስፈላጊ ክሂል ነው። ከላይ የጽህፈት አይነቶችን በምንመለከትበት ወቅት እንደዚህ ዓይነት ጽሁፎች ተማሪዎች እንደሚከወኑ አይተናል። ይህ የሚያሳየን አብዛኞቹ ተማሪዎች በፈተና ወቅት ተገቢውን ጥራት ጠብቀው ለመጻፍ በቂ ጊዜ እንዳላቸው ፣ አሊያም ጽሁፋቸው የፈለገውን የጥራት ደረጃ ይያዝ ዋናው ትኩረት ይዘት ላይ ብቻ እንደሚደረግ ነው። በሌላ በኩል «አርትኦት ማድረግ» የሚለውም በአብዛኞቹ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው ተብሎ አልተመረጠም። ይሁን እንጂ፣ የዚህ መረጃ እውነትነት በሌሎች ጥያቄዎች ሲመረመር አጠራጣሪ ይሆናል። አርትኦት የሚደረገው በተለይ አፍአዊ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች (surface level writing features) ላይ በመሆኑ በማናቸውም ጽሁፎች ቢሆን የዚህ ዓይነቱ ስራ አስፈላጊ ነው። በመጠይቁም ላይ ለሰዋሰውና ለስርዓተ ነጥብ የተሰጣቸው የከፍተኛነት ደረጃ በ65.86% እና በ75.61% ተማሪዎች ነው። ይህ የሚያሳየን ተማሪዎች አርትኦት ከማድረግ ወይም ከመጻፍ ሂደት ላይ ከማተኮር ይልቅ የመጀመሪያው ስራቸውን (ረቂቃቸውን) ተጠንቅቀው እንደሚጽፉ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ተማሪዎች ቀድመው በወሰዷቸው የጽሁፍ ስልጠናዎች የአርትኦት አስፈላጊነት ካለመገንዘባቸው የመጣ ነው ለማለት ያስችላል።

### 4.2.3 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮችና ጽሁፎቻቸው ውስጥ የሚታዩ ድክመቶች

#### 4.2.3.1 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮች

ከላይ የጽህፈት ስራዎቹን በየጎራው መድበን ስንተነትን በቡድን የሚከወኑ ስራዎች እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ ከተማሪዎች መጠይቅም የተገኘው መረጃ በመጀመሪያው ሴሚስተር ከአጠቃላይ ስራዎቹ አንጻር 20.2% በቡድን የሚከወኑ ስራዎች እንደሆኑ ያሳያል፡፡ በዚህ መጠይቅ ተማሪው በቡድን በማከናወን ያጋጠመው ችግር እንዳለ ተጠይቆ 86.18% ችግር መኖሩን ገልጿል፡፡ የመጠይቁ ቁጥር 22 ጥያቄ ተማሪዎች ያጋጠማቸውን ችግር በጽሁፍ እንዲገልጹ የሚጠይቅ ነበር፡፡ ከዚህ ጥያቄ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየን፣ ተማሪዎች በቡድን የጽህፈት ስራዎችን ለመከወን በጋራ ለመሰብሰብ ተስማሚ ጊዜ ያለማግኘት ፣ እርስ በእርስ በሃሳብ አለመጣጣም እና ሁሉም የቡድኑ አባላት ለቡድኑ ስራ እኩል ፍላጎት የሌላቸው መሆኑ ዋንኛዎቹ ችግሮች ናቸው፡፡ (ለዝርዝሩ አባሪ «ሸ»ን ይመለከቷል፡፡)

#### 4.2.3.2 በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶች

የመምህር መጠይቅ ቁጥር 11 እና 12 ለተማሪዎች አስቸጋሪ የሆኑባቸውን የጽሁፍ ስራዎችና ምክንያቶቻቸውን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ የመጠይቁ መረጃ እንደሚያሳየን በትርጉም ኮርሶች (ELAm 403 እና ELAm 404) አስቸጋሪ የሆኑባቸው ጽሁፎች «ምናባዊ ጽሁፎች» ናቸው፡፡ እነዚህ ጽሁፎች (የትርጉም ስራዎች) ለተማሪዎች አስቸጋሪ የሆኑባቸው ምክንያት የሚከተለው ነው፡፡

> መልዕክትንና ስልትን በአንድ አስመስሎ መተርጎም በአቀባዩ ቋንቋ እንዳለ በትክክል ከመረዳትም በላይ በተቀባዩ አስመስሎ መፍጠሩ የቋንቋውን እምቅ ሀይል ማወቅንና ምናባዊ ጽሁፍን የመጻፍ ችሎታን ስለሚጠይቅና ተማሪዎችም ይህ ስለሚጎድላቸው ነው፡፡

በሌላው በኩል ለተማሪዎች «የምርምር ወረቀቶች» አስቸጋሪ እንደሆኑባቸው ከመምህሩ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ እነዚህ ስራዎች አስቸጋሪ የሆኑባቸው ምክንያቶች ሃሳብን በስርዓት መደርደር፣ መረጃን ማቀናበር፣ ቃላትን በተገቢው ቦታ መርጦ መጠቀም ጽሁፎቹ ግድ ስለሚሉ (እና ተማሪዎቹም እነዚህ ስለሚጎድሏቸው) እንደሆነ ከመምህሩ መጠይቅ ቁጥር 12 የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

የመምህሩ መጠይቅ፣ በተራ ቁጥር 13 ላይ፣ በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩ ችግሮች ወይም ድክመቶች እንዳሉ ይጠይቃል:: መጠይቁን ከሞሉት ስድስት መምህራን ውስጥ አንደኛው የሉም የሚል ምላሽ ሲሰጡ፣ ሌሎች አሉ በማለት የሚታዩትን ችግሮች በተከታዩ ጥያቄ እንደሚከተለው ዘርዝረዋል:: (ዝርዝሩን ከሠንጠረዥ ሰባት ይመለከቷል::)

ሰ ን ጠ ረ ዥ 7

በተማሪዎች የጽህፈት ስራዎች ውስጥ ተደጋግመው የሚታዩ ድክመቶች (ብዛት = 5)

| የድክመቶች ዓይነት | የመረጃ ሰጪ ብዛት በመቶኛ |
|---|---|
| የሃሳብ አወራረድ | 60 |
| አቀራረብ (format ) | 20 |
| መረጃ ማቀናበር | 60 |
| የቃላት አጠቃቀም | 60 |
| የስርዐተ ነጥብ አጠቃቀም | 60 |
| ሰዋሰው | 60 |

እነዚህ ድክመቶች በተማሪዎች ጽሁፎች ውስጥ ከታዩ፣ ድክመቶቹን ለማስወገድ መምህራት የሚያደርጉት ጥረት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል:: ይህን ጥያቄ ለመመለስ፣ ወይም ችግሮች የተማሪዎች እንጂ የመምህራን ባለመሆናቸው ተማሪዎቹ ስህተት መፈጸማቸውን ተገንዝበው እንዲያሻሽሉ የሚጠቁሟቸው እርማት ያገኛሉ ወይ? የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል::

## 4.2.4 ለተማሪ የጽህፈት ስራዎች የመምህራን ምላሽ

የመምህር መጠይቅ ቁጥር 10 መምህራን የተማሪዎችን የጽህፈት ስራዎች በሚያርሙበት ወቅት ምን ላይ እንደሚያተኩሩ ይጠይቃል:: በመምህሩ መጠይቅ ለዚህ ጥያቄ የተገኘው መረጃ መምህራኑን በሁለቱም፣ በቅርጽና ይዘት ላይ እንደሚያተኩሩ ያሳያል:: ለምሳሌ ከአንደኛው መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቃል በቃል ይነበባል፣ «በይዘቱ ላይ ነው ትኩረቱ:: እግረ መንገዴን ግን የሰዋሰው ስህተት፣ ትክክል ያልሆነ የቃል አገባብ፣ ወዘተ አላልፍም - አስተካክላለሁ::»

በእርግጥ፣ መምህራኑ እንዳሉት ከሆነ ለተማሪዎች የመጻፍ ክሂል መዳበር ጥሩ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ነገር ግን የዚህ መረጃ እውነትነት አጠያያቂ ነው። በተለያዩ አገሮች የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ከጽህፈት ትምህርት ውጭ ሌሎች ትምህርቶችን የሚያስተምሩ መምህራን ከቅርጽ ይልቅ ይዘት ላይ ያተኩራሉ (ለምሳሌ Odell 1992፣ Longer 1992 ይመለከቷል)። ስለሆነም የመረጃውን እውነትነት ለማረጋገጥ በጽሁፎች ላይ መምህራኑ የሰጡትን እርማት መመርመር አንደኛው መንገድ ስለነበር በዚህ ጥናትም ይህንን ለማድረግ ተሞክሯል።

የጽሁፍ አስተያየቶችን አይቶ ትኩረታቸው ይህ ነው ለማለት በርካታዎችን መሰብሰብ ይገባ ነበርና ለዚህ ዓላማ 95 የጽህፈት ስራዎች ፈቃደኛ ከሆኑ ሦስት መምህራን ተሰብስበዋል። ከሦስት መምህራን ከተሰበሰቡት የጽህፈት ስራዎች ውስጥ በአንደኛው ስር የተሰበሰቡት፣ የእርማቱ ትኩረት በምን ላይ እንደሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኗል። በነዚህ ስራዎች ላይ በመምህሩ የተደረገው ምልክት አልፎ አልፎ ጥያቄ ምልክት፣ የትክክለኛ ምልክት (✓ ) እና ውጤት (ማርክ) ብቻ ነው። በመሆኑም በነዚህ ጽሁፎች ላይ የመምህራኑን የጽሁፍ እርማት በመመልከት ትኩረቱ ይሄ ነው ለማለት የሚቻል አልሆነም።

ከሁለተኛው መምህር የተሰበሰቡት ጽሁፎችም ላይ ከውጤት በተጨማሪ ዝቅተኛ የጽሁፍ ገጽታዎች ላይ የተደረጉ አንዳንድ ምልክቶች ቢኖሩም፣ በተለይ ይዘቱን አስመልክቶ የተባለ ምንም ነገር የለም። ይሁን እንጂ በዚህ ስራ ላይ ለግምገማው፣ ይዘት አንደኛው መስፈርት እንደሚሆን መገመት አያዳግትም። ምክንያቱም እነዚህ ጽሁፎች ሃሳብን የሚጠይቁ የፈተና ጥያቄ መልሶች በመሆናቸው ነው። ከሦስተኛው መምህር የተገኙ ጽሁፎች የጽሁፍ እርማቶችን የያዙ በመሆናቸው ትኩረታቸው በምን ላይ እንደሆነ ቀጥለን እንመለከታለን።

ሰንጠረዥ 8

በተማሪ ጽሁፎች ላይ የመምህራን የጽሁፍ እርማት (ብዛት= 48)

| የጽሁፍ ገጽታ | የእርማት ትኩረት | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሜካኒክስ (ስርዓተ ነጥብ፣ ፊደል) | 9 | 9.68 |
| ሰዋሰው | 6 | 6.45 |
| ቃላት | 9 | 9.68 |
| አደረጃጀት | 21 | 22.58 |
| ይዘት | 48 | 51.61 |

ከሰንጠረዥ ስምንት እንደምንረዳው የመምህሩ የጽሁፍ እርማት ትኩረት፣ ከሌሎች የጽሁፍ ገጽታዎች ይልቅ በይዘት ላይ ከፍተኛ እንደሆነ ነው:: ይዘት 51.61% ድርሻ አለው:: ዝቅተኛው (6.45%) በሰዋሰው ላይ የተደረገው እርማት ነው::

በሌላው መልኩ የመምህሩ እርማት በፈለገው ላይ ያተኩር፣ ዋናው ነገር በእርማቱ ተማሪው ለመጻፍ ክሂሉ መዳበር ተጠቃሚ ሆኗል ወይ? የሚለው ለዚህ ጥናት መሠረታዊው ቁም ነገር ነው:: በተለያዩ ጥናቶች እንደተገለጸው እርማቶች ጠቃሚ የሚሆኑት ተማሪዎች እነዚያን እርማቶች በመያዝ ጽሁፋቸውን በራሳቸው አስተካክለው መጻፍ ሲችሉ ነው (Samway 1993:133):: ይሁን እንጂ የተማሪው ቃለመጠይቅ እንደሚያሳየን ተማሪዎች ለአብዛኞቹ ኮርሶቻቸው የሚጽፏቸው ጽሁፎች አይመለሱላቸውም:: በእርማቱ ተጠቅመው አስተካክለው መጻፍ ይቅርና ስህተታቸው ምን ላይ እንደሆነም አያዩትም::

## 4.3 በበሳል ድርሰትና በሌሎች የአማርኛ ኮርሶች የሚከወኑ የጽህፈት ስራዎች እርስ በርስ ያላቸው ዝምድናና ልዩነት

በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት የጽህፈት ልምምዶች፣ ከላይ በ4.1 ስር እንደተመለከተው፣ ከዐረፍተ ነገር ምስረታ አንስቶ ሙሉ ድርሰትን በገላጭ፣ በተራኪ፣ በአስረጂና በአከራካሪ ድርሰቶች እስከመከወን ይደርሳል:: አንቀጽና ከአንቀጽ በላይ፣ ወይም ሙሉ ድርሰትን አስመልክተው የሚደረጉት ልምምዶች በቅድሚያ ተማሪዎች ወይም መምህሩ ከተፈለገው

የጽሁፍ ቅርጽ ጋር አብሮ የሚሄደውን ርዕስ ለልምምዱ በመምረጥ ነው:: ለምሳሌ የትምህርቱ ትኩረት በአከራካሪ የድርሰት ዓይነት ላይ ከሆነ ልምምዱ፣ «ሴቶች ከወንዶች ያንሳሉ ወይስ እኩል ናቸው»፣ «ወንደላጤኑት ወይስ ባለትዳርነት»፣ «መሬት ክብ ወይስ ዝርግ» የሚሉ ርዕሶችን በመያዝ ይካሄዳል (ለዝርዝሩ በሠንጠረዥ ሁለት የቀረቡትን ርዕሶች ይመለከቷል):: እነዚህ ልምምዶች ከተለያዩ ነገሮች (ከንባብ፣ ከስዕል፣ ከተፈጥሮአዊ ገጽታ) ጋር በመቀናጀት አልፎ አልፎ የሚከወኑ ቢሆኑም አብዛኞቹ ከግል ገጠመኝ አንጻር ብቻ በመነሳት የሚከወኑ ናቸው:: ባጠቃላይ፣ አብዛኞቹ የበሳል ድርሰት ኮርሶች ልምምዶች ተማሪዎች ስለሚጽፉበት ርዕስ «ትክክለኛ» መረጃ ለመስጠት ድርሳናትን አገላብጠው ወይም ሌሎች ምንጮችን ተመልክተው ከነዚህ የሚያገኙትን መረጃ መሠረት በማድረግ የሚጽፉባቸው አይደሉም:: በልምምዶቹ ዋናው ተፈላገው ነገር መዋቀሩ እንጂ በተመረጠው ርዕስ ላይ ምንጭን ተጠቅሞ «ትክክለኛ» መረጃ ማቅረብ አይደለም::

በሌላው መልኩ፣ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ የሚከወኑት ጽሁፎች የተለያዩ ዓይነት ናቸው:: እነዚህ ስራዎች በርካታ ዓይነት አቀራረብ፣ የተለያዩ የአጸጻፍ ስልት የሚጠይቁ ናቸው:: ሆኖም እነዚህ ጽሁፎች በማናቸውም ላይ የሚጻፉት በአብዛኛው ተማሪዎች በይዘቱ (subject matter) ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳዩ ነው:: የእነዚህ ሃሳብ ምንጭ ከባዶ ወይም ከግል ገጠመኝና ስሜት የሚነሳ አይደለም:: የእነዚህ ስራዎች የሃሳብ ምንጭ (መነሻ) ንባብ ወይም በመማር ማስተማሩ ከኮርሱ የተገኘው እውቀት ነው::

ከነዚህ ነጥቦች አንጻር ሲታይ በበሳል ድርሰት የሚደረጉት ልምምዶች በሌሎች ኮርሶች ከሚከወኑት የጽህፈት ስራዎች ልዩነታቸው የጎላ ነው:: ይህውም፣ ከላይ በየእርእስቱ በተናጥል እንደተመለከተው፣ በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት የጽህፈት ልምምዶች አብዛኞቹ ከግል ገጠመኝ አንጻር የሚከወኑ ሲሆኑ፣ በሌሎች ኮርሶች የሚከወኑት ደግሞ አብዛኞቹ ከግል ገጠመኝ ወይም ስሜት ላይ በመነሳት የሚከወኑ አይደሉም:: በተጨማሪም በበሳል ድርሰት ኮርሶች የሚደረጉት ልምምዶች ቅድሚያ ትኩረታቸው አንድን የጽሁፍ መዋቅር ወይም ህግ ለማሳወቅ ሲሆን፣ በሌሎች በአብዛኞቹ ኮርሶች የሚደረጉት ግን ባብዛኛው አንድን እውቀት ለማሳየት ወይም መረጃ ለማስተላለፍ (ለመስጠት) ነው::

ይሁን እንጂ፣ ይህ ልዩነት (በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች መካከል ያለው) ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች በሚደረጉ የጽህፈት ስራዎች መካከል እርስ በርስ መደጋገፍ የለም

ወይም መደጋገፉ ዝቅተኛ ነው የሚለውን አያመለክትም፡፡ በአጠቃላይ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ያሉ ኮርሶች በቋንቋው ከማስልጠን አኳያ የተቀረጸ በመሆናቸው በነዚህ ኮርሶች ተማሪው የሚያከናውናቸው የጽሁፍ ስራዎች መካከል መደጋገፍ አለ፡፡ ለምሳሌ ሶስተኛ አመት የሚያስተምር መምህር የተገኘ የመጠይቅ መረጃ እንደሚያሳየን፣ ለተማሪዎች የምርምር ጽሁፎች አስቸጋሪ ናቸው ይልና ለዚህ አስቸጋሪነት ምክንያቱ ሀሳብን ከእንግሊዝኛ ወስደው ስለሚጽፉ ነው ይላል፡፡ ይህ በእውነት ችግራቸው ከሆነ ተማሪዎቹ በአራተኛ አመት ደረጃ ሲደርሱ በትርጉም ኮርሶች እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ፣ አሊያም ቢያንስ ለመቀነስ የሚያስችላቸው በርካታ የትርጉም ልምምዶች ያደርጋሉ፡፡ ይህ በአንደኛ ኮርስ የሚደረገው ልምምድ በሌላኛው ኮርስ በሚደረገው መታገዙን የሚያሳይ ይመስለናል፡፡ በአጠቃላይ መልኩ ሲታይ፣ በበሳል ድርሰት የሚደረጉት ልምምዶች በተገኘው መረጃ መሠረት ለሌሎች የጽህፈት ስራዎች ጋር ተደጋጋፊ ናቸው ለማለት አያስደፍርም ብንልም፣ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ በሌሎች ኮርሶች በሚደረጉ የጽህፈት ስራዎች መካከል ምንም አይነት መደጋገፍ ወይም ዝምድና የለም ማለታችን ግን አይደለም፡፡

ምንም እንኳ መምህራኑ ለተማሪ ጽሁፎች የሰጡትን እርማት በመያዝ በበሳል ድርሰትና በሌሎች ኮርሶች ያለውን ሙሉ በሙሉ በማነጻጸር ማየት ባይቻለንም ምክንያቱም ከላይ በርእስ 4.2 ስር እንደተመለከትነው አብዛኞቹ ስብስብ ጽሁፎቹ ከማርክ በስተቀር ሌላ እርማት አልተደረገባቸውምና የተወሰኑትን ብቻ ይዘን ስንመለከትም በሁለቱ መሀከል ልዩነት መኖሩን እንገነዘባለን፡፡ በበሳል ድርሰት ኮርሶች በሰንጠረዥ 4 እንደተመለከተው የመምህሩ የጽሁፍ እርማት በይዘት ላይ 17.8% ብቻ ነው፡፡ በሌሎች ኮርሶች ደግሞ፣ በሰንጠረዥ 8 እንደተመለከተው በይዘት ላይ የተደረገው የጽሁፍ እርማት 51.6% ነው፡፡ ይህ በበሳል ድርሰት ኮርሶችና በሌሎች ኮርሶች የጽህፈት ስራዎች መካከል ካለው ልዩነት በተጨማሪ በእርማት መሀከልም ልዩነት መኖሩን ይጠቁመናል፡፡ ይህም ለተማሪ ጽሁፎች የመምህራን የጽሁፍ እርማት በበሳል ድርሰት ኮርሶች ከይዘት ይልቅ በቅርጽ ላይ ሲያተኩር፣ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ ባሉ ኮርሶች ግን ከቅርጽ ይልቅ በይዘት ላይ ያተኩራል፡፡

# ም ዕ ራ ፍ   አ ም ስ ት

## መደምደሚያና አስተያየት

### 5 . 1 መደምደሚያ

በበሳል ድርሰት ኮርሶች የጽህፈት ልምምዶች፣ በተለይ በመጀመሪያው ኮርስ (ELAm 203 ) ዐረፍተ ነገርን በተናጥል እና ከአረፍተ ነገር በላይ አንቀጽን በመጻፍ የሚከወኑ ሲሆኑ፣ በሁለተኛው ኮርስ (ELAm 204) ደግሞ ሙሉ ድርሰትን በተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች (ገላጭ፣ ተራኪ . . .) በመጻፍ የሚከወኑ ናቸው:: በነዚህ ኮርሶች የሚደረገው ልምምድ ከዐረፍተ ነገር ተናጠል ምስረታ አንስቶ እስከ ሙሉ ድርሰት የሚዘልቅ ነው:: እነዚህ ልምምዶች የተለያዩ መዋቅሮችን፣ የጽሁፍ ሕግጋትን ለማሳወቅ የሚደረጉ ናቸው:: የእነዚህ ልምምዶች ቅድሚያ ትኩረት ተግባቦታዊ ተግባርን ማዳበር ነው ለማለት አያስደፍርም::

ይሁን እንጂ፣ ይህ የመዋቅር ልምምድ በተግባቦት ላይ አላተኮረም ተብሎ የሚወቀስ አይመስለንም:: ይህም፣ አንደኛ፣ የቋንቋ ትምህርት በመሆኑ፣የቋንቋ ትምህርት ሰዋሰዋዊ እና ወይም ሌሎች የጽሁፍ ሕግጋትንና መዋቅራትን ማስተማር ስለሚገባው ነው:: ሁለተኛ ተማሪዎች ከሁለተኛ ደረጃ ይዘውት የመጡት ልምድ ደካማ ስለሆነ ነው:: የመምህሩ ቃለመጠይቅ እንደሚያመለክተው ከሆነ፣ ዐረፍተ ነገርን በተናጥል ከመከወን ጀምሮ ትምህርቱ እንዲሰጥ የሆነበት ምክንያት ተማሪዎቹ አረፍተ ነገርን በተናጥል እንኳን በትምህርቱ መከወን ያልተሳካላቸው በመሆኑ ነው::

ይህ በተማሪው ችግር ላይ የማተኮሩ ጉዳይ በጥሩነቱ ሊወደስ የሚገባው ቢሆንም፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ሙሉ ተሳታፊ በማድረግ ችግራቸውን ለመቅረፍ በሚያስችል የጽሁፍ ሂደት ላይ የሚያተኩር ሆኖ አናገኘውም:: ጽህፈትን በሂደታዊ ስልት ማስተማር አልፎ አልፎ፣ 20% ያህል ብቻ (ያም ቢሆን ሙሉ ሂደት ላይ ያተኮረ አይደለም::) በትምህርቱ የሚከወን ነው:: ይህ አለመደረጉ በእርግጥ ተማሪዎች እነዚህን ኮርሶች (ELAm 203 እና ELAm 204) ከወሰዱ በኋላም ጥሩ የጽሁፍ ሂደት እንደሌላቸው ከተማሪው መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያሳያል::

አብዛኞቹ ተማሪዎች ጽሁፍን በመከወን ያላቸው ልምድ በቂና ጥሩ ጸሐፊዎች የሚያልፉበት ሆኖ አልተገኘም::

በሌላ በኩል፣ ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ በተለያዩ ኮርሶች ለተማሪዎች በርካታ የጽህፈት ስራዎች ይሰጣሉ። በአንድ ኮርስ እስከ ሦስት የሚደርሱ የጽህፈት ስራዎች እንደሚሰጡ ተመልክተናል። ይህ፣ ጽህፈትን ለመማር ዋናው ነገር መጻፍ ነው ከሚለው ብሂል ወይም አመለካከት ጋር አብሮ የሚሄድ፣ በራሱም ሲታይ እውነትነት ያለው ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ በክሂልነቱ ጥሩ ነው ቢባልም፣ ጽህፈትን ለመማር «ዝም ብሎ መጻፍ» ብቻ የሚፈይደው ነገር በጣም አነስተኛ ነው። ጽህፈትን ለመማር መጻፍ የሚለው አመለካከት ጠቃሚ የሚሆነው መጻፉ መስመር ይዞ ለክሂሉ መዳበር ተገቢ እገዛ የሚያደርግ ሲሆን ነው።

በዚህ መልኩ፣ በነዚህ ኮርሶች (ከበሳል ድርሰት ውጭ ባሉት) የሚደረጉት የጽህፈት ስራዎች፣ በአንድ ወገን፣ በብዛትና የተለያየ ዓይነት ቅርጽና ስልት ይዘው በመከወናቸው የሚያስመሰግን ቢሆንም፣ መምህራኑ በነኚህ ስራዎች ላይ የሚያደርጉት ጥረት ለጽህፈት ክሂል መዳበር ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚመሰገን አይደለም። መምህራኑ ለጽህፈት ክሂል ብለው የሚያደርጉት ጥረት በዚህ ጥናት ውስጥ እንደተጠቆመው እጅግ በጣም ደካማ ነው። የዚህ ድክመት ምክንያት ምናልባት የትምህርት ክፍሉ በራሱ ለነዚህ ጉዳዩች ትኩረት ሰጥቶ መምህራኑን ካለማነጋገሩ ወይም መምህራኑ እንዲነጋገሩበት የጋራ መድረክ ካለመፍጠሩ የመጣ ሊሆን ይችላል። ጽሁፎቹ የኮርሱ መሠረታዊ አካል ስለሆኑ ይሰጣሉ እንጂ ፣ ተማሪዎች ወደፊት የቋንቋው አስተማሪ ወይም ባለሙያ ስለሚሆኑ በዚያ ላይ የክሂሉ ባለቤት ሆነው እንደገኙ ከሚል አመለካከት አይሰጡም። በአብዛኛው፣ የጽህፈት ክሂል የሚለውን የድርሰት ኮርስን ብቻ የሚመለከት አድርገው የሚቆጥሩ መምህራን በርካታ ናቸው።

በሌላ በኩል፣ ተማሪው ለሚጽፋቸው ጽሁፎች ምን ዓይነት አስተያየት እንደተሰጠው አለማወቁ ከፍተኛ ችግር እንደሆነ በትንታኔው ተመልክተናል። ይህ በትንታኔው እንዳየነው፣ ከበሳል ድርሰት ውጭ ባሉ ኮርሶች የሚደረጉት አብዛኞቹ የጽህፈት ስራዎች ታርመው ለተማሪው ካለመመለሳቸው በተጨማሪ የቀረበው እርማት በራሱ ስህተቱን አያመለክትም። ስህተቱን የሚያመለክቱ የተወሰኑትም ደግሞ ከፍተኛ ትኩረታቸው በይዘት ላይ ነው። በበሳል ድርሰት የሚደረገው ደግሞ ባብዛኛው ከይዘት ይልቅ ቅርጽ ላይ ያተኮረ ነው። ይህ ሁናቴ ተማሪው ለጽሁፎቹ ከመምህሩ በሚሰጠው (በሚቀርብለት) የጽሁፍ እርማት ተጠቃሚ ሆኗል ለማለት የሚያስችል አይመስለንም።

በአጠቃላይ፣ በዚህ ጥናት እንደተመለከትነው፣ ተማሪው በክፍሉ ቆይታው በሚወስዳቸው ኮርሶች በርካታ የጽህፈት ስራዎችን ያከናውናል:: እነዚህን በማከናወኑ ተጠቃሚ መሆኑ አይካድም:: ይሁን እንጂ፣ የበለጠ በነዚህ ስራዎች ተጠቃሚ እንዲሆን መምህራኑ በኮርሶቻቸው ከሚያስተምሩት «ይዘት» በተጨማሪ ለክሂሉ መዳበር ብለው የሚያደርጉት ጥረት ለመኖሩ በዚህ ጥናት መረጃ አልተገኘም:: የጽህፈት ክሂል ከበሳል ድርሰት ኮርሶችና ሌሎች በቀጥታ ጽህፈትን ከሚመለከቱት (ለምሳሌ ELAm 202) ውጭ የጽህፈት ክሂልን ለማስተማር በሌሎች ኮርሶች ትኩረት ለመደረጉ ምንም ማስረጃ የለንም:: በበሳል ድርሰት ኮርሶችም ቢሆን የሚያደርጉት ልምምዶች በሌሎች ኮርሶች ከሚደረጉት የጽህፈት ስራዎች ጋር ሲተያዩ ከግንኙነታቸው ይልቅ ልዩነታቸው የሰፋ ነው:: በበሳል ድርሰት በሚያደርጉት የጽህፈት ልምምዶች ተማሪዎች በኮርሶቹ እንዲያውቁ የተፈለገውን የጽሁፍ ህግ ወይም መዋቅር የሚማሩት በሌሎች ኮርሶች የሚያጋጥሟቸውን የጽሁፍ ስራዎች በማገናኘብ እነዚያን አይነት ስራዎች በክፍል ውስጥ በማምጣት አቀናጅቶ አለመሆኑን ስትንታኔው ተመልክተናል:: ከነዚህ ስራዎች ነጥቦች አንጻር ስንመለከት ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለሚገኙ መደበኛ ተማሪዎች በአማርኛ በሚሰጡ በሳል ድርሰትና ሌሎች ኮርሶች ውስጥ የጽህፈት ክሂልን በመተጋገዝና በመተባበር ለማዳበር የሚደረገው ጥረት በጣም ደካማ ነው ለማለት የሚቻል ይመስለናል::

## 5 . 2 አ ስ ተ ያ የ ት

የጽሁፍ ክሂል በአንድ ጊዜ የሚጨበጥ አይደለም:: በሐገራችን ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት የተነፈገው ነው:: ይህ በመሆኑ ተማሪዎችን ብቁ ጸሐፊዎች ለማድረግ በበሳል ድርሰት ኮርሶች ወይም በሌሎች ውስን የጽህፈት ኮርሶች ብቻ ተመርኩዞ ክሂሉን ለማዳበር ይቻላል የሚል እምነት የለንም:: በእርግጥ፣ በተለያዩ ኮርሶች በርካታ የጽህፈት ስራዎች ይከወናሉ:: ከላይ እንደገለጽነው፣ ጽህፈትን ለመማር ዋናው ነገር መጻፍ ነው የሚል አመለካከት ቢኖርም ይህ «መጻፍ» የጽህፈት ክሂልን እንዲያዳብር በሌሎች የጽሁፍ ልምምዶች ሊታገዝ ይገባዋል:: ስለዚህም በጽህፈት ትምህርት በአንጻራዊ አጭር ጊዜ ውስጥ የክሂሉ ባለቤት ለመሆን ተገቢና ትክክለኛ ልምምዶችን ማከናወን አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው:: ስለሆነም ከዚህ ጥናት ግኝት በመነሳት ለወደፊቱ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል የተሻሉ ጸሐፍት ለማፍራት ይቻለው ዘንድ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል::

1 . ምንም እንኳ ከጽህፈት ትምህርት ውጭ የሚያስተምሩ መምህራን በኮርሶቻቸው የሚያስተምሩት ይዘት ቢኖርም የጽህፈት ክሂልን አስመልክቶ የተወሰኑ ነገሮችን ማድረግ የሚችሉ ይመስለናል::

ሀ / ተማሪዎች የሠሩቸውን የጽህፈት ስራዎች በወቅቱ አርሞ መመለስ፣

ለ / በእርማቱ ወቅት መምህራን ጊዜ ወስደውም ቢሆን (ምናልባት ጊዜ ከሌለው ከጽህፈት መምህራን ጋር በመተባበር መስራት የሚቻል ይመስለናል) ተማሪዎች የሚታዩባቸውን ድክመቶች በመጠቆም እርማቱ ከውጤት መመዝገቢያነት ባሸገር ለክሂሉ መዳበር ጠቃሚ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፣

ሐ / አንዳንድ ስነትምህርታዊ ገለጻ፣ (ስለአጻጻፍ፣ ስለመረጃ አሰናነድ ወዘተ.) ማድረግ::

2 . የድርሰት ትምህርት በመዋቅር ላይ ማተኮሩ ተገቢነት ቢኖረውም፣ አሁን ካለበት ሁኔታ መሻሻል የሚገባው ነገር ያለ ይመስለናል:: የድርሰት ትምህርት ዓላማ በአንድ በኩል ለተማሪው ስህተቱን ፈልጎ ራሱ አስተካክሎ መከወን የሚያስችለውን ብቁ ክሂል ማስጨበጥ፣ በሌላ በኩል በሌሎች ኮርሶች ለሚያስፈልጉ የጽህፈት ስራዎች ብቁ ማድረግ ነው::

ስለሆነም፣ እነዚህን ነገሮች አጣጥሞ ለማቅረብ፣ የጽሁፍ ሂደትን ንባብ- ምርኩዝ በሆኑ ስራዎች ለማስተማር ቢሞከር ተገቢነት ይኖረዋል:: በዚህ ሂደትም አሁን የሚተኮርባቸው ሰዋሰው፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የአንቀጽ አገነባብ ወዘተ. ማስተማር የሚቻል ይመስለናል::

ይህ የሚደረገው፣ በሌሎች ትምህርቶች (ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ) የሚከወኑ ስራዎች ከንባብ ጋር ባብዛኛው የተቆራኙ በመሆናቸው ሳይሆን፣ ንባብ የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግም በርካታ ጥናቶች ስለሚያሳዩ ነው (ለምሳሌ Krashan 1984፣ Eisterhold 1990 ይመለከቷል):: ከዚህም በላይ የመጻፍ ሂደት፣ ፍቺ የመፍጠር (Meaning making) ጣጣ የሆነውን ያህል፣ የማንበብ ሂደትም ፍቺ የመፍጠር ሂደት ነውና ሁለቱም ይተጋገዛሉ (Zamel 1992፡463):: ስለዚህም ከንባብ ጋር ጽህፈትን ማጣመሩ ጠቃሚ ነው:: ይህ ንባብ ምናልባት ለተማሪዎች ተጨማሪ ጫና ይፈጥርባቸዋል ቢባል እንኳ፣ ጽህፈቱን በሌሎች ኮርሶች ከሚያደርጋቸው ንባቦች ጋር ማቀናጀት የሚቻል ይመስለናል::

3 . የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል፣ ተማሪዎች በመጻፍ በኩል ያለባቸው ችግር ምንድነው ብሎ መርምሮ ወይም አወያይቶ እንደማያውቅ ከመምህራንና ከክፍሉ ሲ.ቀመንበር ጋር የተደረገው ቃለመጠይቅ ያሳያል:: በተማሪዎች ላይ በማተኮር ማስተማር፣ ጠቃሚነቱ በተለያዩ ዘርፎችና ጥናቶች የታየ ነው::

ስለሆነም " ትምህርቱን " ብቻ አስመልክቶ ውይይትና ስብሰባ ከማድረግ ጋር፣ ቢያንስ ጎን ለጎን ተማሪዎች ያሉበትን ደረጃ መርምሮ፣ ችግር ካለባቸው የሚረዱበትን፣ ከሌለባቸው የያዙት በጎ ነገር የሚጠናከርበትን መንገድ መፈለግ ይገባዋል:: ይህ እንዲቻል በየዘርፉ መምህራንን ሰብስቦ ማነጋገርና ማወያየት የክፍሉ ልማድ እንዲሆን ከዚህ ጥናት በመነሳት የበኩላችንን ቀና አስተያየት ለመስጠት እንወዳለን::

# ዋ ቢ ጽ ሁ ፎ ች


ማረው አለሙ:: 1987:: «በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል በ2ኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ንጽጽራዊ ግምገማ ጥናት» (የሁለተኛ ዲግሪ ሚሟያ ጥናት):: አዲስ አበባ፣ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (የልታተመ)

ሰሎሞን ተሰማ:: 1987:: «የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ገላጭ ጥናት» (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት):: አዲስ አበባ፣ ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)

ሺበሽ አለማየሁ:: 1985:: «የቅድመ ድህረ 1984 ዓ.ም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ምንባቦች ንጽጽራዊ ግምገማ» (የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናት):: አዲስ አበባ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል::(ያልታተመ)

በየነ ማሞ:: 1985:: «በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?» (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት):: አዲስ አበባ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)

ባዬ ይማም:: 1987:: <u>የአማርኛ ሰዋሰው::</u> አዲስ አበባ ፣ ት. መ . ማ . ማ . ድ::

ተስፋዬ ሸዋዬ 1981 :: «ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር»:: አዲስ አበባ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ:: (ያልታተመ)

_____ :: 1986:: <u>አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር::</u> አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ::

ተክለማርያም ፋንታዬ::1955:: <u>አንደኛ የድርሰት መምሪያ</u>:: አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት::

ነጋሳ እጇታ::1965:: «በ1962 ዓመተ ምህረት የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ የስህተት ዓይነቶች» /የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ/:: አዲስ አበባ ፣ የኢትዩጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል::(ያልታተመ)

አለማየሁ ጸጋዬ:: 1986:: « በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ስህተቶች ዋና ዋና ምንጮች» /የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት/:: አዲስ አበባ፣ ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት:: (ያልታተመ)

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት::1982:: <u>ጥሩ የአማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?::</u> አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

ክፍሌ ሀብተማርያም::1986 «የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ» /የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት/:: አዲስ አበባ፣ ድህረ-ምረቃ ት/ቤት:: (ያልታተመ)

Bazerman, Charles .1992." From Cultural Criticism to Disciplinary Participation: Living with Powerful Words". In A.Herrington & C.Moram (eds.), Writing, Teaching and Learning in the Disciplines (PP 61 - 68). New York: The Modern Language Association of America.

Braine G. 1989. "Writing in Science and Technology: An Analysis of Assignments from Ten Undergraduate Courses" in. English for Specific Purposes. 8 (1): 3-15.

Brooks, A. & P. Grundy. 1990. Writing for Study Purposes: A Teacher's Guide to Developing Individual Writing Skills. Cambridge: Cambridge University Press.

Brumfit, C. 1990. Communicative Methodology in Language Teaching: The Roles of Fluency and Accuracy. Cambridge: Cambridge University Press.

Chenoweth, N.Ann. 1987. " The Need to Teach Rewriting." In ELT Journal .1(1): 25-29.

Chimombo, Moria. 1986. "Evaluating Compositions with Large Class" In ELT Journal 40 (1): 20 - 26.

Cohen, Andrew D. 1987. " Student Processing of Feedback on their Compositions". In A. Wenden & J. Rubin, Learners Strategies in Language Learning (PP 57 - 69). Cambridge: Printce Hall International Ltd.

Cohen, Andrew D. & M.C. Cavalcanti: 1990" Feedback on Compositions: Teachers and Student Verbal Reports". In B.K. Kroll (ed), Second Language Writing: Research Insights for the Classroom (PP 157 - 177). Cambridge: Cambridge University Press.

Davies, A. & H. G. Widdowson. 1974 "Reading and Writing". In J.P.B. Allen & S.Pit Corder (eds.), The Edinburgh Course in Applied Linguistics Vol.3. (PP 155 - 188). London: Oxford University Press.

.Eisterhold, J. Carson. 1990. "Reading- writing connections: Toward a Description for Second Language Learners." In B.K. Kroll (ed), (pp88 - 101).

Ferris, Dana R. 1995. "Students Reactions to Teacher Response in Multiple - Draft Composition Classroom. " In TESOL Quarterly 29(1): 33 - 53

Getnet Tizazu .1993. "The Responding Behavior of Sophomore English Instructors of AAU to Student Writing " /MA. . Thesis/ . Addis Ababa University: The School of Graduate Studies. /Unpublished/

Graham,S., Schwarty, S. & C. McArthur 1995. ' Effects of Goal setting and Procedural Facilitation on the Revising Behavior and Writing Performance of Students with Writing and Learning Problems. "In Journal of Educational Psychology. 87(2): 230-240.

Haliday, MAK & McIntosing Anyus, Peter Strevens. 1964 The Linguistic Science and Language Teaching. London : Longman

Hamp-Lyons, L. 1986. "No New Lamps for Old yet, Please (in The Forum). In the Forum). In TESOL Quarterly. 20 (4): 790 - 796.

Hedge, Tricia. 1988. Writing: Resource Books for Teachers. Oxford: Oxford University Press.

Herrington, A. & C.Moran (ed) .1992. Writing, Teaching, and Learning in the Disciplines. New York: The Modern Language Association of America.

Horowitz, D.M. $1986_a$ . " The Author Responds to Hamp-Lyons..." ( In the Forum) TESOL Quarterly. 20 (4): 796 - 797

_____. $1986_b$ . " The Author Responds to Leibman-Kleine ..."(In ---- The Forum). In TESOL Quarterly. 20 (4): 788 - 790.

_____ . $1986_c$. "Essay Examination Prompts and the Teaching of Academic Writing". English for specific purpose. 5 (1): 107 - 120.

_____ . $1986_d$. "Process not Product: Less than Meets the Eye " (In The Forum). TESSOL Quarterly. 20 (1): 141 - 144.

_____ . 1986e. " What Professors Actually Require: Academic Tasks for the ESL Classroom. " In TESOL Quarterly. 20 (3): 445 - 463.

Hutchinson, Tom & Alan Waters. 1987. English for Specific Purpose: A Learning - Centered Approach. Cambridge: Cambridge University Press.

Jenkins, S., Jordan, M.K & P.O. Weiland. 1993. " The Role of Writing in Graduate Engineering Education: A survey of Faculty Beliefs and Practices ." In English for Specific Purpose. 12 (1): 51 - 67.

Johns, A.M. 1981. " Necessary English: A Faculty Survey." In TESOL Quarterly 15 (1): 51-57

Kiflemariam Zerom. 1988. " Acquisition and use of Discourse Markers in Student Writing at Sophomore Level" /MA. Thesis/. Addis Ababa University: The school of Graduate Students. /unpublished/

Krashan, S. 1984. Writing: Research, Theory and Applications, Oxford: Pergaman Institute of English.

Kroll, B. 1979. " A Survey of the Writing Needs of Foreign and American College Freshman." In English Language Teaching Journal. 33(3): 219 - 227.

_____. 1990. " What does Time buy? ESL Student Performance on Home Versus Class Compositions." In Barbara Kroll (ed.)pp 140-154.

_____ . 1991. " Teaching Writing in the ESL context" In Marianne Celce - Murcaia (ed). Teaching English as a Second or Foreign Language. sec.ed. PP 245 - 263. Boston: Heinle & Heinle Publishers.

Kusel, Paul A. 1992. "Rhetorical Approaches to the Study & Composition of Academic Essays." In TESOL Quarterly. 20(4): 457 - 469

Larsen - Freeman, Diane. 1986. Techniques & Principles in Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Leki, I 1990. " Coaching from the Margins: Issues in Writing Response." In B. Kroll(ed.) , (PP 57 -68).

Leki, I AJ. G Corrsen. 1994. "Students Perceptions of EAP Writing Instruction and Writing Needs Across the Disciplines." In TESOL Quarterly. 280 (1): 81 - 103.

Leibman-Kleine, J. 1986 In Defense of Teaching Process in ESL Composition" in the Forum). In TESOL Quarterly. 20 (4): 783 - 788.

Longer, A. Judith. 1992. " Speaking of Knowing: conception of Understanding in Academic disciplines. " In A. Herrington and C. Moran (ed), (pp 69-85).

Mamo Kifle .1981. " Classification and Explanatory Analysis of Student Errors in Advanced English Composition II ". (MA. Thesis/. Addis Ababa University: The School of Graduate Studies. /unpublished/

Morrsella, J, Thilgers, T. L and C. Mclaren. 1992 "How Students Handle Writing Assignments: A Study of Eighteen Response in Six Disciplines". In A. Herrington and C.Moran(eds)., (pp 174 - 188)

Martin, Nancy. 1992. " Language Across the Curriculum: Where it Began and what it promises". In A. Herrington and C. Moran (eds), (pp 6 - 21).

McArthur, Tom. 1984 A Foundation Course for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Morris, Barbara L. 1982 " The English Language Communicative Needs of Addis Ababa University Studies. " /MA Thesis /. Addis ababa University: The School of Graduate Studies. /unpublished/

O'Connell, Peter. 1982. " Suggestopedy & the Adult Language Learner. " In ELT Documents: 113 - Humanistic Approaches an Empirical View. London: The British Council.

Odel, Lee. 1992. " Context - Specific Ways of knowing & the Evaluation of Writing" In A. Herrington & Moram (eds.), (pp 86 - 98).

Olshtain, Elite. 1991. "Functional Tasks for Mastering the Mechanics of Writing and Going Just Beyond. " In Mariane Celce - Murcia(ed).

Raimes, Ann. 1993. Techniques in Teaching Writing. Oxford: Oxford University Press.

Reid, Joy .1994. " Responding to ESL Students 'Texts: The myths of Appropriation. " In TESOL Quarterly. 20 (4) 273 - 292.

Richards, Tack C. 1990. The Language Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, jack C. & T.S. Rodgers .1986. Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press.

Roobinson, Pauline .1991. ESP Today: A Practioner's Guide. Great Britain: Prentice Hall International.

Royster, J.J .1992. "From Practice to Theory: Writing Across the Disciplines at Spelman College". In A. Herrington & C. Moran(ed.), (pp 119-131).

Russel, D.R. 1987. " Writing Across the Curriculum and the communications Movement: Some Lessens from the Past" In College Composition and communication. 38(2): 184 - 194.

______. 1992. "American Origin of the Writing Across - the curriculum Movement" In A Herrington & C. Moran(eds) (pp 22 - 42).

Samway, K.D. 1993. " This is Hard, isn't it?" : Children Evaluating Writing." In TESOL Quarterly 27:2, 233 - 258.

Santos, T. 1988."Professors' Reactions to the Academic Writing of Nonnative Speaking Students." In TESOL Quarterly. 22 (1): 69 - 90

Shih, M. 1986. " Content-based Approaches to Teaching Academic Writing " In TESOL Quarterly. 20(4): 617-648.

Silva, T. 1990. "Second Language Composition Instruction: Developments, Issues & Directions in ESL". In B.Kroll(eds.), (pp 11-23).

Spack, R. 1988. " Initiating ESL Students into the Academic Discourse Community: How Far Should We Go?" In TESOL Quarterly. 20 (1): 29-51.

Stren, H.H 1983. Fundamental Concepts of Language Teaching. Oxford: Oxford University Press.

Swales, John M. 1990. Genre Analysis: English in Academic & Research Settings. Cambridge: Cambridge University Press.

Tesfay Abebe .1991. " Teaching Writing in Grade Eleven: The Existing Practice Versus the Controlled & the Guided Methods." /MA. Thesis/. Addis ababa University: The School of Graduate Studies. /unpublished/

Tarone, E & G. Yule. 1989. Focus on the Language Learner. Oxford: Oxford University Press.

White, Ron 1987 Writing Advanced. Oxford: Oxford University Press

White, Ronald. 1989. " Teaching Written English. Oxford: Heineman International

Zamel, V. 1985. " Responding to Student Writing. In "TESOL Quarterly. 19 (1): 79 - 101.

_______. 1992. "Writing One's Way into Reading." In TESOL Quarterly. 26 (3): 463 - 485.

## ሙዳየ ቃላት

| | | |
|---|---|---|
| ሂደት ተኮር ስልተ ትውር | = | process centerd - approach |
| መርሐ ግብር | = | program |
| መካኒክስ | = | mechanics |
| የሙከራ ጥናት | = | pilot study |
| ማብራሪያ | = | discussion |
| ምላሽ | = | response |
| ራይቲንግ አክሮስ ዘ ካሪኩለም | = | writing across the curriculum |
| ስህተት ፍንጮች | = | false cues |
| ስልተ ትውር | = | approach |
| ስርዓተ ትምህርት | = | curriculum |
| ቅይጥ ስልተ ትውር | = | Eclectic approach |
| ቅድመ-ጽሁፍ | = | pre-writing |
| የብጤ እርማት | = | peer correction |
| ተላውጦ | = | variable |
| ትምህርት መስክ | = | discipline |
| ትምህት መስክ-ምርኩዝ | = | discipline-based |
| ትውር | = | theory |
| ንቅናቄ | = | movement |
| አለምአቀፋዊ ትውር | = | global theory |
| አረፍተ ነገር ደረጃ ማጠናከሪያ ልምምዶች | = | sentence level reinforcement exercises |
| አነስተኛ ስህተቶች | = | local errors |
| አፍአዊ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች | = | surface level writing features |
| እንግሊሽ ፎር ስፔስፊክ/ ስፔሻል ፐርፐዝ | = | English for secific/special purpose |
| እንቅስቃሴ | = | movement |
| ከፍተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች | = | high level writing features |
| የኮርስ መግለጫ | = | course description |

| | | |
|---|---|---|
| የኮርስ ቢጋር | = | course outline |
| ዋና ስህተቶች | = | global errors |
| ውጤት | = | result |
| ውጤት ተኮር ስልተ ትውር | = | product focused approach |
| ዝቅተኛ ደረጃ የጽሁፍ ገጽታዎች | = | low level writing features |
| ዲስኩር | = | discourse |
| የዲስኩር ማኅበረሰብ | = | discourse community |
| ዲስኩር ደረጃ የተግባር ልምምዶች | = | discourse level practice exercises |
| ድኅረ-ጽሁፍ | = | post-writing |
| ግላዊ ብዕሮግ | = | personal essay |
| ጥሩ ፍንጮች | = | good cues |
| ጥብቅ ጽሁፍ | = | controlled writing |
| የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | = | problem of the study |
| የጥናቱ ንድፍ | = | the design of the research |
| ጥንታዊ ግላዊ ብዕሮግ | = | traditional personal essay |
| የጽሁፍ ክሂሎች(ገጽታዎች) | = | writing skills/features |
| የጽህፈት ልምምድ | = | writing exercises |
| የጽህፈት ስራ | = | writing task |
| ፍቺን መፍጠር | = | meaning making |

# አባሪ

## አባሪ « ሀ» – መጠይቅ

## አባሪ ሀ . 1 . – የመምህር መጠይቅ

### አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
### ድህረ ምረቃ ምትምህርት ቤት
### በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል መምህራን
### የሚሞላ መጠይቅ

መግቢያ

ይህ መጠይቅ በክፍልዎ የሚሰጠው የበሳል ድርሰት ትምህርት እንዴት አድርጎ እርስዎ በሚያስተምሩት ወይም በሚያስተምሯቸው ኮርሶችና በሌሎች ኮርሶች ለሚያስፈልጉ የጽህፈት ስራዎች ተማሪዎችን ማዘጋጀት ይችላል? የሚለውን አቢይ ጥያቄ ለመመለስ ለተጀመረው ጥናት መረጃ ማሰባሰቢያ ነው::

እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል:: ስለዚህ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእግስትና በጥሞና በማንበብ ተገቢውን መልስ በመስጠት እንዲተባበሩኝ የምጠይቀው ለቅን ትብብርዎ በቅድሚያ ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ ነው::

ማሳሰቢያ ፣

1. ይህ መጠይቅ የበሳል ድርሰት ኮርስ መምህራንን አይመለከትም::
2. የትምህርት ማስተላለፊያው ቋንቋ አማርኛ ያልሆነ ኮርስ የሚያስተምሩ መምህራንን አይመለከትም::
3. ይህ መጠይቅ የሚሟላው በዚህ ዓመት/ 1988 ዓ.ም./ ለሚያስተምሯቸው ኮርሶች ብቻ ነው:: ኮርሶቹም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀን ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የሚሰጡት ብቻ ይሆናሉ::

እባክዎ መጠይቁን ከሞሉ በኋላ ለክፍሉ ጸሐፊዎች ይመልሱ::

የሚያስተምሩት ኮርስ ምንድን ነው? /ከአንድ በላየ ከሆነም ሁለቱንም ይጻፏቸው/ ________
________________________________________

2. በኮርስዎ ምን ዓይነት ጽሁፎች ናቸው ተማሪዎች የሚጽፏቸው? / ዓይነታቸውን ይዘርዝሩ / ምሳሌ:- ሐተታዊ ፈተናዎች (essay exams) ፣ ሂሳዊ ጽሁፎች ፣ ምናባዊ ጽሁፎች ፣ ከመጀመሪያ ወይም ከሁለተኛ ምንጭ ላይ በመመስረት የሚደረጉ የምርምር ወረቀቶች፣ ሪፖርቶች፣ ወዘተ. /________________________________________
________________________________________
________________________________________

3. ተማሪዎች በሴሚስተሩ /በኮርስዎ ወይም በኮርሶችዎ/ ምን ያህል የጽህፈት ስራዎች ልምምዶች ማከናወን ይጠበቅባቸዋል? /________________________________________
________________________________________

4. ምን ያህሉ በክፍል ውስጥ ይሠራሉ? ------------------------------- የትኞቹ?-------
----------------------------------------------------------------------

5. ምን ያህሉ በቤት ይሠራሉ?------------------------------የትኞቹ?-----------------
----------------------------------------

6. ምን ያህሉ በቡድን ይከወናሉ? ----------------------------------------የትኞቹ?--------
---------------------------------------------------

7. ምን ያህሉ በግል ይከናወናሉ? -----------------------------------------የትኞቹ? ------
----------------------------------------------------

8. እነዚህን የጽህፈት ዓይነቶች ለተማሪዎች የሚሰጡበት ምክንያት ምንድን ነው? ---------
------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------
-------------------------------------------

9. የጽህፈት ክሂል ኮርስዎን ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ነው ይላሉ?
/ከመረጡት ተርታ ባለው ሳጥን ውስጥ «X»ምልክት ያስቀምጡ/

እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ☐
በጣም አስፈላጊ ነው ☐
አስፈላጊ ነው ☐
አስፈላጊ አይደለም ☐

10. የተማሪዎችን ጽሁፍ በሚያርሙበት ወቅት ትኩረት የሚያደርጉት ምን ላይ ነው? -----
------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------

11. ለተማሪዎች ከሰጧቸው የጽህፈት ስራዎች ውስጥ አስቸጋሪ ሆነውባቸዋል
የሚሏቸው የትኞቹ ናቸው? ------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------

12. እነዚህ የጽህፈት ዓይነቶች አስቸጋሪ /ከባድ/ የሆኑባቸው ለምን ይመስልዎታል? -------
------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------

13. በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ በአብዛኛው ተደጋግመው የሚታዩ ችግሮች አሉ?
አሉ ☐ የሉም ☐

14 ለተራ ቁጥር 13 መልስዎ «አሉ» ከሆነ ምን ዓይነት እንደሆኑ ይግለጹ፡፡ /ለምሳሌ መረጃ በተገቢው ቦታ ያለመጥቀስ፣ የጥቅስ አወሳሰድና አቀማመጥ፣ የሃሳብ አወራረድ፣ የመረጃ ማቀናበር፣ የሰዋሰው፣ የቃል አመራረጥ፣ የስራዓተ ነጥብ አጠቃቀም ወዘተ. ስህተቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡/ በሠረዝ መዘርዘሩ በቂ ነው/ -----------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------

15 ስለተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ የሚሰጡት አስተያየት ካለ አጠር አድርገው ይግለጹ፡፡
/ለአስተያየትዎ ቦታ ካነሰዎ ጀርባውን ገጽ ይጠቀሙ/ -----------------------------------

አባሪ ሀ. 2 . የተማሪ መጠይቅ

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

በተማሪዎች የሚሞላ መጠይቅ

መግቢያ

ይህ መጠይቅ ተማሪዎች ከበሳል ድርሰት ኮርሶች ውጭ በሌሎች የአማርኛ ኮርሶች የሚያጋጥሟቸውን የጽሁፍ ስራዎች በቀላሉ መከወን እንዲችሉ በድርሰት ትምህርት እንዴት አድርጎ መርዳት /ማዘጋጀት/ ይቻላል? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ለተጀመረው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ነው:: እያንዳንዳችሁ የምትሰጡት መረጃ ለጥናቱ መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል:: ጊዜያችሁን በመውሰድ ስለምታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

ማሳሰቢያ

ይህ መጠይቅ ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ስነጽሁፍ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ በምትወስዷቸው ኮርሶች በአማርኛ ቋንቋ እናንተ የምትከውኗቸውን የጽህፈት ስራዎች ብቻ የሚመለከት ነው:: በአማርኛ ቋንቋ ምንም ዓይነት ኮርስ የማትወስዱ እና/ወይም በአማርኛ ቋንቋ ምንም ዓይነት ጽሁፍ ለተለያዩ ኮርሶች የማትጽፉ /በዚህ ሴሚስተር/ ከሆነ ይህን መጠይቅ መሙላት አይጠበቅባችሁም::

I . ባሁኑ ጊዜ ባከናወንካቸው እና/ወይም በምታከናውናቸው የጽህፈት ስራዎች ቀጥለው ከተዘረዘሩት ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ የሆኑትን ከ1 - 5 ደረጃ በመስጠት በእያንዳንዳቸው በተተወው ክፍት ቦታ ላይ አስቀምጥ::

/1 ማለት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፣ 2 ማለት በጣም አስፈላጊ ነው፣3 ማለት አስፈላጊ ነው፣ 4 ማለት በዝቅተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው እና 5 ማለት ፈጽሞ አያስፈልግም ማለት ነው::/

-------- 1 . ሃሳብን በተጠያቂያዊና በተቀናበረ መልኩ ማቅረብ

------- 2 . ተጠያቂያዊ /logical/ ግንኙነት በዐ/ነገሮች፣ አንቀጾች እና በምዕራፎች መሀከል መፍጠር

-------- 3 . መረጃን መተንተን

-------- 4 . ሃሳብን በሌች ድርሳኖች ወይም ምርምሮች ማጎልበት

-------- 5 . የሰዋሰውና የዐ/ነገር መዋቅር ጥናት

-------- 6 . ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም

-------- 7 . ስርዓተ ነጥብና ፊደል አስተካክሎ መጻፍ

-------- 8 . ቢጋር መንደፍ

-------- 9 . ለየነጥቦቹ እንደአስፈላጊነታቸው ተገቢውን አፅንኦት መስጠት

-------- 10. የመጻፉ ፍጥነት

-------- 11. ንድፍና ክለሳ ማድረግ

-------- 12. አርትኦት ማድረግ

-------- 13. ጥሩ ማጠቃለያ ማቅረብ

-------- 14. መረጃን በተገቢው ቦታ መጥቀስና መሠነድ/ምንጩን ማመልከት/

-------- 15. ማሳጠር

-------- 16. ማስፋፋት

-------- 17. ውስብስብ ሃሳቦችን በተገቢው ጥራት መግለጽ

II . የሚከተሉትን ጥያቄዎች እያንዳንዳቸውን እንደ የባህሪያቸው መልስ፡፡

18. የበሳል ድርሰት ትምህርት ባሁኑ ጊዜ ለምታከናውናቸው ወይም ላከናወንካቸው ጽሁፎች ምን ያህል ረድቶሃል?

ሀ / እጅግ በከፍተኛ ደረጃ

ለ / በከፍተኛ ደረጃ

ሐ / በበቂ ሁኔታ

መ / በዝቅተኛ ደረጃ

ሠ / እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ

19. በቡድን የምትከውናቸው ጽሁፎች አሉ?

ሀ . አሉ ለ . የሉም

20 . ለተራ ቁጥር 19 መልስህ «ሀ» ከሆነ ከአጠቃላይ ስራዎቹ ምን ያህሉን እንደሆነ በመቶኛ/በፐርሰንት/ ግለጽ፡፡

በቡድን ----------- %

በግል ----------- %

21. በቡድን በማከናወን ያጋጠመህ ችግር አለ?

ሀ . አዎ ለ . የለም

22. ለተራ ቁጥር 21 መልስህ ሀ ከሆነ ምን ዓይነት ችግር እንዳጋጠመህ በአጭሩ ግለጽ፡፡ ---

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

23. ጽሁፍን ከመጀመርህ በፊት፣ በመጻፍ ላይ እያለህና ከመጻፍህ በኋላ ምን ዓይነት ደረጃዎችን ወይም ሂደቶችን ታልፋለህ? ----------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

የትምህርት ዓመት ----------------------------------------

አቢይ ትምህርት / Major / ------------------------------

መለስተኛ ትምህርት / Minor / ------------------------------

ስለትብብርህ/ሽ በድጋሚ አመሰግናለሁ/

## አባሪ «ሰ» - የበሳል ድርሰት ኮርሶች ቢጋሮችና መግለጫ

### ሰ . 1 .የበሳል ድርሰት ኮርሶች ቢጋሮች

### ሰ . 1 . 1 የበሳል ድርሰት ቢጋር

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

በቋንቋዎችና ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስነጽሁፍ ክፍል

<u>የበሳል ድርሰት I (ELAm 203) ቢጋር</u>

1 . የትምህርቱ ዓላማዎች

1.1 የቃላትን ዓይነቶችና ባህርያትን ማስለየት

1.2 ትክክለኛ ዐረፍተ ነገር መጻፍን ማለማመድ

1.3 የአንቀጽ አጻጻፍን ማለማመድ

2 . የትምህርት ዝርዝር ርዕስ

2.1 የቃላት ትምህርት

2.1.1 የቃላት ዓይነቶች

2.1.2 የቃላት ባህርያት

2.1.3 የቃላት አጠቃቀም

2.2 ዐረፍተ ነገር

2.2.1 የዐረፍተ ነገር ዓይነቶች

2.2.2 የዐረፍተ ነገር ባህርያት

2.3 ስርዓተ ነጥብ

2.4 የአንቀጽ አጻጻፍ

2.4.1 የአንቀጽ ባህርያት

2.4.1.1 አንድነት

2.4.1.2 ጽምረት (ግጥምጥምነት)

2.4.1.3 ጉልህነት

2.4.2 የአንቀጽ ግንባታ

<u>ዋቢ መጽሐፍት</u>

<u>ለበሳል ድርሰት I እና II ( ELAm 203/204)</u>

ተስፋዬ ሸዋዬ /1986/ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ችሎታን ማዳበር:: አዲስ አበባ፣ት.መ.ማ.ማ.ድ

ዬናስ አድማሱና ሌሎች /1966/ አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ:: አዲስ አበባ፣ አአዩ. የኢትዮጵያቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል /ያልታተመ/

ዳኛቸው ወርቁ/1977/ የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ:: አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

Arnaudet, Martin L. Mary Ellen Barrett (1990). Paragraph Development. 2nd Ed. EnglewoodCliff; Regents/ Prentice Hall.

Bakerm Rance G. & Billie Philipe (1987). The sampler: Patterns for Composition 2nd Ed. Lexington; Dc. Heath and Company.

Clifton, Lucile & Alexander Macgibbon (1968). Compostion: An Approach Through Reading. New Your; Harcourt.

Dougherty, Barbey Nyce (1984). Composing choices for Writers: A Cross-Disciplinary Rhetoric. New Yourk;

Ezor, Howin & Jill Lewis (1984) From paragraph to Essay: A process approach for Beginning college writing. New York; McGraw-Book company.

Guth, Hans P(1989) The Writers Agenda & Wadsworth writer's Guide (shonker edition). Belmont: Wadson publishing company.

Hadges, John C. & Others (1990). Harbrace College Handbook. 11th Ed. SanDiego, New Yourk; Harcourt Brace Jovanovich, publishers.

Marius Richard & Harvey S.Wioner (1988) The McGraw-Hill College Handbook. New York; McGraw-Hill Book Company.

ለ . 1 . 2 የበሳል ድርሰት II ቢ.ጋር

*አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ*

*ቋንቋዎች ጥናት ተቋም*

*የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል*

<u>የበሳል ድርሰት / ELAm 204/ ቢ.ጋር</u>

*<u>የትምህርቱ ዓላማ</u>*

በዚህ ኮርስ መጨረሻ ተማሪዎች ድርሰት ለመጻፍ ዘገባ ለማቅረብና መጣጥፍ ለማዘጋጀት እንዲችሉ በተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች የጽህፈት ችሎታቸውን ለማዳበር ልምምድ ያደርጋሉ፣ ይጽፋሉ ልዩ ልዩ ጽሁፎችን አንብበው ይመረምራሉ፣ ሪፖርትም ያቀርባሉ።

*<u>የትምህርቱ አርዕስት</u>*

1 . የአንቀጽ ክለሳ

2 . የጽሑፍ ዐይነቶች

2.1 የማሳወቂያ / Informative / ጽሑፍ

2.2 ኪነታዊ / Creative /

2.3 የማግባቢያ /Persuassive/ ጽሁፍን በሚመለከት ገለጻ ይደረጋል

3 . የድርሰት አጻጻፍ መሠረታዊ መርሆዎች

3.1 የርዕስ አመራረጥንና ርዕስን ማጥበብ

3.2 ቢ.ጋር መንደፍ

3.3 ድርሰት ረቂቅ ማውጣት

3.4 የተሟላ ድርሰትን የመጻፍ ልምምድ ያደርጋሉ

4 . የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች

4.1 ገላጭ

4.2 ተራኪ

4.3 አስረጂ

4.4 አከራካሪ ድርሰቶች ላይ ልዩ ልዩ ልምምድ ያደርጋሉ::

5 . የመጽሐፍ ዘገባ አጻጻፍ

<u>መመዘኛ</u>

የክፍል ውስጥ መለማመጃዎች 50% ሲኖራቸው፣ የመጨረሻው ፈተና 50% ነጥብ ይኖረዋል::

1 . በተለያዩ የድርሰት ዓይነቶች ይጽፋሉ

2 . አንድ የታተመ መጽሐፍ አንብበው የመጽሐፍ ዘገባ ያቀርባሉ

## *ለ . 2 የበሳል ድርሰት ኮርሶች መግለጫ*

Department of Ethiopian Languages & Literature Course Description

ELAm 203 Advanced Composition I (3)

Definition of the forms of non-fiction writing, semantic and structural relations of words in sentences; writing grammatically correct sentences; paragraph writing; unity, coherence, emphasis, the topic sentence; paragraph development using details, examples, comparison and contrast.

ELAm 204 Advanced composition II (3)

Writing essays; choosing a topic, narrowing a topic, outlines, developing outlines, transitions, unity, coherence and enphasis, point of view, tone; the different forms of essay writing; exposition, narration, description, argumentation. (prerequisite ELAm 203)

*<u>አባሪ «መ» የቃለመጠይቅ ጥያቄዎች</u>*

ከበሳል ድርሰትና ከሌሎች የአማርኛ ኮርሶች መምህራንና ተማሪዎች ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ የቀረቡት የመነሻ ጥያቄዎች ከዚህ በታች በየጎራው የተዘረዘሩት ናቸው::

መ.1 ለበሳል ድርሰት ኮርሶች መምህርና ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

ሀ / ለመምህሩ የቀረቡ ጥያቄዎች

- በኮርሰዎ ምን ዓይነት የጽህፈት ልምምዶች ይከወናሉ?
- የተማሪዎችን ድርሰት በሚያርሙበት ወቅት ምን ላይ ነው ትኩረት የሚያደርጉት?
- ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ በመለዋወጥ አርመው ያውቃሉ?
- በክፍልዎ የጽሁፍ ሂደት ላይ በማተኮር የሚደረግ የጽሁፍ ልምምድ አለ?
- ተማሪዎች የጽሁፍ ልምምዶችን ከሌሎች ስራዎች ጋር በቅንጅት ወይስ በተናጠል ነው የሚያደርጉት ?
- እርስዎ ያስተማሯቸው ተማሪዎች በሌሎች ኮርሶች የሚያጋጥሟቸውን የጽህፈት ስራዎች የመከወን ብቃት መርምረው ያውቃሉ?

ለ / ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

- መምህራችሁ ለጽሁፎቻችሁ የሚሰጧችሁ አስተያየት በምን ላይ ያተኮረ ነው?
- የምታደርጓቸው የጽህፈት ልምምዶች በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው?
- የጽህፈት ልምምዶቹን በምን መልክ ነው የምታከናውኑት?

መ.2 ለሌሎች ኮርሶች መምህራንና ተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

ሀ / ለመምህራን የቀረቡ ጥያቄዎች

- በእርሰዎ ግምት ተማሪዎች ዐረፍተ ነገርን፣ አንቀጽንና ባጠቃላይ ሙሉ የጽህፈት ስራን በመከወን ያላቸው ደረጃ ምን ያህል ነው?
- ጥሩ መጻፍ አለመቻል ኮርስዎን በጥሩ ውጤት ለማለፍ ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው?
- ጥሩ ጽህፈት ክሂል በአንድ ጊዜ ወይም በተወሰነ ኮርሶች ብቻ ሊጨበጥ ይችላል የሚል እምነት አለዎት?
- የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል አስመልክቶ ከድርሰት መምህር ጋር በግል ወይም በክፍሉ አማካይነት ተሰባስባችሁ ተወያይተው ያውቃሉ?
- ተማሪዎች በኮርስዎ የሚጽፏቸውን ጽሁፎች አርመው ይመልሱላቸዋል?

ለ / ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

- አሁን በምትወስዷቸው ኮርሶች ምን ዓይነት የጽህፈት ስራዎችን በአማርኛ ትጽፋላችሁ?
- የትኞቹ የጽህፈት ስራዎች አስቸጋሪ ሆነውባችኋል?
- መምህራኑ የጽህፈት ስራዎቹን አከዋወን አስመልክቶ የሚያቀርቡላችሁ መመሪያ አለ?
- ጽሁፎቻችሁ ታርመው ይመለሱላችኋል?

## አባሪ «ረ» በተማሪ ጽሁፎች ላይ የተደረገ የጽሁፍ እርማት ትንተና

### ረ. 1 የጽሁፍ እርማት ክፍፍል ( Taxonomy )

| አይ ነ ት | | ገ ለ ጻ | ም ሳ ሌ |
|---|---|---|---|
| 1 . መካኒክስ | | | |
| | 1.1 ፊደል | - መምህሩ ፊደሉን በመክበብ ተፈላጊውን እርማት ይጽፋል<br>- መምህሩ የጎደለውን ፊደል ብቻ በመክበብ ጨምሮ ይጽፋል<br>- መምህሩ ፊደል የጎደለውን ቃል ሙሉ በሙሉ አስተካክሎ ይጽፋል | - የዓያሌ<br>- ጓደኛ (ዬ)<br>የሆነች<br>- የሆች |
| | 1.2 አጻጻፍ | - መምህሩ ትክክል ያልሆነውን አጻጻፍ ይከባል<br>- መምህሩ በጽሁፍ አስተያየት ይሰጣል | - ትምህርት ቤቶች<br>- ህዳግ በአንድ በኩል ብቻ ነው የሚጠብቀው |
| | 1.3 ስርዓተ ነጥብ | - ስርዓተ ነጥብ የሚያስፈልግበትን ቦታ በመክበብ በውስጡ ስርዓተ ነጥቡን ይጽፋል::<br>- መምህሩ የጽሁፍ አስተያየት ያቀርባል | - ተምችቶች ተኝቷል(::)<br>- እንዴ ስርዓተ ነጥብ ስትፈልግ ብቻ ነው የምትጠቀመው? |
| 2 . ሰዋሰው | | - መምህሩ ስህተቱን በመክበብ የስህተቱን ዓይነት ይጽፋል<br>- የሰዋሰው (የአገባብ) ስህተት የፈጠረውን ቃል ወይም ፊደል ሠርዞ አስተካክሎ ይጽፋል | - በምናገኘው ወይም በምናወጣቸው<br>በረራውን በረራው |
| 3 . ቃላት | | - መምህሩ አላስፈላጊ ነው ያለውን ቃል ይሠርዛል<br>- መምህሩ ቃሉን በመክበብ ተለዋጭ ቃል ይሰጣል | - የመሳሰሉትን በማሰብ ሲሆን<br>- ለምጹ ጠባሳው |
| 4. አደጃጀት | | - መምህሩ አስተያየት ይሠጣል<br>- አንቀጽ የሚከፈልበትን ቦታ ያመለክታል<br>- መምህሩ አስተያየት ይሰጣል | - ቋጠር ፈታ ቋጠር ፈታ ሆነ<br>- የአንቀጽ አከፋፈል ችግር አለበት<br>አዲስ አንቀጽ<br>- የተመደቡበኩት<br>- ሃሳብ ያንሰዋል<br>- ምን የተለየ ነገር አጋጠመህ? ታዲያ ለትዝታ የሚሆን |
| 5. ይዘት | | | - ከጨዋታው ወጣህ<br>- ይወጣ የሊለውን እንዴት አወቅህ |

### ረ. 2 የጽሁፍ እርማት አተናተን

የጽሁፍ እርማቱን ትኩረትን ለመመርመር የተሰበሰቡት ድርሰቶች በቅድሚያ ለእያንዳንዳቸው የመለያ ቁጥር (ኮድ) ተሰጥቷቸዋል:: በማስከተል ከላይ በተዘረዘሩት አምስት የጽሁፍ ገጽታዎች አኳያ እያንዳንዳቸውን በየመለያ ቁጥራቸው ተዘርዝረዋል:: ከዚያም በየጽሁፎቹ ላይ የተሰጠው እርማት ዓይነቱን በመመርመር በየጎራው ታሊ በማድረግ ተቀምጧል:: በየጎራው ያሉትም ታሊዎች በእያንዳንዳቸው ስር (በመካኒክስ፣ በሰዋሰው ወዘተ.) ተደምረው በመቶኛ ምን ያህል እንደሆኑ ከአጠቃላይ እርማቱ አንጻር ተሰልተው በሠንጠረዥ በማስፈር በጥናቱ ተተንትነዋል::

## አባሪ «ሐ» - የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎች ዝርዝር

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ
ክፍል በ1987 የመደበኛው መርሃ ግብር ተማሪዎች የመጀመሪያ ዲግሪ
ማሟያ ጽሁፎች ዝርዝር

| | | |
|---|---|---|
| 1. | አብርሃም አለሙ | የግራዋ ወረዳ አካባቢ ገበሬዎች ደርሽ/ የስራ ዘፈን ግጥሞች ትንተና |
| 2. | ይጋርዱልሽ ተቀባ | ከ1960_64 ዓ.ም መጨረሽ ድረስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ግጥሞች ስብስብ፣ መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር |
| 3. | ብርቱካን መንገሽ | የአላባ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ |
| 4. | በላይ ሠይድ | ደራሲ ገበየሁ አየለና የስነጽሁፍ ስራዎቹ |
| 5. | አበበ በላይ ተ/ማርያም | የዋንዛዬ ጸበልተኞች ስነቃላዊ ግጥሞች |
| 6. | በቀለ ኂ/ማርያም | የደሴ ከተማ ሠፈርተኞች አስያየምና ስለከተማዋ የሚነገሩ አፋዊ ግጥሞች ይዘት |
| 7. | ማርዬ ተፈራ | አበይት የአተረጓጎም ድክመቶችና ተርጓሚው የተከተለው የትርጉም አመለካከት በ «አሳረኛው» ትርጉም ውስጥ |
| 8. | መሠረት አከለ | ምስለ ሴት ከ1980-86 ዓ.ም በወጡ የግጥም መድበሎች ውስጥ |
| 9. | ሙሉዓለም ታምሬ | የትምህርት ዕቅድና የክፍል ውስጥ ትግበራ ጥናት በእንጦጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የቀለምና የሙያ ትምህርት ቤት |
| 10. | ሽምሽዲን የሱፍ | ሜርይስ በምዕራብ ሐረርጌ ኦሮሞ |
| 11. | አንለይ ጣሴ | በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽህፈትን ክሂል ለማዳበር መልመጃዎች እንዴት መቅረብ አለባቸው |
| 12. | ታደለች ተስፋው | ከ1955 - 1959 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጡ ግጥሞች ናሙና መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር |
| 13. | አበባው ይሁኔ | በ «አዲስ ዘመን» ጋዜጣ ላይ ከ1950 - 54 ዓ.ም የወጡ የናሙና ግጥሞች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎች ጋር |
| 14. | ኃ/ሚካኤል ተክሉ | በአዲስ ዘመን ጋዜጦች ላይ የወጡ ግጥሞች መዘርዝር ከአጫጭር መግለጫዎቻቸው ጋር /1933 - 1939/ |
| 15. | አምባቸው አለባቸው | በፎገራ ወረዳ የሴት ጣውንት ግጥሞች ይዘትና ቅርጽ ትንተና |
| | ታፈረ በላይ | የኢትዮጵያ አድቬንቲስት የውዳሴ መዝሙሮች ቅርጽና ይዘት |
| 16. | | |
| 17. | አስፋው ገረመው | በኢትዮጵያ ሬዲዮ በኪነጥበባት ኘሮግራም ከ1956 - 1966 ዓ.ም የቀረቡ ዝግጅቶች መግለጫዊ መዘርዝር |
| 18. | ሰሎሞን ዮሐንስ | በ1984 የተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የሰዋሰው ይዘትና አቀራረብ ግምገማ |
| 19. | ጌታቸው ገበየሁ | በጅጅጋ አካባቢ የሚኖሩ ሶማሌዎች ለግመሎቻቸው የሚገጥሟቸው ግጥሞች ይዘት ትንተና |
| 20. | ጠጂቱ በሬቻ | ከ1983 እስከ 1986 ዓ.ም ታትመው በገበያ ላይ የዋሉ የአማርኛ ዘፈን ግጥሞች መዘርዝር፣ ስብስብና አህዛዊ ትንተና |
| 21. | ደጀኔ ማንደፍሮ | የሴተኛ አዳሪዎች የስም ለውጥ በአዲስ አበባ |

## አባሪ «ሸ» - ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮችና የሚያልፉበት የጽሁፍ ሂደት

ሸ .1 ተማሪዎች በቡድን በማከናወን ያጋጠሟቸው ችግሮች
(በተማሪ መጠይቅ ቁጥር 22 የተሰጠ መልስ ዝርዝር)

- የቡድን ስራ ከሆነ ቸል የማለት ሁኔታ ይታያል:: ምክንያቱም እንደራሳችን ስራ ስለማናየውና ሃሳባችንን በሌላው ላይ ስለምንጥል::
- በቡድን የሚከናወኑት ስራዎች የግልንም አስተያየት መቀበል የግድስለሆነ የሁሉንም ሃሳብ ለማስተካከል በስራ ላየ ጌዜን ይወስዳል፣ በመጽሃፎች መጠቀም ስዓት ለሃሳቡ ያለው አመለካከት ስለሚለያይ ጥረትነቱ ያጠራጥራል::
- ስራውን በቡድን መስራት ከጊዜ አንጻር እንዲሁም የአንዱ ሃሳብ ለሌኛው ጣዕም (ተቀባይነት) አለመስጠት ክርክር ማስነሳቱ ጥሩ ፈር ቀዳጅ ሆኖ ሳለ ውሳኔ ወይም ተቀባይነት ያለው ሃሳብ ላይ አለመድረስ በቡድን መሀከል ቅራኔ ይፈጥራል:: በግል ደረጃ ከሆነ ግን ያለምንም ገደብ የፈለገውን ነጥብ (የስራውን አጥጋቢነት) ያገኛል::
- አብረውኝ የሚሰሩት ልጆች ስራውን በኔ ላይ ብቻ ጥለው ይሄዳሉ::
- አቦ ጭቅጭቅ ነው:: አንዳንዱ በጆሮ ቦታ እጅ እንቀጥል ይልሀል:: መድሃኒቱ አምባገነን መሆን ነው::
- 1 . ከጓደኞቼ ጋር በሃሳብ አለመጣጣም
  2 . የጊዜ ሁኔታ
  3 . የምንግዴለሽነት መታየት
- አብሮህ የሚሠራው ተማሪ ስራውን አንተ ላይ መተው መፈለጉ ትልቁ ችግር ነው:: ሌላው ችግር አብሮ ለመስራት አመቺ ጊዜና ሁናቴ አይኖርህም:: ስለዚህ ብዙውን ጊዜ እራስህ ለመስራት ትገደዳለህ:: በሌሎቹ ስራ አለመረካት፣ ሌሎቹ 'logical' ለሆነ ክርክር ዝግጁ አይሆኑልህም::
- ለመስራት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሐሳብ አለመጣጣም ሊኖር ስለሚችል::
- በቡድን ለመሰባሰብ በዋናነት የጊዜ ጉዳይ፣ በአንድ ኮርስ በተለያየ አቅጣጫ በቀቀናዊ ስራ እንድሠራ መነዝነዝ
- በቡድን ስራ ጊዜ በአብዛኛው በሀሳብ ያለመግባባት ይኖራል:: በሌላ በኩል ደግሞ ለስራው ሁሉም እኩል ፍላጎት ስለሚኖረው ጥራት ይጎድላል:: ቸልተኝነት ይበዛል::
- ሰው ለሰው አስተሳሰቡና አመለካከቱ የተለያየ በመሆኑ አንደኛው ይሄ ይሁን ሲል እኔ ደሞ ሌላ ይሁን ስል በሚፈጠረው ክርክር ግጭትን ፈጥረናል::
- በሀሳብ ለመስማማት አለመቻል:: ወይም ደግሞ ለመስማማት ቢቻልም ስምምነት ለመድረስ በሚደረግ ክርክርና ውይይት ረዥም ጊዜ መስዋት ማድረግ:: ስምምነት ለመፍጠር ሲባል ያላመኑበትን ነጥብ መቀበል::
- አዎ በቡድን ስስራ ያጋጠመኝ ችግር እንደሚመስለኝ ከሆነ ያለፍላጎታቸው የሚማሩ ተማሪዎች በቡድን participate የማድረግ ከልባቸው ወይም ግልጽ ሆነው ሐሳባቸውን አያወጡም::
- በቡድን በምንሠራበት ጊዜ (ጽሁፍን) በአብዛኛው የተለያዩ ሃሳቦች ስለሚጋጩ የሀሳብ አለመጣጣም ያጋጥማል:: ስለዚህ ይህ በቡድን በሚሰራ ስራ ላይ ጎልቶ የሚታይ ችግር ነው::

- በቡድን ለመስራት በቀጠሮው ለመገናኘት በጣም ችግር አለ አንዱ ለመጣ ሌላው ይቀራል በዚህ መሀከል ሌላው ስራ እንዳንሠራ ሠአታችንም ይቃጠላል::
- በቡድን ስራዎችን በምናከናውንበት ጊዜ የሀሳብ አለመጣጣም ወይም አለመግባባትና በአንድ ሀሳብ አለመስማማት ዋናው ችግር ነው:: በተጨማሪ የመገናኘት ችግር አለ::
- አንዱ የሚያቀርበው ሀሳብ ሌላው አባል ሊቀበለው አለመቻል፣ ተሳትፎ አለመኖር፣አንዱ በሌላው ላይ ሀሳቡን መጣልና ሐላፊነት አለመስማት፣
- በሃሳብ አለመጣጣም፣ ግዴለሽነት፣ አንዱ ባንዱ ላይ ጥገኛ መሆን::
- በቡድን የተሰጠንን ስራ በምናከናውንበት ጊዜ በመካከላችን አለመግባባት ይፈጠራል:: ለመስራት በተዘጋጀንበት ሰአት ግማሹ ስለሚቀር እሱ ሳይሰራ እኔ ምን በወጣኝ አይነት ነገር፣ ስራው ለብዙ ጊዜ ስለሚጓተት ስራው ጥራት አይኖረውም::
- የቡድን አባላት የተዋቀሩት በመመራረጥ ሳይሆን በዘፈቀደ በመሆኑ ለስራ ያለን ፍላጎት የተለያየ በመሆኑና ስራውን ለመስራት የሚንገናኝበት ሰዓት ላይ አለመስማማት
- የሀሳብ አለመጣጣም፣ በሰዎች (በጥቂቶች) ትክሻ ላይ ሆኖ ተመሳስሎ ለውጤት መብቃት፣ በጊዜ ያለመጠቀም፣ ነገሮችን ወይም የተሰጠውን የቡድን ስራ ያለመገንዘብና መሠል ጉዳዩች ችግሮች ናቸው::
- በዚህ በቡድን ስራ ላይ የተለያዩ ችግሮች ይገኛሉ፣ እነዚህም 1ኛ ከቡድኑ ጋር በተገቢው ጊዜና ሰዓት ስራውን አለመስራት፣ 2ኛ ለስራው አስፈላጊ የሆነ (material) እጥረት ችግሮች አጋጥመውኛል::
- ያጋጠመኝ ችግር የቡድኑ አባላት በተቀጣጠርንበት ጊዜና ቦታ አለመገኘት ተጠቃሽ ችግር ነው:: እንዲሁም በስራው ላይ የተለያዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ስለሚሆኑ ለስራው የቡድን ስራ እንቅፋት ነው:: በአጭሩ የፍላጎት መለያየት ስላለ::
- በሀሳብና በምናነሳቸው ነጥቦች ላይ ያለ መስማማት ችግር አለው:: ከዚህ በተጨማሪ እኔ ያነሳሁት ነጥብ መጀመሪያ መስፈር አለበት የሚልም ችግር አለው::
- በሀሳብ አለመስማማት፣ በቃላት ምርጫ አለመስማማት፣ የተስማሙበት ሀሳብ ቢሆን በማስፈር ጊዜ እንደጸሀፊው ስሜት የመግለጽ (በአገላለጹ ሒደት) አለመስማማት
- ያጋጠመኝ በቡድን መስራት ላይ ጸባይ ለጸባይ አለመስማማት የሀሳብ መጋጨት ያንን ለማስወገድ ጊዜ ይፈጃል::
- በቡድን ስራ ላይ ከሚያጋጥሙት ችግሮች አንዱ (ያጋጠመኝ) አብረን ቀምንሰራ ልጆች ጋር በሀሳብ ያለመግባባት ሲሆን ይሒውም ሁሉም የራሱን ሐሳብ ማጽደቅ ስለሚፈልግ በአንድ ሀሳብ ሆኖ መስራት ያስቸግራል::
- 1. ቀጠሮ ሰዓት አለማክበርና መቅረት:: 2. ስራውን በአንድ ሰው ላይ የመጣል አዝማሚያ፣ 3. የቡድኑ አባላት ከቡድኑ ተማሪዎች የሚሻላቸው ተማሪ ያቀረበውን ሐሳብ ያለማንገራገር መቀበል:: 4. የለፋም ያልለፋም እኩል ውጤት የማግኘት፣
- በአጠቃላይ ለመስራት በሚፈለግበት ጊዜ በአንድ ላይ ሆኖ ለመወያየት አንዱ ሲመጣ ሌላው የመቅረትና በሀሳብ አለመስማማት ይፈጠራል::
- ብዙ ጊዜ የሀሳብ አለመጣጣም ችግር አጋጥሞኛል:: ግን በቡድን መሠረት የተለያየ ሀሳብ እንዲነሳ እገዛ ያደርጋል:: እንዲህ ሆኖ ግን መቋጫው ስምምነት ላይ ሲደረስ ነው:: እና የሀሳብ አለመጣጣም የቡድን ስራ የሚባለውን እስከ ማስጠላት ደረጃ አድርሶብኛል::

ሸ. 2. ተማሪዎች ጽሁፋቸውን ለማውጣት የሚያልፉበት ሂደት (ለተማሪ መጠይቅ ቁጥር 23 በተማሪዎች የተሰጡ መልሶች)

- በመጻፍ ላይ እያለሁ የመረጋጋት ሁኔታውም እየጣመኝ ይመጣል:: ሳልጀምር ግን ጭንቀቶች ይበዙብኛል:: ከጨረስኩ በኋላ ግን ዘሀሳቦች ነጻ ሁኜ ያው ለውጤት ማሰብ ይሆናል:: ከዚህ ላይ ግን መታየት ያለበት ጽሁፍን ከመጀመሬ በፊት በምን ሁኔታ ልጻፈው የሚለው ሀሳብ ነው::
- በጽሁፍ መጀመሪያ ቢጋር ላይ የሚቀርበው ዋና ሀሳቦችን መምረጥ ላይ፣ ስራ/በጽሁፍ ደግሞ የሐሳቡን ማስቀመጥ ብሎም ጽንሰ ሃሳቡን ማጠቃለል ላይ ያለው ተከተላዊ ሂደት
- ቢጋር ማሙጣት፣ መረጃ መሰብሰብ፣ ሐሳብን ማዋቀር የሚፈለገውን ሀሳብ የያዘ ንድፍ በማሙጣት ሀሳብን ማብራራት ማጕላበትና የመጨረሻ ጽሁፍን ማስቀመጥ (ማውጣት)
- ጽሁፍ ከመጀመሬ በፊት ቁጥ ብዬ ስለምጽፈው ነገር አስባለሁ፣ በመጻፍ ላይ እያለሁ ጽሁፌ እስከጣመኝ ድረስ ደጋግሜ እጽፋለሁ፣ እቀዳለሁ፣ እጥላለሁ፣ እንደገና እጽፋለሁ፣ ከጻፍኩ በኋላ ለጓደኛዬ አስገመግማለሁ::
- ንድፍ ማሙጣት አለብኝ:: ያንን ተከትዬ እጽፋለሁ፣ ለአካዳሚክ ጽሁፎች ቢችል ለሌችም:: አንዳንዴ መነሳሳት ሲያቅተኝ ግን በንዴት ዝም ብዬ መለቅለቅ እጀምራለሁ:: ወይ በኋላ ይጠራል:: ወይ እንዳለ እተወዋለሁ::
- የሀሳብ ቅደም ተከተል ይዘትን ጠብቆ መሄድን::
- በመጀመሪያ ስለምጽፈው ነገር አስባለሁ:: በሚገባ ማለት የምፈልገውን ከተረዳሁ በኋላ በተራ ወረቀት ላይ እንዲመርጡልኝ አሰፍራለሁ:: በየርዕሱ ስርና በየአንቀጾችም ዋና ዋና የምላቸውን ሀሳቦች በቢጋር መልክ አወጣና ይህን ተከትዬ እጽፋለሁ:: በየርዕስ ነገሩ ማብቂያ - ጽሁፌን አነብና ማለት የፈለኩትን ማስፈሬን አረጋግጣለሁ:: መጻፍን ሳጠናቅቅም የጽሁፉን ተጠያቂያዊ ሂደትና የመልዕክቱን መተላለፍ አረጋግጣለ::
- ጽሁፍን ከመጀመሬ በፊት የምጽፋቸውን ቃላት ሐረጋት፣ አረፍተ ነገሮች አስባለሁ፣ በአጠቃላይ የምጽፈውን ሀሳብ አውጠነጥናለሁ:: በመጻፍ ላይ እያለሁ ደግሞ ሐሳቡ እንዳይዛባ ጥንቃቄ አደርጋለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ ደግሞ የጻፍኩትን ጽሁፍ እንደገና አነባለሁ:: አንዳንድ ቃላትን ወይም ሃሳቦችን አስተካክላለሁ::
- አስባለሁ ዝም ብዬ አስባለሁ ቢጋር የሚመጣው አይምሮዬ ውስጥ ነው (Amorphus) ለነበረው ሀሳብ አይንና ጆሮ እግርና ጭራ ሲበጅለት፣ ቢጋር ተነደፈ ማለት ነው ከዛ ፍሰስ ይላል ሀሳቤ በቅርጽ በቅርጹ ደግሜ ሳነበው በመጀመሪያው የሃሳብ ፍሰት ያላስተዋልኳቸው ስህተቶች ይከሰቱልኛል አስተካክላቸዋለሁ::
- ንድፍ ማሙጣት፣ መተንተን፣ ማስፋፋትና የተስፋፋውን ቅደም ተከተሉን ተከትሎ ማስፈር::
- ምን ልጻፍ?፣ እንዴት ልጻፍ?፣ ጽሁፌ ምን ያህል አምሯል የሚል ደረጃዎችን እማልፍ ይመስለኛል::
- በመጀመሪያ ርዕስ መምረጥና ሐሳብ ማመንጨት፣ ስለርዕሱ ዋና ዋና ነጥቦችን መደርደር፣ የተደረደሩ ነጥቦችን በማቀናበር እኒህን ሂደቶች መጻፍ
- የአጻጻፍ ስልቶችን ማወቅ፣ ሐሳቤን በተገቢው ለመግለጽ መሞከርና ከጻፍኩ በኋላ ደግሞ ስህተቴን ለማረም ደግሜ ማንበብ ያስቸገረኝን የሚያውቅ ሰው በመጠየቅ ወይም መጽሐፍቶችን በማንበብ ስህተቴን አስተካክዬ እጽፋለሁ::
- ከመጀመሪሬ በፊት ሐሳብና የመጽሐፍ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት:: በመጻፍ ላይ እያለሁ የሚያስፈልገኝ ሃሳብን ማሰባሰብ (አትኩሮት) ከጻፍኩ በኋላ ደጋግሜ ማንበብ ስህተቶችን ለማስወገድ

- መረጃ መፈለግ፣ ሃሳቤን የምገልጽበትን ሁኔታና ቅድመ ተከተል መወሰን (ቢጋር መጻፍ)፣ የተሰበሰበ መረጃና የወሰንኩበትን ቅደም ተከተል መመርኮዝ ቋንቋ መምረጥና ንድፍ ጽሁፍ መጻፍ፣ እንደገና መከለስ (ከዚህ ጊዜ አላስፈላጊ ነጥቦችን ማውጣትና የቀሩ ነጥቦች ካሉ መጨመር::
- ሐሳብን የማሰባሰብ እና የማስተዋል::
- ጽሁፍን ከመጀመሬ በፊት ሌሎች ተመሳሳይ የተሰሩትን ጽሁፎች እመለከታለሁ፣ በመጻፍ ላይ እያለሁ ግን ሙሉ ትኩረት በመስጠት ነው:: ከጻፍኩ በኋላ ግን ክለሳ አደርጋለሁ::
- ጽሁፍን ከመጀመሬ በፊት ለጽሁፌ የሚሆኑትን ነገሮች አዘጋጃለሁ:: በመጻፍ ላይ እያለሁ ሙሉ ትኩርቴን ስለምጽፍበት ነገር በትጋት እሰራለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሰራሁትን ስራ እከልሳለሁኝ:: ስለዚህ እነዚህን ደረጃዎች አልፋለሁ::
- ይህን ስራ ለመጀመር በመጀመሪያ የተለያዩ መጽሐፍን ማገላበጥ፣ መመርመር እጀምራለሁ:: ከዚያም ስራዬን በትዕዛዙ መሠረት እጀምራለሁ:: ይህንንም ስራ በንድፈ ሀሳብ ደረጃ አወጣለሁ:: ከዚያም ዋናውን ስራዬን እጀምራለሁ:: ስራዬንም እንደጨረስኩኝ ከሌላ ስራዎች ጋር አስተያየዋለሁ ስህተት ካለው ስህተቱን አስተካክላለሁ::
- ጽሁፍ ከመጀመሬ በፊት ስለምጽፈው ጉዳይ ያለኝ ዕውቀት፣ መረጃዎቼ ምን እንደሚመስሉና ጥራታቸውን አስባለሁ፣ በመጻፍ ላይ እያለሁ ደግሞ አንባቢዬ እንደምጽፈውና እኔ እንደምፈልግ ይረዳልኛል? አሁን ምን ማለት አለብኝ? እላለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ ደግሞ እንደገና ማስተካከል የሚገባኝ ነገር አለ? እላለሁ::
- ከመጀመሬ በፊት፣ ስለምጽፈው ነገር ዝርዝር ሀሳቦችን በቢጋር መልክ አስቀምጣለሁ:: በመጻፍ ላይ እያለሁ:- ሐሳቤን ሙሉ በሙሉ በምጽፈው ጉዳይ ላይ ሪማድረግ በምክንያት አስደግፌ እጽፋለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ ደጋግሜ በማንበብ ረቂቁን ከመጻፌ በፊት የቀረ ሀሳብ ካለ በመሀል እጨምራለሁ::
- ጽሁፍን ከመጀመሬ በፊት ቢጋር አወጣለሁ:: ከዚያም በአወጣሁት ቢጋር መሠረት ነጥቦችን አስፍፍቼ እጽፋለሁ:: በመቀጠል በአንቀጽ በመከፋፈል በእራፊ ወረቀት አሰፍራለሁ:: በመጨረሽም ያሉትን ጥቃቅንም ሆነ ጉላ ያሉ ስህተቶችን አስተካክየ በዋናው ወረቀት ላይ እገለብጣለሁ:: ከጻፍኩ በኋላም አነበዋለሁ::
- በመጀመሪያ ልጽፍ ከምፈልገው ነገር ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጽሁፎች አነባለሁ:: ከዚያ ልጽፍበት የምችለውን ጉዳይ እመርጣባለሁ:: ቀጥሎም ለጽሁፉ መነሻ የሚሆኑትን ንድፎች አወጣለሁ:: ከዚያም የመጀመሪያውን ረቂቅ እጽፋለሁ ሁለተኛውን ረቂቅ እያስተካከልኩ እጽፋለሁ :: በሦስተኛው ላይ ዋናውን እጽፋለሁ::
- ከመጀመሬ በፊት እንዴትና ምን መጻፍ እንዳለብኝ አስባለሁ:: በመጻፍ ላይ እያለሁ ያሰብኩትን ለማስፈር እጥራለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ ጻፍ ጻፍ ይሰማል::
- ጽሁፍ ከመጀመርኩ በኋላ በመጻፍ ላይ ያለኝ የሀሳብ ለውጥ ሊሆን ይችላል::
- መጀመሪያ ለመጻፍ ሀሳብ በጣም ይከብደኛል ማለትም ወረቀቱንና ብዕሩን ለማገናኘት ከጀመርኩ በኋላ ግን ከአሰብኩት በላይ እጽፋለሁ:: በተለይ አነቃቂ የሆኑ ነገሮች ከወሰድኩ ( ጫት ) በጣም ወረቀትና ቀለም አይበቃኝም::
- በመጀመሪያ ለጽሁፍ የሚረዳኝን መረጃዎች በመሰብሰብ ከአጠራቀምኩ በኋላ ያጠራቀምኳቸውን መረጃዎች በሌላ ወረቀት ላይ ካረቀቅሁ በኋላ ሃሳቦችን ካስተካከልኩ በኋላ ቀጥታ ወደ ዋናው ጽሁፍ ለመጻፍ ያስችለኛል::
- ይህን አረፍተ ነገር ለማለት የፈለገው ነገር ወይም መልዕክቱ ግልጽ አይደለም:: ስለዚህ ለወደፊቱ ለተፈለገው ነገር (መልዕክቱ) ግልጽ አድርጐ ለማቅረብ መጣር ይኖርብኃል::

- በመጀመሪያ አስፈላጊ ነጥቦችን ለመሰብሰብ እሞክራለሁ፣ ከዚያም ሊኖራቸው የሚገባውን ቅደም ተከተል እወስናለሁ:: (ቢጋር) ከዚያም የመጀመሪያ ረቂቅን አዘጋጃለሁ:: ረቂቁን መሠረት በማድረግ የሚጨመረውን እየጨመርኩ አላስፈላጊውን እየቀነስኩ ዋናውን ጽሁፍ አዘጋድና በጽሁፍ የሚታዩ ቃላትና ስርዓተ ነጥቦች ግድፈት ማረም::
- በመጀመሪያ የምጽፈውን ነገር በደንብ አስባለሁ ከዚያም በመጻፍ ላይ እያለሁ ተጠንቅቄ መጻፍ ያለበኝን እጽፋለሁ:: ከጻፍኩ በኋላ በአግባቡና በስርዓቱ መቀመጥ ያለበት ቦታ አስቀምጠዋለሁ:: በመጨረሻም መስጠት ላለብን ክፍል እሰጣለሁ::
- ጽሁፍን ከመጻፌ በፊት እንዴት እንደሚጻፍ በሀሳብ ደረጃ ብዙ ነገሮችን እቀምራለሁ:: በመጻፍ ላይ እያለሁ ደግሞ በሀሳብ ደረጃ ያሉትን በተግባር ለማሳየት የተለያዩ ጥረቶችን አደርጋለሁ:: ማለት የተፈለገውን ሀሳብ በትክክል ለአንባቢም ሆነ ለአዳማጭ ለመግለጽ ተፈላጊ ነገሮችን በተፈላጊው ነገር ላይ ለማምጣት የቃላት ምርጫ ሀሳብን በትክክል ማስተላለፉ (direct way) እናም ሀሳብን በትክክል ማስረዳት::

## ማ ረ ጋ ገ ጫ

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑንና በጥናቱም የተጠቀምኩባቸውን ድርሳናት ዋቢነታቸውን በትክክል ማመልከቴንና መሰነዴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም: - ግርማ አውግቸው

ፊ ርማ: -

በ ታ: - አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ቀ ን: - ሰኔ 1987 ዓ.ም

# Table of Contents

Volume III, Nos. 1-9, 1987-1995

Page

*Number 1*: College of Social Sciences . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

**GEOGRAPHY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**HISTORY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**SOCIAL ANTHROPOLOGY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

*Number 2*: Faculty of Business and Economics . . . . . . . . . . . . . . . . .

**ECONOMICS** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

*Number 3:* Faculty of Education . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

**CURRICULUM & INSTRUCTION** . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**EDUCATIONAL ADMINISTRATION** . . . . . . . . . . . . . . . .
**EDUCATIONAL PSYCHOLOGY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

*Number 4:* Faculty of Medicine . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

**ANATOMY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**BIOCHEMISTRY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**COMMUNITY HEALTH** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**MEDICAL MICROBIOLOGY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**MEDICAL PHYSIOLOGY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

*Number 5:* Faculty of Science . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

**BIOLOGY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**CHEMISTRY** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**GEOLOGY AND GEOPHYSICS** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**PHYSICS** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .
**STATISTICS** . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .